
መሪዎችን ማሳደግ

አውደ ጥናት

# ጽሑፎች

የቅጂ መብት © 2026 HTTP



## 1. ጽሑፎች ምንድን ናቸው?

ጽሑፎች በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኙ የመጻሕፍት ስብስብ ናቸው። በብሉይ ኪዳን ሦስት የመጻሕፍት ስብስቦች አሉ። ሦስቱ ስብስቦች ሕግ፣ ነቢያትና፣ መጻሕፍት በመባል ይታውቃሉ። በዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ደግሞ ጽሑፎች ከሕግ እና ከነቢያት መጻሕፍት በኋላ ተደርድረዋል።

ሆኖም በዘመናዊ መጽሐፍ ቅዱሶች ብሉይ ኪዳን ውስጥ በሦስት የተለያዩ የመጻሕፍት ስብስቦች አልተከፋፈሉም። ነገር ግን እነዚህን ሦስት የተለያዩ የመጻሕፍት ስብስቦች በብሉይ ኪዳን ውስጥ እንዳሉ በማወቅ ኢየሱስ ከሦስቱ የመጻሕፍት ስብስቦች ለትምሕርቱ የሚሆን ግብዓት እንደተጠቀመ ግልጽ ነው (**ሉቃስ 24፡44–45** ይመልከቱ)።


እንደዚሁም ደግሞ ሐዋሪያው ጳውሎስም በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተለያዩ የመጻሕፍት ስብስቦችን እንዳሉ ተረድቶ ነበር። ስለዚህም እንደ ኢሱስም በስብከቱና በማስተማሩ ሂደት ውስጥ እነዚህን የተለያዩ የመጻሕፍት ስብስቦች በመጥቀስ ተጠቅሟል (**የሐዋሪያት ሥራ 28፡23** ይመልከቱ)።


በሕጉ ውስጥ ያሉት መጻሕፍት ኦሪት ዘፍጥረት፣ ኦሪት ዘጸአት፣ ኦሪት ዘሌዋውያን፣ ኦሪት ዘኍልቁ እና ኦሪት ዘዳግም ናቸው። እነዚህ ሁሉ መጻሕፍት የጻፈው ሙሴ ነው። እነዚህ መጻሕፍት ከጥንታዊ ታሪክ በጣም የላቁ ናቸው። ደግሞ ስለ ክርስቶስ እና ስለ ወንጌል ክስተት የሚናገሩ ናቸው (**ዮሐንስ 5፡ 45–47** ይመልከቱ)። በሕጉ ውስጥ ያሉት መጻሕፍት የመጀመሪያ በመሆናቸው ምክንያትም ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት የተለዩ ናቸው። እነዚህ መጻሕፍት ከሌሎች የመጽሕፍ ቅዱስ መጻሕፍት አይጠቅሱም ወይም አያጣቅሱም። ሆኖም በሕጉ ውስጥ የሚገኙት መጽሕፍት በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት በተደጋጋሚ ተጠቅሰዋል ወይም ጥቅም ላይ ውሏል።

የነቢያት መጻሕፍት በመባል የሚታወቁት መጽሐፍት ኢያሱ ወልደ ነዌ፣ መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ፣ መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ (እነዚህ በመጀመሪያ እንደ አንድ መጽሐፍ ነበሩ)፣ መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ፣ መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ (እነዚህም ደግሞ በመጀመሪያ እንደ አንድ መጽሐፍ ነበሩ)፣ ትንቢተ ኤርሚያስ፣ ትንቢተ ሕዝቅኤል፣ ትንቢተ ኢሳይያስ እና "አሥራ ሁለቱ ትናንሽ ነቢያት" ናቸው። አሥራ ሁለቱ አንዳንድ ጌዜ "ትናንሽ ነቢያት" በመባል ይታወቃሉ እነዚህም (ትንቢተ ሆሴዕ፣ ትንቢተ ኢዩኤል፣ ትንቢተ አሞጽ፣ ትንቢተ አብዲዩ፣ ትንቢተ ዮናስ፣ ትንቢተ ሚኪያስ፣ ትንቢተ ናሆም፣ ትንቢተ ዕንባቆም፣ ትንቢተ ሶፎንያስ፣ ትንቢተ ሐጌ፣ ትንቢተ ዘካሪያስ፣ እና ትንቢተ ሚልክያስ) ናቸው። እነዚህም መጻሕፍት

ስለ ክርስቶስ እና ስለ ወንጌል ክስተት ይናገራሉ (**የሐዋሪያት ሥራ 3፡17–26** እና 1 **ጴጥሮስ 1፡10–12** ይመልከቱ)።

ጽሑፎች በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሦስተኛው የመጽሕፍት ስብስብ ሲሆኑ፤ በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉት መጽሐፍት የተደረደሩበት ትክክለኛ ቅደም ተከተል በተለያዩ ጥንታዊ ዝርዝሮች ውስጥ የተለያየ ነው። ይሁን እንጂ በጣም ጥንታዊ የሚባለው ዝርዝር በሚከተለው መንገድ አዘጋጅቶታል፡- መጽሐፈ ሩት፣ መዝሙረ ዳዊት፣ መጽሐፈ ኢዮብ፣ መጸሐፈ ምሳሌ፣ መጽሐፈ መክብብ፣ መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን፣ ሰቆቃው ኤርሚያስ፣ ትንቢተ ዳናኤል፣ መጽሐፈ አስቴር፣ መጽሐፈ ዕዝራና መጸሐፍ ነህምያ፣ (ዕዝራና ነህምያ በመጀመሪያ እንደ አንድ መጽሐፍ ነበር) እና መጽሐፈ ዜና መዋዕል ( መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊና መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ በመጀመሪያ እንደ አንድ መጽሐፍ ነበር)። እነዚህም መጻሕፍት፣ ልክ እንደ ሕግ እና ነቢያት ሁሉ ስለ ክርስቶስ እና ስለ ወንጌል ክስተት ይናግራሉ (እንደገና **1 ጴጥሮስ 1፡ 10–12** ይመልከቱ)።





## 2. ጽሑፎች የተድረደሩት እንዴት ነው?


ጽሑፎች ከነቢያት ቀጥሎ ነው የተደረደሩት፤ ይህ ማለት የጽሑፎች የመጀመሪያ መጽሐፍ የሆነው (መጽሐፈ ሩት) ከነቢያ መጨረሻ የሆነው ከትንቢተ ሚልክያስ ቀጥሎ ይገኛል ማለት ነው።


በጽሑፎች ውስጥ የሚገኙት መጻሕፍት በተለያዩ ጥንታዊ ዝርዝሮች ውስጥ በተለያየ መንገድ ተደርድረዋል። ይሁን እንጂ በጣም ጥንታዊ የሚባለው ዝርዝር በሚከተለው መንገድ አዘጋጅቶታል፦ መጽሐፈ ሩት፣ መዝሙረ ዳዊት፣ መጽሐፈ ኢዮብ፣ መጸሐፈ ምሳሌ፣ መጽሐፈ መክብብ፣ መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን፣ ሰቆቃው ኤርሚያስ፣ ትንቢተ ዳናኤል፣ መጽሐፈ አስቴር፣ መጽሐፈ ዕዝራና መጽሐፍ ነህምያ፣ (ዕዝራና ነህምያ በመጀመሪያ እንደ አንድ መጽሐፍ ነበር) እና መጽሐፈ ዜና መዋዕል ( መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊና መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ በመጀመሪያ እንደ አንድ መጽሐፍ ነበር)።

በጽሑፎች ውስጥ ያሉትን መጽሐፍት በሁለት ክፍል ሊከፈሉ ይችላሉ፤ በመጀምሪያ የግጥም መጽሐፍት እነዚህም አንድ ቦታ ላይ የተቀመጡ ናቸው፤ ሁለተኛ የትረካ መጽሐፈት በመባል የሚታወቁት ሲሆን እነዚህም አንድ ላይ ተደርድረው ይገኛሉ። የግጥም መጻሕፈት ስድስት ናቸው፤ እነዚህም፦ መዝሙረ ዳዊት፣ መጽሐፈ ኢዮብ፣ መጸሐፈ ምሳሌ፣ መጽሐፈ መክብብ፣ መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን እና ሰቆቃው ኤርሚያስ ናቸው። እንደዚሁም የትረካ መጻሕፍት በመባል የሚታወቁ አራት መጻሕፍት አሉ፤ እነዚህም፦ ትንቢተ ዳናኤል፣ መጽሐፈ አስቴር፣ መጽሐፈ ዕዝራና ነህምያ እና መጽሐፈ ዜና መዋዕል ናቸው። ከጽሑፎች ውስጥ ያለ ቦታው የተቀመጠ የሚመስለው ብቸውኛው መጽሐፍ መጽሐፈ ሩት ነው። መጸሐፈ ሩት የትረካ መጽሐፍ ነው፤ ይሁን እንጂ ከትረካ መጽሕፍት ጋር አልተድረደረም። ይልቁንም የተቀመጠው ከግጥም መጻሕፍት በፊት ነው። መጽሐፈ ሩት በጽሑፎች ውስጥ የመጀመሪያ መጽሐፍ ነው። ይህ ለየት ያለ መጽሐፍ መጀመሪያ ላይ የሚታየው ለምንድን ነው? መጽሐፈ ሩት መጀመሪያ ላይ የተደረገው ምናልባት አጠቃላይ ብሉይ ኪዳንን የመጨረሻው ቅርጽ እንዲይዝ ያዘጋጀው አርታኢ (አርታኢዎች) መጽሐፈ ሩትን የጽሑፎች መግቢያ እንደሆነ ተገንዝቦ ሊሆን ይችላል።

በጽሑፎች ውስጥ የመጨረሻው መጽሐፈ ዜና መዋዕል ነው። ነገር ግን በጽሑፎች ውስጥ ካለው የመጨረሻው መጽሐፍ በላይ ነው። ይህም ማለት ጽሑፎች በብሉይ ኪዳን ውስጥ የመጨረሻው የመጻሕፍት ስብስብ ሲሆን፤ ዜና መዋዕል ደግሞ የብሉይ ኪዳን የመጨረሻው መጽሐፍ ነው። ዜና መዋዕል መጨረሻ የሆነበትም ምክንያት ብሉይ ኪዳንን የመጨረሻውን ቅርጽ እንዲይዝ ያዘጋጀው አርታኢ ዜና መዋዕል ለብሉይ ኪዳን መጨረሻ መጽሐፍ እንዲሆን ፍጹም ተስማሚ እንደሆነ ተገንዝቦ ሊሆን ይችላል።

ደግሞም ዜና መዋዕል የብሉይ ኪዳን ፍጻሜ ከመሆን ያለፈ ነገር ያደርጋል፤ ይህም የአዲስ ኪዳን መግቢያ በመሆን ግልጽ በሆነ ሁኔታ ወደ ማቴዎስ መጽሐፍ ያመለክታልና።





### 3. ጽሑፎች ከሕጉ የሚለዩት እንዴት ነው?

ሕጉ የተቀረው የብሉይ ኪዳን እና የመላው መጽሕፍ ቅዱስ መግቢያ ነው። ሕጉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጣም አስፈላጊ የሆነውን ገጸ ባሕሪይ እርሱም እግዚአብሔርን ለአንባቢ ያስተዋወቃል። በተጨማሪም ሕጉ ሰዎችን ለአንባቢ ያስተዋውቃል እንደዚሁም ሰዎች ለምን እንደተፍጥሩም ያብራራል። ሕጉ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረውን ታሪክ ለአንባቢ ያስተዋውቃል። ሕጉ እግዚአብሔር ማን እንደሆነ፣ የእግዚአብሔር ቃል አስፈላጊነት፣ የኃጢአት ችግር እና እግዚአብሔር ለኃጢአት ያዘጋጀው መፍትሔ ለአንባቢ ያስረዳል።

ነገር ግን ጽሑፎች ከላይ ከጠቀስናቸው ውስጥ አንዱንም አያደርጉም። **የመግቢያ ጽሑፎች አይደሉምና**፤ ለምሳሌ አንባቢውን ከእግዚአብሔር ጋር አያስተዋውቁም፤ ይልቁንም እግዚአብሔርን በመግልጥ እና በሕጉ የተጀመርውን መዳበር ይቀጥላሉ። እንደዚሁም ደግሞ ጽሑፎች ስለ ሰዎች፣ ስለ ኃጢአት ችግር እና እግዚአብሔር ለኃጢአት ችግር ያዘጋጀውን መፍትሔ ለአንባቢ አያስተዋውቁም። ይሁን እንጂ ጽሑፎች ስለ ሰዎች፣ የኃጢአት ችግር እና እግዚአብሔር ለኃጢአት መፍትሔ ያዘጋጀውን በመግልጽ ይቀጥላሉ። እንግዲህ ጽሑፎች በምንም ዓይነት ሁኔታ እንደ መግቢያ አያገለግሉም ማለት ነው። ይልቅስ በተፈጥሮአቸው የመጽሐፍ ቅዱስ መልዕክት **እየዳበረ** የሚሄድ መሆኑን ያሳያሉ።

ጽሑፎች በተፈጥሮዋቸው ሕጉ ላይ በተጀመረው በእግዚአብሔር ቃል **የሚደሰቱ** ናቸው። በሕጉ ውስጥ ውስን ቦታዎች ይህን ደስታ ሲንጸባረቅ ይስተዋላል፣ (ለምሳሌ **ዘጸአት 15** ላይ የሚገኘው የድል ግጥም መመልከት ይቻላል)። ነገር ግን በጽሑፎች ውስጥ እንዲህ ያለውን ደስታ በብዙ ሥፍራ ይገኛል። ለምሳሌ፡- መዝሙራት ስለ በእግዚአብሔር የተቀባው ንጉሥ (ክርስቶስ)፣ የእግዚአብሔር ፍጥርት፣ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን አሳቢነት፣ የእግዚአብሔር ቃል፣ የእግዚአብሔር የጽድቅ ባሕሪይ፣ የእግዚአብሔር ፍጹም ፍርድ እና ስለ የእግዚአብሔር ረዳትነት በማውሳት የሚደሰቱ ናቸው። እነዚህ የጠቀስናቸው ጉዳዮች በሕጉ ውስጥ ተጠቅሰዋል። ነገር ግን  በተለየ ሁኔታ በጽሑፎች ውስጥ በደስታ ሲገለጹ ይስተዋላል። መጽሐፈ ምሳሌ ስለ ጥበብ፣ ከእግዚአብሔር የምትገኝን ሚስት እና የመሳሰሉት ርዕሰ ጉዳዮች በማውሳት የሚደስት መጽሐፍ ነው። በዚህ መልኩ ስንመልከተው በዘፍጥርት 2 ላይ የተነሳው አንዱ ርዕስ ወይም ስለ ሚስት ጉዳይ በማንሳት የሚናገር ነው። መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን ደግሞ የጋብቻና የመተሳሰብ ደስታን የሚገልጥ ነው። እነዚህ ጭብጦች በዘፍጥረት 2 ከተጠቀሱት በላይ በመኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን ውስጥ ከመግቢያ በዘለለ መልኩ ተብራርተዋልና።

በሕጉ እና በጽሑፎች መካከል ያለው ትልቁ ልዩነት በሕጉ ውስጥ ያሉት መጻሕፍት በጽሑፍ ውስጥ ካሉት መጻሕፍቶች ውስጥ አንዳቸውንም አለመጥቀሳቸውን ነው። እንደዚሁም በሕጉ ውስጥ ያሉት መጽሐፍት በጽሑፎች ውስጥ ካሉት መጻሕፍት ምንም ጥቅስ አለመጠቀማቸው ነው። ይህም ማለት በሕጉ ውስጥ ያሉትን መጻሕፍት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከጽሑፎች ውስጥ ማንኛውንም መጻሐፍ ወይም ጥቅስ አይጠቅሱም ማለት ነው።

ነገር ግን በጽሑፎች ውስጥ ያሉት መጻሕፍት ከሕጉ ጥቅሶችን ወይም የተወሰኑት ክፍሎች በተደጋጋሚ ይጠቅሳሉ። እንደዚሁም በጽሑፎች ውስጥ ያሉ ደራሲዎች በሕጉ ውስጥ የሚገኙትን ነገሮች ደጋግመው ይጠቅሳሉ።

ሕጉን በተደጋጋሚ ከመጠቀማቸው የተነሳ በጽሑፎች ውስጥ ያሉ የመጻሕፍቱ አዘጋጆች አንባቢዎቻቸውን ሕጉን በተዘዋዋሪ አንብበውታል ብለው እንደ ሚገምቱ ግልጽ ነው። በጽሑፎች ውስጥ ያሉት ብዙዎቹ ግጥሞችና ታሪኮች ትርጉም የሚሰጡት አንባቢ ሕጉን አስቀድሞ ካነበበ ብቻ ነው።

ምናልባት ሕጉ በጣም ጥልቅ ከሆነ የውኃ ጉድጓድ ጋር ማነጻጸር ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ጽሑፎች (እናም ሁሉም የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች) በየጊዜው ወደዚህ ጉድጓድ (ማለትም ወደ ሕጉ) በመጓዝ ከዚህ ጉድጓድ ውኃ ይቀዳሉ። ነገር ግን ሕጉ ውኃን ከጽሑፎች (ወይም ከሌሎቹ) የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች) ፈጽሞ አይቀዳም።

ደግሞም ጥላ እንደ ሌላ ምስሌ ልንወስደው እንችላለን። ሕጉ በጽሑፎች ላይ (እና በተቀረው የመጽሕፍ ቅዱስ ክፍል ላይ) ትልቅ ጥላ ያጠላል። ስለዚህ ሰባኪ ወይም አስተማሪ የሕጉን መልዕክት እንደሚገባ መረዳት አለበት ማለት ነው። ሰባኪ ወይም አስተማሪ እንደሚገባ የሕጉን መልዕክት ካልተረዳ በጽሑፎች ያለውን የሕጉ ጥላ ሊገልጽ አይችልምና።

በሕጉ እና በጽሑፎች ማካከል ያለው ሌላው ትልቁ ልዩነት የእግዚአብሔር ሕዝብ ያለበት ቦታ ሲሆን፤ ይህም ትኩረት ተችሮታል። ሕጉ የሚያበቃው እሥራኤላውያን ወደ ተስፋይቱ ምድር ሊገቡ ሲሉ ነው። ሕዝቡ **በስደት** እንደነበር የሚታውቅ ነው። ሙሴም ደግሞ ሕዝቡ ባለመታዘዙ ምክንያት በተስፋይቱ ምድር ላይ ብዙ እንደማይቆዩ አስጠንቅቆዋቸዋል። በእርግጥ ጣዖታትን እንደሚያመልኩና በዚሁ ምክንያት ከምድሪቱ እንደሚባረሩ ተነግሮዋቸዋል (**ዘዳግም 4፡25–31** ይመልከቱ)።


ከተስፋይቱ ምድር መሰደድ የተፈጸመው በነቢያት ዘመን በነቢያትም በተነገረው መሠረት ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር በዘዳግም 4 ላይ የገባው ቃል ኪዳን ስለ ስደት ብቻ አልነበረም። እንደዚሁም ሕዝቡን መልሶ ወደ ሰጣቸው የተስፋዪቱ ምድር እንደሚመልስም ጭምር ቃል ገብቶ ነበር። ይህ መመለስ


**የሁለተኛው ዘጸአት** በተመለከተ እንደ ማጣቀሻ ነው። ስለዚህ በጽሑፎች ውስጥ ያሉት ሰዎች በአብዛኛው ያንን የሁለተኛ ዘጸአት እየጠበቁ ነበር። ገና የመጨረሻ ማረፊያቸው ወደሆነው ሥፍራ አልደረሱም ነበርና። በግዞት ምድር ነበሩና (ለምሳሌ አስቴርና ዳናኤል እንኳ እግዚአብሔር ወደ አዘጋጀላቸው ሥፍራ ለመመለስ እየታገሉ ነበር፤ እንደዚሁም እዝራና ነህምያ)። ብዙዎች መጽሐፍት በመከራ ጊዜ በጽድቅ ስለ መኖር ያስተምራሉ (ለምሳሌ ኢዮብ እና ሰቆቃው ኤርምያስ) መመልከት ይቻላል። ስለዚህ ጽሑፎች ሙሉ በሙሉ ወደ ቦታቸው ለመመልስ ለሚጠባበቁ የእግዚአብሔር ሰዎች የሚመለከት ነው።

የጽሑፎች ክፍል የሚያበቃው እሥራኤል ከረጅም ግዞት በኋላ እደገና ወደ ተስፋይቱ ምድር መግባታቸውን በመናገር ነው። ነገር ግን የእግዚአብሔር ሰዎች እንደገና ወደ ተስፋይቱ ምድር ቢገቡም እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባውን ቃል ኪዳን እንዳልተፈጸመ ግልጽ ነው (**ዘፍጥረት 12፡1–3** ይመልከቱ)። የሁለተኛው ቤተመቅደስ ክብር ከመጀመሪያው ቤተ መቅደስ ክብር ያነሰ ነበር። የሁለተኛው አነስ ያለ ነበር። እንደዚሁም ሕዝቡም ታዛዥ አልነበረም። በዕዝራና በነህሚያ በግልጽ እንደተናገረው ሕዝቡ አሁንም አይታዘዙም ነበር። ልባቸው ገና "አልተገረዘም" ነበርና (**ዘዳግም 30፡6** ይመልከቱ)። ስለዚህ የጽሑፎች ክፍል የሚያበቃው አንባቢው የእግዚአብሔር እውነተኛ ማደሪያ እስኪቋቋም ድረስ እና የእግዚአብሔር ሕዝብ በታዛዥነት መመላለስ እንዲጀምር በመጠባባቅ ነው።

> *የሰማይ አምላክ እግዚአብሔር የምድርን መንግሥታት ሁሉ ሰጥቶኛል፤ በይሁዳም ባለችው በኢየሩሳሌም ቤት እሠራለት ዘንድ አዞኛል፤ ከሕዝቡም ሁሉ በእናንተ ዘንድ ማንም ቢሆን አምላኩ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ይሁን እርሱም ይውጣ ብሎ በመንግሥቱ ሁሉ አዋጅ አስነገረ፤ ደግሞም በጽሕፈት ኢድረገው* (**2 ዜና 36፡23**)።

ዜና መዋዕል የሚያበቃው ቤተ መቅደሱ እንዲሠራ ትእዛዝ በመስጠት ነው። የንጉሥ የቂሮስን ቃል የሚፈጽም ማነው? ወጥቶስ የእግዚአብሔርን ቤት (መቅደሱን) የሚሠራ ማነው? በመጨረሻም የቂሮስ ቃል የተፈጽመው በኢየሱስ በኩል ነው። ለእግዚአብሔር "ቤት"ን የሚሠራው እርሱ ኢየሱስ ነው (**ዮሐንስ 2፡18–22** እና **ኤፌሶን 2፡19–22** ይመልከቱ)። የፊተኛው አዳም ያልቻለውን ያደርገው እርሱ ነውና። የእግዚአብሔርን ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር በመመለስ ወደ አምልኮ የሚመራቸውም እርሱ ኢየሱስ ነው።





## 4. ጽሑፎች ከነቢያት ጋር በምን ይመሳሰላሉ?

ነቢያት እና ጽሑፎች እርስ በርሳቸው በብዙ መንገዶች ይመሳሰላሉ። ከእነዚህም መንገዶች አንዳንዶቹ ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

በመጀመሪያ፤ ሁለቱም ክፍሎች እንደ ሁሉም ቅዱሳት መጽሐፍት ስለ ክርስቶስና ስለወንጌል ክስተት ይናገራሉ (**ሉቃስ 24፥25–27፣ 24፥44–47** እና **1 ጴጥሮስ 1፥10–12** ይመልከቱ)።


ሁለተኛ፤ ሁለቱም ክፍሎች የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበትን ቃል አካል ናቸው፤ ስለዚህ በውስጣቸው የተጻፈውም ሁሉ ይፈጸማል (**ዮሐንስ 10፥35** ይመልከቱ)።


ሦስተኛ፤ ሁለቱም ክፍሎች ቤተክርስቲያን  እንድትጠቀምባቸው የታሰቡ ናቸው። ነቢያትም ሆኑ ጽሑፎች “የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ለትመህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማሉ” (**2ኛ ጢሞቴዎስ 3፥16**)። እነዚህ የብሉይ ኪዳን ክፍሎች የእግዚአብሔር ስጦታዎች ናቸው፤ ስለዚህ የእግዚአብብሔር ሕዝብ ወንዶችም ሴቶችም ወደ ብስለት እንዲያድጉ ቤተክርስቲያን እንደትጠቀምባቸው የታቀዱ ናቸው (**2 ጢሞቴዎስ 3፥17** ይመልከቱ)።

አራተኛ፤ ከነቢያት እና ከጽሑፎች የተወጣጡ ክፍሎች በአዲስ ኪዳን ውስጥ በተደጋጋሚ ተጠቅሰዋል። እንደዚሁም ኢየሱስና ሐዋሪያትም ከሁለቱ ክፍሎች የተወጣጡ ክፍሎችን ተጠቅመዋል። በመሠረቱ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በብዛት የተጠቀሰ ወይም ጥቅም ላይ የዋለው የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ መዝሙረ ዳዊት ነው። መዝሙረ ዳዊት ደግሞ ከጽሑፎች ውስጥ ይመደባል። ሌላው በአዲስ ኪዳን ውስጥ በብዛት የተጠቀሰው ወይም ጥቅም ላይ የዋለው የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ትንቢተ ኢሳይያስ ነው። ትንቢተ ኢሳይያስ ደግሞ ከነቢያት ውስጥ ይመደባል።

አምስተኛ፤ ነቢያት እና ጽሑፎች ማለትም ሁለቱም የትረካ መጻሕፍትን እና የግጥም መጻሕፍት ያካትታሉ። በነቢያትም ሆነ በጽሑፎች ውስጥ የትረካ መጻሕፍቶች አንድ መደዳ እንደዚሁም የግጥም መጻሕፍቶችም አንድ መደዳ ተደርድረዋል። በነቢያት ውስጥ ያሉት የትረካ መጻሕፍት ኢያሱ፣ መሳፍንት፣ ሳሙኤል እና ነገሥት ናቸው። በጽሑፎች ውስጥ ያሉት የትረካ መጻሕፍት ዳንኤል፣ አስቴር፣ ዕዝራና ነህሚያ እና ዜና መዋዕል ናቸው። በነቢያት ውስጥ ያሉት የግጥም መጻሕፍት፣ ኤርሚያስ፣ ሕዝቅኤል፣

ኢሳይያስ እና አሥራ ሁለቱ ናቸው። በግጥም መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙት ደግሞ ኢዮብ፣ ምሳሌ፣ መክብብ፣ መኃልየ ዘሰሎሞን እና ሰቆቃው ኤርምያስ ናቸው።





## 5. ጽሑፎች ከነቢያት የሚለዩት በምንድን ነው?

በጽሑፎች እና በነቢያት መካከል ብዙ መመሳሰሎች ቢኖሩም፤ ብዙ ጠቃሚ ልዩነቶች ደግሞ አሉ። ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ጥቂቶቹ በጽሑፎች እና በነቢያት መካከል ያሉ ልዩነቶች ናቸው።

በመጀመሪያ በብሉይ ኪዳን ቀኖና **ምደባ** ውስጥ የተለያዩ ናቸው (ቀኖና የሚለው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተቀባይነት ያላቸውን የመጻሕፍት ዝርዝር ለመግለጽ የሚያገለግል ቃል ነው)። ነቢያት በብሉይ ኪዳን ውስጥ መካከለኛ ክፍል ላይና ደግሞም ከጽሑፎች በፊት ይገኛሉ። ብሉይ ኪዳንን ያዘጋጀው አርታኢ(ዎች) የነቢያትን መልዕክት ከጽሑፎች መልዕክት እንዲቀድም የፈለገ ይመስላል። በሌላ አነጋገር ጽሑፎችን ከማንበብ በፊት የነቢያትን መልዕክት ማንበብ ጠቃሚ እንደሆነ ያመለክታል። ነገር ግን ይህ ማለት ጽሑፎች በራሳቸው ሊነበቡ አይችሉም ማለት ደግሞ አይደለም። ለማለት የተፈለገው በመጀመሪያ ነቢያትን ማንበብ ትልቅ ጥቅም አለው ለማለት ነው። የነቢያት መልዕክት ቅድሚያ ማንበብ ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት በጽሑፎች ውስጥ ለሚገኘው መልዕክት አውዱ ምን እንደሚመስል ስለሚያሳይ ነው።

ለምሳሌ፡- አንድ ሰው ሁሉንም ነቢያት ከማንበቡ በፊት መዝሙረ ዳዊትን ካነበበ (ማለትም ኤርምያስን፣ ሕዝቅኤልን፣ ኢሳይያስንና አሥራ ሁለቱን ጨምሮ) አንባቢው ንጉሥ ዳዊትን የመዝሙረ ዳዊት ዋና ገፀ ባህሪ እንደሆነ የበለጠ ትኩረት ሊሰጥ ይችላል። ስለዚህ መዝሙረ ዳዊት "ስለ ዳዊት" ብቻ የሚናገር ነው ብሎ ሊያስብ ይችላል። ይልቅስ አንድ ሰው ሁሉንም ነቢያት ካነበበ በኋላ  መዝሙረ ዳዊት ሲያነብ (ኤርምያስ፣ ሕዝቅኤል፣ ኢሳይያስ እና አሥራ ሁለቱ ጨምሮ) ንጉሥ ዳዊት የመዝሙረ ዳዊት ዋና ገፀ ባህሪ አድርጎ ላይመለከት ይችላል። እንዳውም መጻሕፍት ወደ ኋላ ወደ ዳዊት የሚያመለክቱ እንዳልሆኑ አንባቢው ይገነዘባል። በተቃራኒው ወደ ፊት በመመልከት የዳዊት ወራሽ የሆነው ክርስቶስን በጉጉት የሚጠብቁ መሆናቸውን ይርዳል ማለት ነው! ሁሉንም ነቢያት ካነበበ በኋላ መዝሙረ ዳዊትን የሚያነብ አንድ ሰው ክርስቶስን የመዝሙረ ዳዊት ዋና ገፀ ባህሪ አድርጎ የመመልከ እድሉ ሰፊ ነው። ትክክለኛው የመዝሙረ ዳዊት ንባብ ደግሞ ይህ ነው። መዝሙሮቹም የሚያወሱት ስለዚህ ጉዳይ ነውና።

ጽሑፎች የብሉይ ኪዳን መደምደሚያ መሆናቸውን ልብ ማለት ያስፈልጋል። ይህም ሆን ተብሎ የተደረገ ነው። ለአዲስ ኪዳን እንደ ተስፋ ሆነው የሚያገለግሉት እነሱ እንጂ ነቢያት አይደሉምና። በዜና መዋዕል ውስጥ ያሉትን የመጨረሻዎቹ ቃላት አንባቢው እውነተኛን ቤተ መቅደስ የሚሠራውን ሰው እንዲጠብቅ ያደርገዋል። ያም ሰው መጣ፤ ስሙም ኢየሱስ ነው።

ሁለተኛ በመልዕክታቸው **ይዘትም** ይለያሉ። ነብያት ስለማይታዘዙ ሰዎች እየተናገሩ ስለሆነ የበለጠ አሉታዊ ናቸው። ጽሑፎች ደግሞ ስለ ሚታዘዙ ሰዎች ስለሚናገሩ የበለጠ አዎንታዊ ናቸው።

ይህ ማለት ነቢያቶች አሉታዊ ክፍሎች ብቻ አሏቸው ማለት አይደለም። ጉዳዩ ይህ አይደለምና። ነቢያት ስለ ክርስቶስ ክብር፣ ስለ መንግስቱ እና የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር ሥፍራ መመለስን የሚናገሩ ብዙ የሚያምሩ ክፍሎችን ይዘዋል። በነቢያት የተነገሩ ብዙ እግዚአብሔርን የሚከትሉ አሉ። ይሁን እንጂ የነብያቱ አጠቃላይ ቃና አሉታዊ ነው።

ይህ ማለት ደግሞ ጽሑፎች ሙሉ ለሙሉ አዎንታዊ ናቸው ማለት አይደለም። ሰዎች እግዚአብሔርን እንደ ማይታዘዙ የተገለጸባቸው ብዙ ክፍሎች አሉ። ይሁን እንጂ የጽሑፎች አጠቃላይ ቃና ግን አዎንታዊ ነው።

ሦስተኛ መለዕክቶቹ በተነገሩበት **ቦታ** ይለያያሉ፤ ነቢያት በአብዛኛው በተስፍይቱ ምድር ይኖሩ በነበረበት ወቅት ስለ እግዚአብሔር ሰዎች በተነገሩ ታሪኮች የተሞሉ ናቸው። እነዚህ መጻሕፍቶች እሥራኤል በጣዖት አምልኮ ምክንያት ከምድሪቱ የተባረሩበት ወደ አሳዛኝ ክስተት  የሚወስደውን ጊዜ ይገልጻል (**ዘዳግም 4፡15–16 እና 29፡16–28** ይመልከቱ)። ብዙዎቹ የመጻሕፍቶች መጻሕፍት የሚያተኩሩት በስደት በሚኖሩ እና እግዚአብሔር መልካም ወደ ሆነው ቦታ እንዲመልሳቸው ሲጠባበቁ ከእግዚብሔር መልካም ቦታ ውጪ በእምነት እንዲኖሩ በሚገደዱ ሰዎች ላይ ነው (**ዘዳግም 4፡27–31 እና 30፡1–10** ይመልከቱ)።

አራተኛ **በዓላማ** ይለያሉ። ነቢያት በአብዛኛው የእሥራኤል ታሪክ እሥራኤል በኃጢአት እየተመላለሰች በነበረችበት ወቅት የተናገሩት ነው። የነቢያት መልዕክት ብዙ የንስኃ ጥሪዎችን አካትተዋል። ጽሑፎች በግዞት ስለነበሩት የእግዚአብሔር ሕዝቦች ታሪክ የሚናገሩ ናቸው። ደግሞ አብዛኛው የጽሑፎች ክፍል የንስሐ ጥሪ አይደሉም። ይልቁንም እንዲጸኑና በእግዚአብሔርም ተስፋ እንዲታመኑ ለፍጻሜም እንዲጠበቁ የተደረገ ጥሪ ነው እንጂ።

በጽሑፎች ውስጥ የሚገኙት የግጥም መጽሐፍት (መዝሙረ ዳዊት፣ ኢዮብ፣ ምሳሌ፣ መክብብ፣ መኃልየ መኃልየ ዘሰሎሞን እና ሰቆቃው ኤርምያስ) እግዚአብሔር የገባቸውን ተስፋዎች ፍጻሜ ከማግኘታቸው ክቡር ቀን በፊት ሰዎች በታማኝነት እንዲኖሩ ለመርዳት ታስቦ የተዘጋጁ ይመስላል። እነዚህ ግጥሞች በሁሉም የሕይወት ዘርፎች ለእግዚአብሔር ሕዝብ ታላቅ አስተዋጽዖ ያበረክታሉ። ለምሳሌ በጽሑፎች ውስጥ የሚገኙት መጻሕፍት ከፍተኛ መከራ በደረሰባቸው ጊዜያት (ኢዮብ፣ መዝሙረ ዳዊት፣ ምሳሌ፣ መክብብ፣ ሰቆቃው ኤርምያስ) ታላቅ ማበረታቻ ይሰጣሉ። ደግሞም የግጥም ምጻሕፍት በትዳር


ላይ ላሉት ለእግዚአብሔር ሕዝቦች (በተለይም መጽሐፈ ምሳሌና መኃልየ መኃልይ) መመሪያ ይሰጣሉ። ብዙውን ጊዜ ግራ በሚያጋባው በዚህ ዓለም ውስጥ ሰዎች በጥበብ እንዲኖሩ (መጽሐፈ ምሳሌና መጽሐፈ ምክብብ) እርዳታ ይሰጣሉ።


የግጥም መጽሐፍት **በነበሩበት ጌዜ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ከነገሠው ንጉሥ ጋር በተያያዘ የተለየ ነበሩ።** በነቢያት ዘመን የነበሩት ሰዎች በነቢያት የተነገሩት አብዛኛውን ጊዜ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ወደ ታዣዥነት ይመራል ተብሎ በሚገመተው ንጉሥ ሥር ይተዳደሩ ነበር። ከእነዚህ ነገሥታት መካከል አንዳንዶቹ ለያህዌ (ለእግዚአብሔር) ታዛዥ ነበሩ። ነገር ግን ከእነዚህ ነገሥታት አባዛኞቹ ታዛዦች አልነበሩም።

እንደዚሁም በጽሑፎች ውስጥ በሚገኙት የትረካ መጻሕፍት ውስጥ የተገለጹት ዋና ገፀ-ባሕሪያት የይሁዳ ወይም የእሥራኤል የሆነ ንጉሥ ነግሦ አይታይም። በአንዳንዶች በጽሑፎች ውስጥ የሚገኙ ሰዎች በአሕዛብ ነገሥታት አስተዳደር ውስጥ ሆነው እንመለከታለን (ለምሳሌ፡- ዳንኤል፣ የዳንኤል ሦስቱ ወዳጆቹ፣ መርዶኪዮስ፣ አስቴር፣ ዕዝራ እና ነህምያ)። ይሁን እንጂ እነዚህ ሰዎችም ቢሆኑ ልክ እንደ ሁሉም የእግዚአብሔር ሕዝቦች በእግዚአብሔር የተቀባ ንጉሥ ማለትም ክርስቶስን ይጠባበቁ ነበር። በዚህ ዘመን ያሉ አማኞች በእግዚአብሔር የተቀባ ንጉሥ እስኪመጣ እየጠበቁ አይደለም። ንጉሡ መጥቷልና። ስሙም ኢየሱስ ነው፤ ስልጣንም ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጥቶታል (**ማቴዎስ 28፡18–20** ይመልከቱ)። ኢየሱስ አሁን በኃይል የእግዚአብሔር ልጅ ነው (**ሮሜ 1፡4**)።

ስለዚህ ዛሬ ያሉት የእግዚአብሔር ሕዝቦች በነቢያት ዘመን ከተገለጹት የአምላክ ሕዝቦች የተለዩ ናቸው። ደግሞም በጽሑፎች ዘመንም ከተገለጹት የእግዚአብሔር ሰዎችም የተለዩ ናቸው። በአሁኑ ጊዜ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ታዛዥ ንጉሥ በእነርሱ ላይ እየገዛ ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ ለንጉሡ ሥልጣን እስኪሰጠውም እየጠበቁም አይደሉም። በሰማይና በምድር ያለውን ሥልጣን ሁሉ  ተሰጥቶታልና።

ሆኖም ልክ በጽሑፎች ውስጥ እንደነበሩቱ በዚህ ዘመንም ያሉውን የእግዚአብሔር ሕዝብ አሁንም እየጠበቀ ነው። እየጠበቁትም ያለው ንጉሣቸው የሆነውን ኢየሱስ ዳግም እስኪመጣ ነው። እስከዚያም ቀን ድረስ የእግዚአብሔር ሕዝብ በመከራ ያልፋል ማለት ነው።





## 6. በጽሑፎች ውስጥ የተገለጹት ሰዎች በእምነት ተለይተው ይታወቃሉ

ነቢያት እና ጽሑፎች በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ በተገለጹት የትረካ ክፍሎች **ከተገለጹት ሰዎች ባሕሪ** አንፃር የተለያዩ ናቸው። በነብያት ውስጥ በእርግጥ ታማኝ ሰዎች ቢኖሩም፣ በከፊል በመታዘዝ ወይም በፍጹም አለመታዘዝ የሚሄዱ ብዙ ብዙ ሰዎች ደግሞ አሉ። የነቢያቱ ደራሲዎች ታዛዥ የሆኑትን የያህዌ (እግዚአብሔር) ተከታዮችን ጉድለቶች በጥንቃቄ ይገልጻሉ። ለምሳሌ የዳዊት ታማኝነትና ታማኝነት የጎደለውን ድርጊቱን እንዴት እንደተገለጸ ይመልከቱ።

በጽሑፎች ውስጥ ያሉት ዋና ገፀ-ባሕሪያት በሌላ በኩል በቋሚነት ታማኝ ሆነው ተገልጸዋል። እንደዚሁም በጽሑፎች ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና ገፀ-ባሕሪያት እንዴት እንደሚገለጹ በጥንቃቄ ያስተውሉ። በጽሑፎች ውስጥ ዋና ገፀ-ባሕሪያት ኑኃሚን፣ ሩት፣ ቦዔዝ፣ ኢዮብ፣ ዳንኤልና ሦስቱ ጓደኞቹ፣ መርዶኪዮስ፣ አስቴር፣ ዕዝራ እና ነህሚያ ናቸው። እነዚህ ገፀ-ባሕሪያት እንደ ታማኝ እና ታዛዥ ተደርገው ተገልጸዋል። በእነዚህ ሰዎች ውስጥ ሙሉ መታዘዝ እንጂ በከፊል መታዘዝ አይታይም። ስለዚህም የያህዌ (የእግዚአብሔር) ታማኝ ተከታዮች ተደርገው ተቆጥረዋል።

በእርግጥም በጽሑፎች ውስጥ ከተገለጹት አንዱ ዓላማ በዚህ ዘመን ለሚኖሩ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ሊከተሉዋቸው ስለሚገቡ ታማኝ ምሳሌዎችን ማቅረብ ነው። እነዚህ መጻሕፍት ወጣት ወንዶች (ዳንኤልና ሦስቱ ጓደኞቹ)፣ ወጣት ሴቶች (ሩትና አስቴር)፣ ሽማግሌዎች (ቦዔዝ፣ኢዮብ፣ መርዶኪዮስ፣ ዳንኤል፣ የዳንኤል ሦስቱ ጓደኞች፣ ዕዝራና ነህሚያ) እና አሮጊት ሴቶች (ኑኃሚን) በታላቅ መከራም ጊዜ ቢሆን በእምነት ስለመኖር እንዴት እንደሆነ ያሳያሉ።



## 7. በጽሑፎች ውስጥ የሚነገረው ታሪክ ምንድር ነው?

በጽሑፎች ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር ሕዝብ ታሪክ በብዙ መልኩ በነቢያት ውስጥ ካለው የእግዚአብሔር ሕዘብ ታሪክ ተቃራኒ ነው።

በነቢያት የተነገረውን አሳዛኝ ታሪክ እነሆ፡-

የሙሴ መጽሐፍ የሚያበቃው እሥራኤላውያን ወደ ተስፍይቱ ምድር ለመገባት ትንሽ ሲቀራቸው ነው። ምናልባት አንባቢው የእሥራኤል ሕዝብ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ እንደሚመላለሱ ተስፋ ያድረግ ይሆናል። ይሁን እንጂ የሙሴን መጽሐፍ በቅርበት ማንበብ አንባቢው እሥራኤላውያን ያሳለፉትን የሐሰት አምልኮና የዓመጸኝነት ታሪክ እንዲገነዘብ ያዘጋጀዋል። ሙሴም እሥራኤላውያን እንደማይታዘዙ እና በምድሪቱም እንደማይቆዩ ተንብዮ ነበር (**ዘዳግም 4፡15–28 ይመልከቱ**)። አንባቢ ነቢያትን በሚያነብበት ጊዜ እሱ ወይም እሷ የሙሴ ትንቢት በኢያሱ፣ በመሳፍንት፣ በሳሙኤል እና በነገሥታት ላይ ሲፈጸም መመልከት ይቻላል። ገና ከጅማሬው የእሥራኤል ሕዝብ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ለመራመድ ፈቃደኛ አልነበረም (**ኢያሱ 7** ይመልከቱ)። ምንም እንኳን እግዚአብሔር እሥራኤልን ደጋግሞ ቢያድናቸውም፤ እሥራኤልም ደግሞ ደጋግመው በአለመታዘዝ ይመላለሱ ነበር፤ የሐሰት አማልክቶችንም ያምልኩ ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር እሥራኤልን ወደ ንሰሐ እንዲጠሩ ነቢያትን ላከ። እሥራኤል ግን ለመስማት ፈቃደኛ አልሆነችም። በመጨረሻም ልክ ሙሴ ትንቢት እንደተናገረባቸው እሥራኤላውያን ከምድሪቱ ተባረሩ። በተመሳሳይ መንገድ የእግዚአብሔር የመጀመሪያ ልጅ የነበረው (አዳም) ከእግዚአብሔር መልካም ሥፍራ (ከኤደን ገነት) እንደተባረረ የእግዚአብሔር “ልጅ” እሥራኤል እንደ ሕዝብ እግዚአብሔር ባስቀመጠው ቦታ መቆየት አልቻለም ነበር።

ብሉይ ኪዳን ውስጥ እሥራኤል በምሳሌዊ አነጋገር በወይን ግንድ ተመስላለች (**መዝሙር 80፡8–18፣ ኢሳይያስ 5፡17፣ ኤርምያስ 2፡21፣ 5፡10፣ 6፡9 እና 8፡13** ይመልከቱ)። እግዚአብሔርም ከወይን ገበሬ ጋር ተነጻጽሯል። እግዚአብሔር ወይኑን (እሥራኤልን) ባዘጋጀው ምድር ተከለ (**ኢሳይያስ 5፡2** ይመልከቱ)። ለአጭር ጊዜም ወይኑ ሲያድግ ታየ (1 **ነገሥት 4፡25** ይመልከቱ)። ነገር ግን ወይኑ ሆምጣጣ ፍሬ አፈራ (**ኢሳይያስ 5፡2** እና **ሆሴዕ 10፡1** ይመልከቱ)። በመጨረሻም ወይኑ ከምድሪቱ ተነቀለ ምድሪቱም ባዶዋን ቀረች (**መዝሙር 80፡8–14**)። ይህ የሚያሳዝን ታሪክ የሆነው በእግዚአብሔር መልካም ቦታ ነው። በ

**ማቴዎስ 21፡33–46**፣ **ማርቆስ 12፡1–9**፣ **ሉቃስ 13:6–9** እና **20:9–18** ላይ ያሉትንም የኢየሱስ ምሳሌዎች ይህን አሳዛኝ ታሪክ ለሰዎች ለማስታወስ የታሰቡ ናቸው።


የጽሑፎች ተግባር በብዙ መንገዶች ይህንኑ የወይኑን ታሪክ እንደገና መተረክ ነው። ይሁን እንጂ በዚህ ታሪክ በእግዚአብሔር ሕዝብ አለምታዘዝ እና ፍሬ አልባነት ላይ አያተኩርም። ይልቁንም ትኩረቱ የእግዚአብሔር ሕዝብ ፍሬያማና የሚታዘዝ በመሆን ወደ ቀድሞ እግዚአብሔር ወደ አስቀመጠው ቦታ እንዲመለስ በማድረግ ላይ ነው።

በጽሑፎች ውስጥ መጀመሪያ የሚገኘው መጽሐፈ ሩት ነው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እየተነገረ ያለው ታሪክ ለጽሑፎች ተገቢ መግቢያ ነው። መጽሐፈ ሩት የሚያተኩረው ምድሯን ትታ በባዕ አገር ለመኖር በሄደች እሥራኤላዊት (ኑኃሚን) ላይ ነው። ይህ የባዕድ አገር ለኑኃሚን ፍሬያማ ቦታ አልነበረም። የኑኃሚን ልጆች ባዕድ ሚስቶችን አገቡ፤ ልጆች ደግሞ አልወለዱም ነበር። በመጨረሻም ባልዋና ሁለቱም ልጆችዋ በስደት ላይ እንዳሉ ሞቱ። ሆኖም ኑኃሚን በግዞት ምድር አልሞተችም። ይልቁንም በእግዚአብሔር ቸርነት ወደ እግዚአብሔር መልካም ሥፍራ ተመለሰች። የሩት መጽሐፍ ደግሞ በትዳርና በፍሬያማነት ያበቃል። ኑኃሚን እግዚአብሔር የገባውን ተስፋ አምላካዊ ዘር አየች።ስለዚህ ይህ የጽሑፎች መጀመሪያ የሆነው መጽሐፍ ሌሎች የጽሑፍ መጽሐፎች ለማንበብ አውድ ለአንባቢው ይሰጣል።

እነዚህ መጻሕፍት የተጻፉት ልክ እንደ ኑኃሚን በግዞት ለነበሩ ነገር ግን ወደ እግዚአብሔር መልካም ሥፍራ ለመድረስ በመጓዝ ላይ ለነበሩ ሰዎች ነው። የእግዚአብሔር ሰዎች የመጭረሻ መዳን የሆነውን የእግዚአብሔር መልካም ሥፍራ ሲጠባበቁ መከራን እንዲታገሡ በጽሑፎቹ ላይ አንጻዖት ይሰጣል። ስለዚህ ምንም እንኳን የእግዚአብሔር ሰዎች በግዞት ላይ ቢሆኑም እንኳ እግዚአብሔር ግን ያለማቋረጥ ታማኝነቱንና ማዳኑን ያሳያቸው ነበር (ለምሳሌ፡- ኢዮብ፣ ዳንኤል፣ የዳንኤል ሦስቱ ጓደኞቹ፣ መርዶክዮስ እና አስቴር ይመልከቱ)።

እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሥፍራን አዘጋጅቷል። እኛ እንደ እግዚአብሔር ሕዝቦች ከዚያ ሥፍራ ውጭ ብንኖርም እንኳ ወደዚያ ሥፍራ መናፈቅ አለብን። ይህም ሃሳብ የጽሁፎች ጭብጥ ነው፤ ለምሳሌ በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ ስለመውጣት የሚናገሩት መዝሙሮች ይመልከቱ (**መዝሙር 120–134**)። እነዚህ መዝሙሮች ሁሉ ለአምልኮ ወደ እግዚአብሔር ሥፍራ በሚደርገው ጉዞ የሚደሰቱ ናቸው። በተጨማሪ የሰቆቃው ኤርምያስንም መጽሐፍ ይመልከቱ። እነዚህ ግጥሞች ስለእግዚአብሔር መልካም ሥፍራ ከመናገራቸውም በላይ የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደዚያ መጓጓት እንዳልበት ያሳያሉ። ጽሑፎች ገና ከመጀምሪያው በአዲስ የጅመሬ ዕድል የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር መልካም ሥፍራ የገባበትን ታሪክ ይናገራሉ።

የእግዚአብሔር “የወይኑ ግንድ” ታሪክ በጽሑፎች ውስጥ አያልቅም። እንደዚሁም በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔርን ፍሬያማ ሕዝብ ታሪክ ይቀጥላል። ታሪኩም የሚጀምረው በኢየሱስ ነው። እርሱም እንደ እሥራኤል ከወይን ግንድ ጋር ተመሳስሏል (**ዮሐንስ 15** ይመልከቱ)። ኢየሱስ “እውነተኛ የወይን ግንድ” ነው ከእሥራኤል በተለየ ሁኔታ ኢየሱስ ሁል ጊዜ መልካም ፍሬ ያፈራል (**መዝሙር 1፡3** ይመልከቱ)። በክርስቶስ የሆኑቱ ሁሉ ደግሞ መልካም ፍሬ ያፈራሉ (**ገላትያ 5፡22–23** ይመልከቱ)።



## 8. በጽሑፎች ውስጥ ግጥም የተለመደ መሆኑ ለምንድር ነው?

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘው መልዕክት ብዙውን ጊዜ ለአንባቢው የሚቀርበው በግጥም መልክ ነው። ግጥም ምናልባት ለማንበብ አስጨጋሪ ሊሆን ይችላል፤ ምክንያቱም ተራ ንግግር አይደለም። ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግጥሞችን እንዴት ማንበብ እንደሚቻል መማር ጠቃሚ ነው። ሰባኪም ቢሆን የመጽሐፍ ቅዱስ የግጥም ክፍሎችን እንዴት እንደሚሰብክ መማሩ አስፈላጊ ነው። ግጥም ለአናባቢም ሆነ ለሰባኪ ወይም ለአስተማሪ በጣም ጠቃሚ ነው። ምክንያቱም ልክ እንደ ሙዚቃ ሁሉ ግጥም ወደ ልብ ውስጥ የመድረስና ስሜትን የመቀስቀስ መንገድ አለው።

ከትረካ ቀጥሎ (በታሪክ ንግርት መልክ ጥቅም ላይ የዋለው የጽሑፍ ዓይነት) ቅኔ ወይም ግጥም በብሉይ ኪዳን ውስጥ በጣም የተለመደ የአጻጻፍ ስልት ነው። ደግሞም በጽሑፎች ውስጥ በጣም የተለመደው የአጻጻፍ አይነት ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ቅኔዎች ሳይረዱ ከጽሑፎች በትክክል ለመስበክ በጣም አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ከጽሑፎች ውስጥ መዝሙረ ዳዊት፣ ኢዮብ፣ ምሳሌ፣ መክብብ፣ መኃልየ መኃልይ እና ሰቆቃው ኤርምያስ በእነዚህ ሁሉ ውስጥ ብዙ ግጥሞች ይገኛሉ። ስለዚህ ለሰባኪ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቅኔዎችን ማወቅ፣ መረዳት እና መጠቀም መቻል አስፈላጊ ነገር ነው።

መጽሕፍ ቅዱሳዊ ቅኔ ወይም ግጥም ልዩ የሆኑ ቃላትን እና የቃላት ዘይቤዎችን ስለሚጠቀም አንባቢው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን ግጥሞች በቀላሉ ማወቅ የሚችልበትን መንገዶች መማር ይችላል። በብሉይ ኪዳን የሚገኙት ግጥሞች በአብዛኛው ቤት የሚመቱ ግጥሞች አይደሉም። ይልቁንም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ግጥም ትይዩ በሚባለው የግጥም ቅርጽ ነው የተጻፈው። ትዩዩነት በአንድ መስመር ስለአንድ ነገር የሚናገርበት መዋቅር ሲሆን ከሱ በኋላ ያለው መስመር ደግሞ ወዲያውኑ ሃሀሳቡን ከመጀመሪያው መስመር ይደግማል ደግሞም የተለያዩ ቃላት በመጠቀም የመጀመሪያውን ሀሳብ በተወሰነ መንገድ ያጠነክረዋል።

ስለ ትይዩነት የሚታሰበው ሌላው መንገድ እንደ ገደል ማሚቶ መሆኑን ነው። የሁለተኛው መስመር የመጀመሪያውን መስመር ሀሳብ ያስተጋባልና። በ“መደበኛ” የገደል ማሚቶ ሂደት አንድ ሰው የሆነ ነገር ብሎ ሲጮህ፤ ምላሽ ሰጪው ገደል ማሚቶ በትክክል ተመሳሳይ ቃላትን ያስተጋባል። ይሁን እንጂ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ግጥሞች ግን አስተጋቢው ተመሳሳይ ቃላትን አይጠቀምም። ምንም እንኳን ተመሳሳይነት ቢኖራቸውም ሁለተኛው መስመር ከመጀመሪያው መስመር የተለየ ነው። ብዙን ጊዜ በተወሰነ መንገድ የሁለተኛው መስመር ጠንከር ይላል።

ከመዝሙራት አንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅኔ ወይም ግጥም ምሳሌ የሚከተለውን እንመለከታለን። በዚህ ግጥም ውስጥ ሁለተኛው መስመር በመጀመሪያው መስመር ላይ የተገኙትን ሃሳቦች እንዴት እንደሚደግም ነገር ግን ይህን ለማድረግ ጠንከር ያሉ ቃላትን እንደሚጠቀም ያስተውሉ፡-

*አቤቱ በቁጣህ አትቀስፈኝ፤*

*በመዓትህም አትገስጸኝ!* **መዝሙር 38፡1**

ልክ ሁለት የተጋደሙ የባቡር ሀዲዶች ትይዩ እንደሆኑ ሁሉ፤ በመዝሙር 38፡1 ላይም ያለው ሁለተኛው መስመር ከመጀመሪያው መስመር ጋር ትይዩ ነው። ይህም ጥቅም ላይ በዋሉት ቃላት ውስጥ ይታያል። ቃላቶቹ በግልጽ እርስ በርሳቸው ይመሳሰላሉና። በመጀምሪያው መስመር ላይ ያለው " በቁጣህ አትቀጽፈኝ" የሚለው ቃል በሁለተኛው መስመር ላይ " በመዓትህ አትገሥጸኝ" እንደሚለው ቃል ነው። ነገር ግን "በመዓትህ" የሚለው ቃል "በቁጣህ" ከሚለው ቃል የበለጠ ጠንካራ መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል። ስለዚህ በድጋሚ ማለት የምንፈልገው ሁለቱም የግጥም መሥመሮች እንደ ባቡር ሀዲድ ናቸው፤ እርስ በርሳቸው ትይዩ ናቸው፤ ነገር ግን "ሁለተኛው የባቡር ሀዲድ" ከመጀምሪያው ባቡር ሀዲድ የበለጠ ጠንካራ ሆኖ ይታያል። በተመሳሳይ መልኩ በ**መዝሙር 38፡1** "አትገሥጸኝ" የሚለው ቃል በመስመር አንድ "አትቅሠፈኝ" ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው። እንደዚሁም በመስመር ሁለት ላይ ያለው "በመዓትህ" የሚለው በመስመር አንድ "በቁጣህ" ከሚለው ቃል ጋር ትይዩ ነው። ነገር ግን በትይዩነት እንደሚጠበቀው "በመዓትህ" የሚለው ቃል "በቁጣህ" ከሚለው ቃል ጋር ትይዩ ቢሆንም "በመዓትህ" የሚለው ግን የበለጠ ጠንካራ ነው።

በ**ምሳሌ 6፡16** ላይ ተመሳሳይነት ያለውን ሌላ ምሳሌ እንመልከት፤

*እግዚአብሔር የሚጠላቸው ስድስት ነገሮች ናቸው፤*

*ሰባትንም ነፍሱ አጥብቃ ትጸየፈዋለች።*

በሁለተኛው መስመር "ሰባት" ተብሎ የተጠቀሰው ቁጥር በመጀመሪያው መሰመር "ስድስት" ተብሎ ከተጠቀሰው ቁጥር እንዴት እንደ ሚበልጥ ልብ ማለት ያስፈልጋል። በእንዲህ ዓይነት መንገድ ቁጥሮችን መጠቀም በትይዩ ግጥሞች የተለመደ ነው። ሁለተኛው ቁጥር ከመጀመሪያው ይበልጣል። እግዚአብሔር "በሚጠላው" እና በእርሱም ዘንድ "አስጸያፊ" በሆነው ነገር መካከል ያለውን እድገት ልብ ማለት ያስፈልጋል። የሁለተኛው አገላለጽ የበለጠ ጠንከር ይላልና።

እንደገና ለማስታውስ ያህል ግጥም በጽሑፎች ውስጥ በጣም የተለመደ የሥነ-ጽሑፍ  አይነት ነው። ለምንድነው  በጽሑፎች ውስጥ ከሚገኘው ብዙውን መልዕክት በግጥም መልክ ለአንባቢ የቀረበው? ለዚህ ጥያቄ ምናልባት ብዙ መልሶች ሊኖሩ ይችላሉ። ከነዚህም ውስጥ አምስት ምክንያቶች እነሆ፦


1. ግጥም እንደ ሙዚቃ ወይም የጥበብ ሥራ ነው። ስለዚህ ልክ እንደ ሙዚቃ ወይም የጥበብ ሥራ የልብ ቋንቋ ይናገራል። የቅዱሳት መጻሕፍት አንዱ ክፍል የሆነው መዝሙረ ዳዊት ለሺህ ዓመታት በብዛት ጥቅም ላይ የዋለበት አንዱ ምክንያት የግጥም መጽሐፍ በመሆኑ ነው።


2. ግጥም ፍቅርን፣ ደስታን፣ ተስፋን እና ውበትን የሚገልጽበት መንገድ ሌሎች የሥነ ጽሑፍ ዓይነቶች በቀላሉ ሊገልጹት በማይችሉበት መንገድ ነው። ይህ በተለይ ፍቅር፣ ደስታ፣ ተስፋ እና ውበት በጽሑፎች ውስጥ ዋና ዋና ጭብጦች በመሆናቸው በጣም አስፈላጊ ነው።

3. በግጥም ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው “የልብ” ቋንቋ በተለይም ሰዎች በመከራ ውስጥ በሚያልፉበት ጊዜ አስፈላጊ ነው። በመከራ ጊዜ መታገስ በጽሑፎች ውስጥ ዋና ጭብጥ ስለ ሆነ ስለዚህ ግጥም ለጽሑፎች ተፈጥሯዊ ምርጫ ነው። ግጥም በመከራ ለሚያልፉ ሰዎች እንደ ስጦታ ነው።

4. ግጥም የትይዩነት አካል የሆነው የማያቋርጥ ድግግሞሽ በተለይም አንድን ነጥብ ለማጉላት በጣም ተስማሚ ነው። በመሆኑም በግጥም ውስጥ ያሉት ዋና ዋና ነጥቦች በጠንካራ ቃላት ተደጋግመው ይነገራሉ።

5. በግጥም መልክ የተጻፉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በትረካ መልክ ከተጻፉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ይልቅ ለማስታወስ ቀላል ናቸው። አብዛኛው ሰው ማንበብ በማይችልበት ዘመን የጽሑፎች መልዕክት ሕዝቡ ሊደግመውና ሊያስታውሰው በሚችለው በግጥም መልክ መጣ። ሰዎች ማንበብ በሚችሉባቸው ቦታዎች እንኳ የቅዱሳት መጻሕፍት ቃላት በቃላቸው እንዲይዙ አስፈላጊ ነገር ነው። ደግሞም ከሌሎች የሥነ ጽሑፍ ዓይነቶች ይልቅ ግጥሞችን በቃል ለመያዝ ቀላል ከመሆኑ አንጻር እግዚአብሔር ሕዝቡ በተለይም የግጥም ክፍሎችን እንዲያስታውሱ ይፈልግ ይሆን ይሆናል።





## 9. በጽሑፎች ውስጥ ያሉት ዋና ገፀ ባህሪያት በነቢያት ዘመን ከኖሩት አብዛኞቹ ሰዎች በጣም የተለዩ ናቸው። በጽሑፎች ውስጥ ያሉት ዋና ገፀ-ባህሪያት በታላቅ የፈተና ጊዜም እንኳ ቢሆን ለእግዚአብሔር ታዛዦች ናቸው።

በጽሑፎች ትረካ መጽሐፍት ውስጥ የተገለጹት ዋና ገፀ ባህሪያት ለእግዚአብሔርና ለትዕዛዛቱ ታዛዦች ናቸው። ኢዮብ፣ ኑኃሚን፣ ሩት፣ ቦዔዝ፣ የዳንኤል ሦስቱ ጓደኞቹ፣ መርዶኪዮስ፣ አስቴር፣ ዕዝራ እና ነህሚያ ሁሉም ታማኝ የእግዚአብሔር ተከታዮች ተደርገው ተገልጸዋል። በዚህም ዘመን ያሉ ክርስቲያኖች ሊከተሉዋቸው የሚገቡ ምሳሌዎችን ከእነዚህ ሰዎች አንዳቸውንም በ“ዋና” ወይም በ“ትንሽ” ኃጢአቶች አለመከሰሳቸው አበረታች ነገር ነው።


ነገር ግን በእመነታቸው እና በታዛዥነታቸው ምክንያት ልንመስላቸው የሚገባው በትረካ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙትን ዋና ገፀ ባህሪያት ብቻ አይደሉም። እደዚሁም ደግሞ ገጣሚው በግጥም ክፍሎች ውስጥ ሲናገር እንደ ታዛዥ እሥራኤላዊ ተገልጿል። በሰቆቃው ኤርምያስ ላይ ባለው ባለቅኔ ታዛዥ እሥራኤላዊ እንዴት እንደሚያዝን የሚያሳይ ምሳሌ ነው። በመኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን ላይ የሚገኘው ገጣሚ ታዛዥ እሥራኤልዊ ስለ ጋብቻ ያለውን አመለካከት የሚያሳይ ምሳሌ ነው። በእያንዳንዱ መዝሙረ ዳዊት ውስጥ ያለው ገጣሚ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው ሰው በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ እንዴት እንደሚያስብ ወይም እንደሚያደርግ የሚያሳይ ምሳሌ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ይሰጣል።

በጽሑፎች ውስጥ ከተገለጹት የዋና ገፀ ባህሪያት መታዘዝ በነቢያት ጊዜ ከትገለጹት የአብዛኞቹ ሰዎች አለምታዘዝ በጣም የተለየ ነው። በነቢያት ዘመን እሥራኤላውያን ለተወሰነ ጊዜ ባለመታዘዝ ይመላለሱ ነበር፤ ከዚያም በከፊል ንስሐ ይገቡና መታዘዝ ይጀምራሉ፤ ደግሞም መልሰው ባለመታዘዝ ይመላለሳሉ ከዚያም መልሰው በላመታዘዛቸው ይጸጸታሉ። የእሥራኤላውያን በተደጋጋሚ መውደቅና መነሳት ለእግዚአብሔር በዘላቂነት በመታዘዝ ለመኖር የልብ ለውጥ እንደ ሚያስፈልጋቸው አመላካች ነበር።

በጽሑፎች ዘመን የነበሩቱ ሰዎች ለምንድን ነው ታዛዥ የተባሉት? ሰባኪ ወይም አስተማሪ የዚህን ጥያቄ መልስ በጥንቃቄ ሊያስብበት ይገባል። ሰዎቹ ታዛዥ ናቸው ምክንያቱም እግዚአብሔር ታዛዥ እንዲሆኑ ስለረዳቸው ነው።

በጽሑፎች ውስጥ ከምናገኛቸው ከዋና ገፀ ባህሪያ መካከል አንዳቸውም በእሥራኤላውያን ነገሥታት ዘመን አለመኖራቸው ትኩረት የሚስብ ጉዳይ ነው። በጽሑፎች ውስጥ የሚገኙትን ሁሉም ሰዎች እውነተኛው ንጉሥ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ እንዲነግሥ በጉጉት ይጠባበቁ ነበር። ያም እውነተኛ ንጉሥ ክርስቶስ ነው።

ጽሑፎች





## 10. በጽሑፎች ውስጥ ያሉት ዋና ገፀ ባህሪያት ጣዖታትን አያመልኩም ነበር።

በ**ዘዳግም 4፡15–28** ሙሴ እሥራኤላውያን በጣዖት አምልኮ ምክንያት ከመልካሚቱ ምድር የሚባረሩበት ዘመን እንደ ሚመጣ ተንብዮ ነበር። የሆነውም ይኸው ነው። ምንም እንኳን በእግዚአብሔር ፀጋ ምክንያት በሥራኤል ውስጥ አንዳንዶች ሰዎች ጣዖትን ባያመልኩም (ለምሳሌ **1 ነገሥ 19፡18** ይመልከቱ)፣ በነቢያት የተገለጹት አብዛኞቹ ሰዎች ጣዖታትን ያመልኩ ነበር። በዚህ ኃጢአት ምክንያትም የእሥራኤል ሕዝብና የይሁዳ ሕዝብ ከምድሪቱ ተባረሩ። ነቢያት የእሥራኤልን ጣዖት አምልኮ ተናገሩ፤ እራኤል ንስሐ መግባት አለባት የሚል ጥሪ አቀረቡ፤ እሥራኤል ግን ንስሐ ለመግባት ፈቃደኛ አልነበረችም፤ በዚህ ምክንያት የእሥራኤል ከምድሪቱ ተማርከው መሄዳቸውን ይናገራሉ።

በጽሑፎ ውስጥ ከሚገኙት የትረካ መጽሕፍት የተገለጹት ዋና ገፀ ባህሪያት ጣዖት አምላኪዎች አልነበሩም (ዳንኤልን፣ አስቴርን እና ዕዝራና ነህምያን ይመልከቱ)። የእግዚአብሔር ጸጋ በዝቶላቸው ጣዖት አያመልኩም ነበር። በሌላ መልኩ እውነተኛውን አምላክ ደግሞ የሚፈልጉትን ያህል ለማምለክ አይችሉም ነበር። ምክንያቱም እነሱ በኖሩበት ዘምንና ቦታ መቅደስ አልነበርም፣ ሊቀካህን አልነበራቸውም እንደዚሁም የሚመራቸው ንጉሥ አልነበርም።

በጽሑፎች ውስጥ የነበሩቱ ሰዎች **በሆሴዕ 3፡4** በተገለጸው ዘመን ውስጥ ይኖሩ ነበር።

*የእሥራኤል ልጆች ያለ ንጉሥ ያለ አለቃ፣ ያለ መሥዋዕትና ያለ ዓምድ፣*


*ያለ ተራፊም ብዙ ወራት ይቀመጣሉና።*

የሐሰት አማልክትን እያመለኩ ባይሆንም በመጽሐፍቶቹ ዘመን ሕዝቡ ይጠባበቅ ነበር። እግዚአብሔር እውነተኛው ቤተ መቅደስ እንዲሠራ በቸርነቱ እንዲፈቅድላቸው እና እግዚአብሔር ጻድቅ ንጉሥ እንዲሾምላቸው እየተጠባበቁ ነበር።

ይሁን እንጂ በዚህ ዘመን ያሉ የእግዚአብሔር ሰዎች ቤተመቅደስንና ንጉሣቸውን እየጠበቁ አይደሉም፤ ምክንያቱም በ**ሆሴዕ 3፡5** ላይ የተገለጸው ጊዜ ደረሷልና!

*ከዚያም በኋላ የእሥራኤል ልጆች ተመልሰው አምላካቸውን እግዚአብሔርንና ንጉሣቸውን ዳዊትን ይፈልጋሉ፤ በኋለኛውም ዘመን ፈርተው ወደ እግዚአብሔርና ወደ በረከቱ ይመጣሉ።*

በዚህ ጥቅስ በተነገረው መሠረት "የኋለኛው ዘመን" መጥቷል። እውነተኛው የዳዊት ልጅ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በዙፋኑ ላይ ጠቀምጧል። የእግዚአብሔር ሕዝብ፤ "በአብርሃም" በኩል "እግዚአብሔርን እና ቸርነቱን በመፍራት መጥተዋል። አማኞች ሁሉ የአብርሃም ልጆች ስለሆኑ እና እንደዚሁም በአብርሃም በኩል "የእሥራኤል ልጆች" በመሆናቸው የእነዚህ ሁሉ ተስፋዎች ወራሾች ናቸው (**ሮሜ 2፡28–29፤ ገላትያ 3፡7–9፣ 29** ይመልከቱ)።






## 11. ዋነኞቹ ገፀ ባህሪያት በመከራ ወቅት የእግዚአብሔር ጽናት ምሳሌዎች ናቸው።

በጽሑፎች ትረካ ክፍል ውስጥ ያሉት ዋና ገፀ ባህሪያት በታላቅ መከራ ውስጥ የአምላካዊ ጽናት ምሳሌነት ያመለክታሉ። ዳንኤል፣ የዳንኤል ሦስቱ ወዳጆች፣ መርዶኪዮስ፣ አስቴር፣ ዕዝራና ነህምያ ብዙ መከራ ደርሶባቸዋል። ይህም እግዚአብሔር በዚህ ምድር ላይ ለሕዝቡ ሁልጊዜ ሰላማዊ ሕይወትና ብልጽግና ብቻ እንደማይሰጣቸው የሚያሳይ ማስረጃ ነው። ይሁን እንጂ የእነዚህ ሰዎች በእምነታቸው መጽናት እግዚአብሔር ሕዝቡ የሚያጋጥማቸውን ፈተናዎች ለመቋቋም የሚያስችል ብርታት እንደሚሰጣቸው የሚያሳይ ነው።

ነገረ ግን በጽሑፎች ትረካ ክፍል ውስጥ ያሉት ዋና ገፀ ባህሪያት መከራ የሚቀበሉት እነርሱ ብቻ አይደሉም፤ እንደዚሁም እንደ መግቢያ በሚያገለግለው በመጽሐፈ ሩት ውስጥም መከራ መቀበል ዋና ጭብጥ ነው። ኑኃሚንና ሩት በጣም ተቸግረው ነበር። እንደዚሁም የብዙ መዝሙሮች ደራሲያን በግልጽ መከራ እንደ ተቀበሉ ያሳያል። ኢዮብ ከባድ ፈተናዎችን አስተናግዷል። የሰቆቃው ኤርምያስ ጸሐፊም እንደ ተሰቃየ እርግጥ ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ መከራ መቀበል በጽሑፎች ውስጥ እንደ ዋና ጭብጥ ተገልጿል። የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚሰቃይ ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን መከራ ቢቀበልም በእምነቱ ደግሞ እየበረታ የሚሄድ ሕዝብ ነው እንጂ።

በዚህም ዘመን ያሉት የእግዚአብሔር ሕዝቦች በጽሑፎች እንደ ተገለጹት ሰዎች በጣም መከራ ሊቀበሉ ይችላሉ። እግዚአብሔር ግን ሕዝቡን ከክፉ ነግሮች ሁሉ ያድናቸዋል። ስለዚህ የእግዚአብሔር ሕዝብ በፈተና ሲያልፍ የዘላለም ሕይወት እንዲወርሱ በጽሑፎች ውስጥ እንዳሉት ሰዎች መጽናት ይጠበቅባቸዋል። ኢየሱስ ወደ ምድር መጥቶ ለሰዎች ሞቷል ከሞትም ተነስቷል ማለት በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ መከራ የለም ማለት አይደለም። የእግዚአብሔር ሕዝብ በመከራ ወቅት መታገሥ እንዳለባቸው የሚናገሩ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች አሉ። ለምሳሌ፡- **2 ጢሞቴዎስ 3፡12፣ 4፡5፣ ዕብራውያን 10፡ 32–39፣ 12፡2–3፣ 12፡7፣ 13፡12–14፤ ያዕቆብ 1፡2 እና 1 ጴጥሮስ 2፡19–23** ይመልከቱ።





## 12. ጽሑፎች በተስፋ የተሞሉ ናቸው

ነቢያት በእግዚአብሔር ታሪክ ውስጥ ያለውን በአስከፊ የአለመታዘዝ ጊዜ ትንቢት ይናገሩ ነበር። የእሥራኤል ሕዝብ በባዕድ አገር ያልኖሩበትን ጊዜ የሚገልጹት የነቢያት የመጨረሻ መጻሕፍት (ሐጌ፣ ዘካሪያስ እና ሚልክያስ) እንኳን ሕዝቡን በደስታ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ እንደሚመላለሱ አድርገው አያቀርቡም። ምንም እንኳን ሰዎቹ ከስደት ተመለሰው አሁን በተስፋይቱ ምድር ቢኖሩም ለእግዚአብሔር ነገር ግድ አልነበራቸውም (ለምሳሌ፦ **ሐጌ 1፡1–11፣ ዘካሪያስ 1፡2–6** እና **ሚልክያስ 1፡1–2፡17** ይመልከቱ)። ሕዝቡ ባኣልን እያመለኩ ባይሆንም እንኳ ነገር ግን እግዚአብሔርን ደግሞ በእውነት አያመልኩም ነበር።

ይሁን እንጂ በአለመታዘዝም ጊዜ ቢሆን ሁልጊዜ እግዚአብሔርን የሚወዱ ሰዎች ነበሩ። እነዚህም ሰዎች በጽሑፎች ውስጥ ዋና ገፀ ባህሪያት ናቸው። ይህ ፈሪሃ እግዚአብሔር የነበራቸው ሰዎች አንዳንድ ጊዜ **ቅሬታዎች** ተብለው ይጠራሉ። ጽሑፎች ደግሞ ለእግዚአብሔር ቅሬታዎች በሚሆኑ መልዕክት የተሞሉ ናቸው። ቅሬታዎች የእግዚአብሔር ሕዝብ በግዞት በሚኖርበት ዘመን እንኳ ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆን እንደሚቻል ያሳያሉ። ስለዚህ ጽሑፎች ለእግዚአብሔር ሕዝብ እውነተኛ ተስፋና እርዳታ ይሰጣሉ። እንደዚሁም ጽሑፎች በእግዚአብሔር የተቀባውን ንጉሥ (ክርስቶስ) ለሚጠባበቁና በመከራ ለሚሰቃዩ የእግዚአብሔር ሰዎችን የሚያበረታታ መልዕክት የያዙ ናቸው።

የዚህ ዘመን ምእመናን ጽሑፎች በተጻፉበት ዘመን ከኖሩት ሰዎች በጣም የተለየ በሆነ ዘመን ውስጥ ይኖራሉ። በእርግጥ ንጉሡ መጥቷል! ቤተ መቅደሱም እየተገነባ ነው (**ኤፌሶን 2፡19–22** ይመልከቱ)። መንፈስ ቅዱስ በአማኞች ውስጥ ይኖራል፤ ስለዚህ በማንኛውም ሁኔታ የማያቋርጥ እርዳታ እና ማበረታቻ ይሰጣል (**ዮሐንስ 14፡15–17** ይመልከቱ)። ደግሞም አማኞች ዛሬ ሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ ብሉይና ሐዲስ ኪዳን አለላቸው። ይሁን እንጂ ዛሬም ቢሆን አማኞች ከእግዚአብሔር መልካም ቦታ ውጪ እየኖሩ ነው። ቀድሞውንም ሕይወት አግኝተናል ነገር ግን ሙሉ ርስታችንን ገና አልተቀበልንም። ለዚህም ነው **ያዕቆብ 1፡1** እና **1 ጴጥሮስ 1፡1** አማኞች "በስደት" እንደሚኖሩ የሚገልጹት። ጽሑፎች ዛሬም ለአማኞች በተስፋ የትሞሉ ናቸው። እግዚአብሔር በስደት የሚኖሩትን ሕዝቦቹን እንደሚያስብና ደግሞም በጣም አስቸጋሪ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ እንኳን ታማኝ መሆን እንደሚቻል ያሳያሉ። በረግጥ በክርስቶስ የሆኑ ሁሉም አማኞች ይሰደዳሉ ( **ማቴዎስ 5፡10–12፣ 2 ጢሞቴዎስ 3፡12 እና ራዕይ 12** ይመልከቱ)። ስለዚህ አማኞች ጌታቸውን ሳይክዱ መዘልቅ ይኖርባቸዋል። ጽሑፎች በስደት ውስጥ ሲያልፉ እርሱን እንዳይክዱ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ከሰጣቸው "መፍትሔዎች" አንዱ ናቸው።





## 13. መጽሐፈ ሩት ፍጹም ተስማሚ የሆነ የጽሑፎች መግቢያ ነው

ተደጋግሞ እንደ ተገለጸው መጽሐፈ ሩት በጽሑፎች ውስጥ የመጀመሪያ መጽሐፍ ነው። ስለዚህ በብሉይ ኪዳን ቀኖና ውስጥ ልዩ ቦታ አለው (ቀኖና ሥልጣን ያላቸው የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ዘርዝር ማለት ነው)። መጽሐፈ ሩት በጽሑፎች ውስጥ ላሉ መጽሐፎች ሁሉ ለአንባቢ እንደ መግቢያ ሆኖ ያገለግላል። ይህ ማለት አንባቢን ለቀሪዎቹ ጽሑፎች ለንባብ ቃና እና እንደዚሁም በጽሑፎች ውስጥ ላሉት ዋና ዋና ጭብጦች ያዘጋጃል ማለት ነው።

መጽሐፈ ሩት ማን እንደጻፈው ወይም መጽሐፉ መቼ እንደተጻፈ አይታወቅም። ይሁን እንጂ በሩት ላይ የተገለጹት ሁኔታዎች የተፈጸሙት መቼ እንደሆኑ ይታወቃል። በመጽሐፈ ሩት ውስጥ የተገለጹት ክንውኖች የተፈጸሙት "በዘመነ መሳፍንት" ጊዜ ነው (**ሩት 1:1**)። ይህም ማለት መጽሐፈ መሳፍንት ውስጥ በተመዘገበበት ጊዜ በሩት ውስጥ የተፈጸሙት ድርጊቶች ተፈጽሟል ማለት ነው። ይህም ደግሞ በዘመናዊ መጽሐፍ ቅዱሶች ውስጥ መጽሐፈ ሩት  ከመጽሐፈ መሳፍንት በኋላ የተቀመጠበትን ምክንያት ያብራራል። ይሁን እንጂ የሩት መጽሐፍ ከመጽሐፈ መሳፍንት በጣም የተለየ እና ዓላማውም ለየት ያለ እንደሆነ ግልጽ ነው። ሆኖም ዓላማው በጽሑፎች ውስጥ ከሚገኙት ከሌሎች መጻሕፍት ጋር ተመሳሳይ ይመስላል። ስለዚህ ለዛም ሳይሆን አይቀርም ሩት ከነቢያት ጋር ሳይሆን በጽሑፎች ውስጥ የተደረደረው።

በመጽሐፈ መሳፍንትና ሩት መካከል ያለውን ልዩነት በቀላሉ የሚታይ ነው። በመሳፍንት ውስጥ ጥቂት ታማኝ ሰዎች ቢኖሩም በአብዛኛው በሰዎች አለመታዘዝ እና እምነት ማጣት ላይ ያተኩራል። ሕዝቡ በአብዛኛው እግዚአብሔርን መከተል አይፈልግም ነበር። መጽሐፈ ሩት ግን በዋና ገፀ ባህሪያቱ ታዛዥነት እና ታማኝነት የሚያተኩር መጽሐፍ ነው። በመጽሐፈ መሳፍንት ውስጥ "ሰው ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር" (**መሳፍንት 21:25**)። ነገር ግን በመጽሐፈ ሩት ውስጥ ዋንኞቹ ገፀ ባህሪያት በእግዚአብሔር ፊት ትክክል የሆነውን ለማድረግ ይጠነቀቁ ነበር። በመሳፍንት ውስጥ እግዚአብሔር ከብዙ ሰዎች የራቀ ይመስላል። በሩት ውስጥ ደግሞ እግዚአብሔር ለሰዎች በጣም የቀረበ ይመስላል። እንደዚሁም በተከናወኑ ሁነቶች ሁሉ የእግዚአብሔር መልካም እጅ በሥራ ላይ እንዳለ የሚያሳይ ማስረጃ አለ።

የትረካ መጽሐፍ እንደ መሆኑ መጠን ምናልባት አንባቢው መጽሐፈ ሩትን በጽሑፎች ውስጥ ካሉት ሊሎች የትረካ መጽሐፎች ጋር እንደሚገኝ ሊገምት ይችል ይሆናል። በሌላ አነጋገር ሩት ከዳንኤል፣ ከአስቴር፣ ከዕዝራና ነህሚያ እና ከዜና መዋዕል ጋር መያያዙ ተፈጥሯዊ ነው። ይሁን እንጂ ሩት በጽሑፎች ውስጥ ከሌሎች የትረካ መጽሐፎች ጋር አልተቀመጠም። በመሠረቱ ሌሎችም በጽሑፎች ውስጥ የሚገኙት ማለትም የግጥም መጻሕፍት (መዝሙረ ዳዊት፣ ኢዮብ፣ ምሳሌ፣ መክብብ፣ መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን

እና ሰቆቃው ኤርምያስ) በሩት እና በጽሑፎች ውስጥ በሚገኙ ሌሎች የትረካ መጻሐፍት መካከል ይገኛሉ። ሩት ግን በጽሑፎች ውስጥ ካሉት ሌሎች “ታሪኮች” ሆን ተብሎ ተለይቷል። ይህም የመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻው ቅደም ተከተል ያዘጋጀው አርታኢ (ዎች) መጽሐፈ ሩትን ለተቀሩት ጽሑፎች መግቢያ ይሆናል ብለው ስለገመቱ ሊሆን ይችላል።

በጽሑፎች ውስጥ ካሉት ዋና ዋና ጭብጦች አንዱ **ታማኝነት** ይመስላል። ጽሑፎች የእግዚአብሔርን ታማኝነት ለቃልኪዳኑ ተስፋዎች ያጎላሉ። ጽሑፎች መከራ የሚቀበሉትን ሕዝቦቹን ለመጠበቅ እንደሚችል የእግዚአብሔርን ታማኝነት ያሳያሉ። እንደዚሁም የእግዚአብሔር ሕዝቦች በእግዚአብሔር በመታመን ሲቀጥሉ እና ሙሉ የሆነውንና የመጨረሻው መዳን ሲጠባበቁ የሚያሳዩትን ታማኝነት ያጎላሉ። እንደዚሁም ጽሑፎች በትክክለኛውጊዜ ታማኝ ሕዝቡን ከመከራ ለማዳን እና ወደ ዘላቂ የእረፍት ቦታቸውን ለመውሰድ እንደሚችል የእግዚአብሔር ታማኝነት ይገልታሉ። መጽሐፈ ሩት እነዚህ ነገሮች ሁሉ ላይ አጽንዖት ይሰጣል። በሩት ውስጥ ያለው ታሪክ አንባቢውን ስለእግዚአብሔር ታማኝነትና በመከራ የሚያልፈው የእግዚአብሔር ሕዝብ ታማኝነት በጽሑፎች ውስጥ በሚገኙ በተቀሩት መጻሕፍት እንደ ታየው በትክክል ያዘጋጃል።

መጽሐፈ ሩት የሚጀምረው በሚያበረታታ መንገድ አይደለም። እንዳውም **ሩት 1፡1–5** ያለው የመጽሐፈ መሳፍንት ክፍል ይመስላል። በእስራኤል ውስጥ ረሃብ እንዳለ ይናግራል (ሩት 1፡1)። እግዚአብሔር ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ ቃል የገባላቸውን “ወተትና ማር በምታፈሠው” በመልካሚቱ ምድር ላይ ያለው ረሃብ በዘፈቀደ እንደ ተከሰተ ዓይነት ክስተት ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም። ይልቁንም ይህ ረሃብ እግዚአብሔር ሕዝቡ ባለመታዘዛቸው እና በጣዖት አምልኮታቸው ምክንያት እንዳልተደሰተ ማሳያ ተደርጎ መታየት ይኖርበታል (**ዘዳግም 28፡15–24** ይመልከቱ)። በረሃቡ ምክንያት ነው የኑኃሚን ባል ቤተሰቡን ይዞ ከተስፋይቱ ምድር ወደ ሞዓብ ምድር የተሰደደው። ይህም በእግዚአብሔር ላይ እምነት እንዳልነበረው ያሳያል። በዚያም በተሰደደበት በሞአብ ምድር ሞተ። ከዚያም ደግሞ የኑኃሚን ሁለቱ ወንዶች ልጆች የእሥራኤል አምላክ የማያመልኩትን አሕዛብ ሚስቶች አገቡ። ከተጋቡም በኋላ ከኑኃሚን ወንዶች ልጆች ያገቡት ሁለቱም ሴቶች ልጆች አልወለዱም። ይህ ማለት በኑኃሚን ቤተሰብ ውስጥ ፍሬያማነት ሳይሆን መካንነት የተለመደ ነበር። በመጨረሻም የኑኃሚን ሁለቱም ልጆች ሞቱ። እነዚህ ሁሉ ክስተቶች ከመጽሐፈ መሳፍንት ጋር ይመሳሰላሉ። እግዚአብሔር ኑሃሚንን የተዋት ትመስላለች። ባልዋ ሞተ፤ ልጆችዋም ሞቱ፤ ስለዚህ ተስፋዋ ሁሉ የሞተ ይመስላል። ስለዚህም ነው ስሟን ከኑኃሚንነት ወደ ማራነት የቀየረችው (**ሩት 1፡20** ይመልከቱ)። ሕይወት ለእሷ “መራራ” ሆናለችና።

መጽሐፉ “ሩት” እየተባለ ቢጠራም የመጽሐፈ ሩት ዋና ገፀ ባህሪ ግን ሩት አይደለችም። ዋና ገፀ ባህሪ ተደርጋ የምትወሰደው ኑኃሚን ነች። ይህም በብዙ ምክንያቶች ግልጽ ነው። መጽሐፉ የሚጀምረውና የሚያበቃውም በኑኃሚን ላይ በማተኮር ነው (**ሩት 4፡14–17** ይመልከቱ)። ከዚህም በተጨማሪ መጽሐፉ ውስጥ ያለው ጽሑፍ ኑኃሚን ዋና ገፀ ባህሪ መሆንዋን ለአንባቢው ያሳስባል። ለምሳሌ ያህል በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ በቤተልሔም ያሉ ሴቶች “**ለኑኃሚን** ወንድ ልጅ ተወለዶላታል” በማለት በሩት ልጅ መወለድ ሲደሰቱ እንመለከታለን።

የመጽሐፉ ጭብጥ ኑኃሚን ከእስራኤል ምድር መሰደድዋና በሕይወቷ ውስጥ ያለው ሞት እና ፍሬ ቢስነት አይደለም። ስደት፣ ሞት፣ እና ፍሬ አልባነት የዚህ ታሪክ ጠቃሚ **ዳራ** ናቸው። ነገር ግን በሩት ውስጥ ያለው ታሪክ ጭብጥ ኑኃሚን ወደ እሥራኤል ምድር ስለተመለሰችበት እና እግዚአብሔር ለእሷ ስላለው ታማኝነት ነው። ኑኃሚን ምንም እንኳን ተስፋ የሚሆን ምክንያት ባይኖራትም እግዚአብሔር ግን እንድታፈራ እና እንድትበዛ አደረገ (**ዘፍጥረት 1፡26–28** ይመልከቱ)። የኑኃሚን ፍሪያማነት ደግሞ የሚያተኩረው **አዳኙ** የሚመጣበት ዘር በመወለዱ መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል (**ሩት 4፡14**)።

በመሠረቱ በመጽሐፈ ሩት ውስጥ የሚነገረው ታሪክ በጽሑፎች ዘመን የነበረው የእግዚአብሔር ሕዝብ ታሪክ ነው። በዚህ ጊዜ ኖኃሚን እንደ እሥራኤል ነበረች። እሥራኤልም እንደ ኖኃሚን በግዞት ውስጥ ነበረች። የእሥራኤል ሕዝብ እንደ ኖኃሚንም በባዕድ አገር ይኖር ነበር። ሞትና አሳዛኝ ነግሮች ገጥሟቸዋል እና ፍሬም አያፈሩም ነበር። እግዚአብሔር ግን በምሕረቱ ወደ ቀድሞ ሥፍራቸው ይመልሳቸዋል። ስለዚህ እሥራኤላውያን ልክ እንደ ኑኃሚንም (እና እንደ ጥንቶቹ እሥራኤላውያን) ከግዞት ምድር መውጣታቸው አይቀርም። እሥራኤልም እንደገና ፍሬያማ ትሆናለች አዳኙም ይወለዳል (ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ)! ይህም አዳኝ ልክ እንደ ኑኃሚን የልጅ ልጅ ለእግዚአብሔር ሕዝብ “ሕይወትን የሚመልስ” ነውና።

ስለዚህ ሩት እውነተኛ ታሪክ ቢሆንም በጣም ከትልቅ ታሪክ ምሳሌ ጋር የተያያዘም ነው። የእግዚአብሔር ሕዝቦች ልክ እንደ ኖኃሚንም “በሁለተኛው ዘጸአት ወይም መውጣት” ወደ እሱ እየመጡ ነው። መጽሐፈ ሩት እንግዚአብሔር ሕዝቡንም ሆነ ዘላለማዊ እቅዱን እንደማይረሳ የሚያሳይ መጽሐፍ ነው። እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደራሱ መመለስና ፍሬያማ ማድረግ ይችላል። ይህንንም ያደርገው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ ነው።

መጽሐፈ ሩት ለብዙ ታዳሚዎች በታላቅ ማበረታቻ የተሞላ መጽሐፍ ነው፡-

— መጽሐፉ በግዞት ውስጥ ለነበሩት አይሁዶች ማበረታቻ ሊያመጣ በተገባው ነበር። ምክንያቱም እግዚአብሔር አሁንም ከምድራቸው በምርኮ የተወሰዱትን እንደ ሚወዳቸውና ወደ ቀድሞ ሥፍራቸውም ሊመልሳቸው እነደሚወድ አሳይቷል። የብሉይ ኪዳን ጥንቁቅ አንባቢ በመጽሐፈ ሩት ውስጥ የሚነገረውን ታሪክ አዲስ እንዳልሆነ ማየት ይችላል። ሙሴም በ**ዘዳግም 4፡29–31** እና **30፡1–10** ስለ እሥራኤል ከመርኮ መመልስ ተናግሮ ነበር።

— መጽሐፉ በግዞት እንደነበሩት አይሁዳውያን ከእግዚአብሔር መልካም ሥፍራ ውጪ ለሚኖሩ በዛሬው ጊዜ ያሉ ክርስቲያኖች ታላቅ መበረታቻ ሊሰጣቸው ይገባል። በዚህ ዘመን ያሉ አማኞች “እንደ ተበተኑቱ አሥራ ሁለቱ ነገዶች” (**ያዕቆብ 1፡1**) እና “እንደ ተበተኑቱ መጻተኞች ( **1 ጴጥሮስ 1፡1**) ተደረገው ተገልጸዋል። ይህ ማለት በዚህ ዘመን ያሉ ክርስቲያኖች በመጨረሻ “የማረፊያ ቦታቸው” ላይ አይደሉም ማለት ነው። መጽሐፈ ሩት እግዚአብሔር በጥንት ጊዜ ለሕዝቡ ታማኝ እንደነበረና ሕዝቡን ወደ መልካም ቦታው ለመመለስና ወደ ዕረፍት ለማምጣት ያለውን ችሎታ ያሳያል። ስለዚህም በዚህም ዘመን ያሉ የእግዚአብሔር ሕዝቦች እግዚአብሔር ለሕዝቡ የገባውን ቃል መፈጸም ይችል እንደሆነ ሲያስቡ በመጽሐፈ ሩት ታላቅ ማበረታቻ ወይም መጽናኛ ሊያገኙ ይችላሉ።

— መጽሐፉ በክርስቶስና በሕዝቡ መካከል ያለውን ታላቅ ጋብቻ እንደ ሚፈጸም የሚያበረታታ መልዕክት ያቀርባል። የሩትና የቦዔዝ ጋብቻ በክርስቶስና በሕዝቡ መካከል ለሚደረገው ጋብቻ እንደ ጥላ ነው። እግዚአብሔር በሩትና በቦዔዝ መካከል ያለው ጋብቻ እንዲፈጸም ከበስተጀርባ ሆኖ እየሠራ እንደነበር ሁሉ እንደዚሁም በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መካከል ያለውንም የጋብቻ ሥነ ሥርዓት እንዲፈጸም ከመጋረጃ ጀርባ እየሠራ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ነው (**ራዕይ 19፡6–10** ይመልከቱ)።

— መጽሐፉ ክርስቶስን ሲጠባበቁ የነበሩትን ሰዎች የሚያበረታታ መልዕክት እዳለው ሁሉ፤ እንደዚሁም ደግሞ ከክርስቶስ ሞት እና ትንሣኤ በኋላም ለሚኖሩ ሰዎች የሚያበረታታ ሊሆን ይገባዋል። መጽሐፈ ሩት ክርስቶስ ከመወለዱ ከረጅም ጊዜ በፊት እግዚአብሔር ብዙ የማይታዩ ተአምራትን ይሠራ እንደነበር ያሳያል። መጽሐፉ የዳዊትን መወለድ አጽንዖት ይሰጣል ( **ሩት 4፡17** እና ቁጥር **22** ይመልከቱ)፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ከዳዊት ልጆች አንዱ ለዘላለም በዙፋኑ ላይ እንደሚቀመጥ ቃል ገብቶ ነበር ( **2 ሳሙኤል 7፡1–17** ይመልከቱ)። የዳዊት ወራሽ የሆነው

(ክርስቶስ) በጽሑፎች ውስጥ ዋና ጭብጥ ነው። ስለዚህ በጽሑፎች ውስጥ ያለው የመጀመሪያው መጽሐፍ አንባቢውን ከዚህ ጭብጥ ጋር ማስተዋወቁ ተገቢ ነገር ነው።

— ይህ መጽሐፍ እግዚአብሔር ፈቃዱን የሚያደርጉ ሰዎችን ከየትኛውም ሕዝብ ቢሆን እንደሚቀበል ያጎላል። መጽሐፈ ሩት ከእሥራኤል ወገን ያልሆነውን ሕዝብ በጥልቀት የሚያበረታታ መጽሐፍ ነው። ሩት ሞዓባዊት መሆኗ—እንደዚሁም ደግም በጣም አነጋጋሪ የሆነ ያለፈ ታሪክ ካለው ሕዝብ ወገን መሆኗ ( **ዘፍጥረት 19፡30–38** ይመልከቱ)፤ እግዚአብሔር ሰዎችን ከሁሉም ቦታዎችና ሁኔታዎች እንደሚቀበል ያሳያል። እግዚአብሔር አሕዛብን ይቀበላል (እንደ ሩት) እና “መሸሸጊያ” እንዲያገኙ “ በክንፉ በመሸፈናቸውም” ይደሰታል ( **ሩት 2፡12** ይመልከቱ)።


— መጽሐፉ መበለቶች እና የውጭ ዜጎችን ወይም እንግዶችን የሚያበረታታ ነው። በዚህ ዓለም “ሥፍራ” ወይም “መጠጊያ” የሌላቸው ሰዎች እግዚአብሔር እንዳልረሳቸው እና በእቅዱ ውስጥ ቦታ እንዳላቸው የሚያስገነዝብ ነው። እግዚአብሔር በክንፎቹ ሥር ሊሸፈኑ ለሚመጡት ሁሉ “መሸሸጊያ” መስጠት ያስደስተዋል (**ሩት 2፡12** ይመልከቱ)። የዛሬይቱም ቤተ ክርስቲያን ብትሆን እግዚአብሔር ለመበለቶች፣ ለወላጅ አልባ ሕፃናት እና ለእንግዶች ጥላ ከሚሆንባቸው መንገዶች አንዱ ናት (**ያዕቆብ 1፡27** ይመልከቱ)።


— መጽሐፈ ሩት በስደት ወቅት ስለመጽናት አንባቢዎችን የሚያበረታታ መልዕክት ያለው መጽሐፍ ነው። ልክ እንደ ኖኃሚንም ሁሉም የግዚአብሔር ሕዝቦች ከስደት እግዚአብሔር ወደ አዘጋጀላቸው ሥፍራ እንዲመለሱ ማድርግ ያስፈልጋል። ምንም እንኳን የሩት መጽሐፍ በመሳፍንት ዘመን የተከሰተ ቢሆንም፤ በዚህም ዘመን ባለው ግዞት የሚኖሩ ሰዎች (**1 ጴጥሮስ 1፡1**፤ እና **ያዕቆብ 1፡1** ይመልከቱ) ወደ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም በሚያደርጉት ጉዞ ሲያዘጋጃቸው መታየት አለበት (**ራዕይ 21፡ 2፤ 22፡5** ይመልከቱ)።

— በመጽሐፈ ሩት ውስጥ ያሉት ዋና ገፀ ባህሪያት በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ለእግዚአብሔር ታማኝ ነበሩ። በመሆኑም ኑኃሚን፣ ሩትና ቦዔዝ ልንለማመዳቸው የሚገቡ ምሳሌዎችን ለአንባቢዎች ትተዋል።

— በመጽሐፈ ሩት ውስጥ የተፈጸሙት ድርጊቶች ትክክለኛ ቀን ባይታወቅም በ 1380 እና በ 1050 ዓከልበ መካከል የተከሰቱ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል።  እንደዚሁም በሩት ውስጥ የተገለጹት

ገፀ ባህሪያት ምናባዊ አለመሆናቸውንና የተገለጹትም ክስተቶች በእርግጥ በእውነተኛ ሰዎች ሕይወት ውስጥ የተከናወኑ እውነተኛ መሆናቸውን መቀበል አስፈላጊ ነገር ነው። ታሪኮቹ ተረት አይደሉምና፤ ነገር ግን አስፈላጊ እውነታዎች ናቸው፤ ምክንያቱም ጌታ ኢየሱስ ከሩት ዘር የመጣ ነውና (**ማቴዎስ 1፡5** ይመልከቱ)። ስለዚህ ኢየሱስ እውን እንደሆነ ካመንን ቅደመ አያቶቹም እውን መሆናቸውን ማመን ደግሞ ይኖርብናል።





## 14. መዝሙራት የእግዚአብሔር ሕዝብ የመዝሙር እና የጸሎት መጽሐፍት ናቸው።

መዝሙራት የጽሑፎች አካል ናቸው። ነገር ግን መዝሙረ ዳዊት በጣም ትልቅ ስለሆነ፣ አንዳንድ ጊዜ ጽሑፎች እራሳቸው “መዝሙረ ዳዊት” ይባላሉ (ለምሳሌ ጽሑፎች **ሉቃስ 24፥44**) ውስጥ እንዴት እንደተጠቀሱ ይመልከቱ)። ምክንያቱም መዝሙረ ዳዊት በጽሑፎች ውስጥ ትልቅ ጎዳግ ያለው ትልቅ መጽሐፍ ነው።

መዝሙረ ዳዊት ጥልቅ ሀዘን እና ደግሞም ታላቅ ደስታ የሚያንጸባርቅ መጽሐፍ ነው። ደግሞም በታላቅ መከራ እንደዚሁም በታላቅ ደስታ ጊዜ የሚጠቅም መጽሐፍ ነው። በተስፋ መቁረጥ ጊዜ መጽናናትን በጨለማ ጊዜ ተስፋ እንዲሰጥ ታልሞ የተዘጋጀ ነው። የአምላካችንና የአባታችን እንደዚሁም የክረቶስ ደስታ የምንጋራበት መጽሐፍ ነው። ለዚህም ነው ለብዙ ሺህ ዓመታት የእግዚአብሔር ሕዝብ የመዝሙር መጽሐፍ እና የጸሎት መጽሐፍ ሆኖ የቆየው። ከክርስቶስ መምጣት በፊት ለኖሩ ሰዎች መዝሙረ ዳዊት ነበራቸው (የክርስቶስ መንገሥ በጉጉት ይጠባበቁ ነበር)፤ እንደዚሁም ከክርስቶስ መምጣት በኋላ ለሚኖሩ ሰዎች የመዝሙ መጽሐፍ እና ጸሎት መጽሐፍ ነው (ክርስቶስ በሕይወቱ፣ በሞቱና በትንሳኤው ያሸነፈውን ድል ወደ ኋላ እየተመለከቱ ናቸውና)። መዝሙረ ዳዊት ሁሉንም የእግዚአብሔር ሕዝቦች ለዘላለም በመዝሙሮችና በጸሎት አንድ ያደረገ መጽሐፍ ነው።

መዝሙረ ዳዊትን በተመለከተ ልብ ልንላቸው የሚገቡ ብዙ ጠቃሚ ነገሮች አሉ። ከእነዚህም ነገሮች መካከል ጥቂቶቹ ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

— **መዝሙረ ዳዊት ለእግዚአብሔር ሕዝቦች የመዝሙር መጽሐፍ እና የጸሎት መጽሐፍ ነው። ይህም ደግሞ ከኢየሱስ ልደት፣ ሕይወት፣ ሞት እና ትንሣኤ በፊት እውነት ነበር። ዛሬም ደግሞ እውነት ነው።** ስለዚህ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት መዝሙሮች እና ጸሎቶች በሁሉም ዘመናት ያሉትን የእግዚአብሔርን ሰዎች ያገናኛሉ። በዚህም ዘመን ቢሆን ቤተ ክርስቲያን እየተጠቀመችበት ነው (**ኤፌሶን 5፥19** እና **ቆላስያስ 3፥16** ይመልከቱ)። መዝሙረ ዳዊት የእግዚአብሔር ሕዝብ አብረው ሲያመልኩ እንዲጠቀሙበት የታሰበ በመሆኑ በመጽሐፉ ውስጥ በርካታ የሙዚቃ መመሪያዎች ተካቶበታል።

— **መዝሙረ ዳዊት የነገረ መለኮት መጽሐፍ ነው።** ደግሞም በአዲስ ኪዳን ውስጥ በብዛት የተጠቀሰ መጽሐፍ ነው። ኢየሱስ እና ሐዋሪያትም ከመዝሙረ ዳዊት የነገረ መለኮት ትምህርት አስተምረዋል። በዚህ መጽሐፍም ክርስቶስ እንደሚነግሥ አብሥረዋል። ይህንንም ያደረጉት ሁሉም መዝሙራት—በተወሰነ መልኩም ቢሆን ከክርስቶስ፣ ከወንጌል ክስተት እና ከክርስቶስ ተከታዮች ጋር የተገናኙ በመሆናቸው ነው።

ሐዋሪያት መዝሙረ ዳዊትን በመጠቀም ስለ ዳዊትና ስለ ዳዊት መንግሥት ታሪክ ትምህርት አላስተማሩም። ዳዊት ደግሞ በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ ዋንኛ ገፀ ባህሪ አልነበረም። ይልቅስ ዳዊት የጻፈው ስለ ክርስቶስ እንደሆነ ያውቅ ነበር። ለክርስቶስ ተከታዮች ዘላለማዊው የመዝሙር መጽሐፍ አካል የሆኑትን አንዳንድ ዘርፎች እየጻፈ መሆኑን ያውቅ ነበር።

መዝሙረ ዳዊት አንባቢዎች ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ ቅቡዕ ንጉሥ (“መሲሕ” ወይም “ክርስቶስ”)፣ ስለ እግዚአብሔር ሕዝቦች፣ ስለ እግዚአብሔር ጠላቶች፣ ስለ ዓለም፣ ኃጢአት፣ ቅዱሳት መጻሕፍት እና ስለሚመጣው ፍርድ እንዴት ማሰብ እንዳለባቸው ያስተምራል። በመዝሙራት ውስጥ ዋናው ጭብጥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እያንዳንዱ መዝሙር በሆነ መንገድ ክርስቶስን ያካትታል።

— **ከመዝሙረ ዳዊት መስበክና ማስተማር ከብሉይ ኪዳን ትረካ ከወንጌልም ወይም ከመልዕክቶች ከማስተማር የተለየ ነው።** ሐዋሪያት በትምሕርታቸውና በስብከታቸው መዝሙረ ዳዊትን ደጋግመው ይጠቀሙ ነበር። በዚህ ዘመንም ቢሆን ሰባኪ ወይም አስተማሪ የሐዋሪያትን ቃል በጥንቃቄ በማንበብ እና መዝሙረ ዳትዊን በመስበክና በማስተማር እንዴት እንደ ተጠቀሙበት ለመማር ትልቅ እገዛ ይሰጣል።

— **የመዝሙረ ዳዊት አርታኢ (ወይም አዘጋጆች) መዝሙረ ዳዊትን በተወሰነ ቅደም ተከተል አዘጋጅቷል።** መዝሙረ ዳዊት 150 የተለያዩ መዝሙሮች ያከተተ መጽሐፍ ነው። ይሁን እንጂ እነዚህ መዝሙሮች በጊዜ ቅደም ተከተል የተደረደሩ አይደሉም። በጊዜ ቅደም ተከተል የተደረደሩ ቢሆን ኖሮ በሙሴ የተጻፈው መዝሙር በመጽሐፍ 4 ላይ ባልተቀመጠም ነበር። ይልቅስ መጽሐፍ 1 ላይ መቀመጥ ነበረበት! ይልቁንም የሙሴ መዝሙር 90ኛው መዝሙር ነው! ስለዚህ መዝሙረ 1

ሆን ተብሎ በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ አንደኛ ላይ ሲቀመጥ መዝሙር 150 ደግሞ ሆን ተብሎ በመጨረሻ ተቀምጧል። አዘጋጁ መዝሙረ ዳዊትን ለምን እንደዚህ እንዳዘጋጀው አልገለጸም። ነገር ግን አንባቢው በቅርበት በማንበብ መዝሙሮቹ እንዴት እንደሚቀራረቡ መወሰን ይችላል።

— የመዝሙረ ዳዊት ቅደም ተከተል የእግዚአብሔርን እቅድ እና የክርስቶስን የመጨረሻ ድል ያሳያል። መዝሙረ ዳዊት የሚጀምረው በመልካምና በክፉ መካከል ያለውን ትግል በመግለጽ ነው (**መዝሙር 1–2** ይመልከቱ)። ሲጀምር ክፉት የበላይ ሆኖ የሚታይ ይመስላል፤ ሆኖም መዝሙረ ዳዊት በምሥጋና ያበቃል። **መዝሙረ ዳዊት 150** ላይ ምንም ክፍት የለም። በመዝሙረ ዳዊት መጀመሪያ ላይ ብዙ ሙሾዎች ቢኖሩም፤ በመደምደሚያው መጽሐፍት ውስጥ ግን ብዙ የምስጋና መዝሙራት አሉ።

— ብዙዎቹ መዝሙራት የተጻፉት በእስራኤል በዙፋን ላይ የተቀመጠ ንጉሥ በነበረበት ወቅት ቢሆንም የመዝሙረ ዳዊት የመጨረሻ አዘጋጅ መዝሙረ ዳዊትን ያዘጋጀው ግን በእሥራኤል በዙፋን ላይ የተቀመጠ ንጉሥ ባልነበረበት ዘመን ነው። ስለዚህ የመዝሙረ ዳዊት አደርጃጀት አርታኢው እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን ዓላማ በተመለከተ የነበረውን ታላቅ እምነት ያሳያል። አዘጋጁ ሊመጣ ያለውን ንጉሥ ለማየት ባይታደልም ነገር ግን በሚመጣው ዘላለማዊ ንጉሥ ይታመን ነበር!

— **መዝሙረ ዳዊት በነቢያት ተጠቅሷል።** ስለዚህ በነቢያት ውስጥ ከመዝሙረ ዳዊት ብዙ ጥቅሶች አሉ (ለምሳሌ **ኤርምያስ 17፡7–8፣ ሕዝቅኤል 47፡12** እና **ዘካሪያስ 9፡10** ይመልከቱ)። ይህም የሚያምለክተን ቢያንስ አንዳንድ ነቢያት መዝሙረ ዳዊትን ማግኘት ችለው እንደ ነበረ ነው። መጽሐፎቻቸውን ሲጽፉ በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ የተጻፉትን ነገሮች በጥንቃቄ ያጠኑ ነበር። ይህም ሊያስደንቀን አይገባም፤ ደግሞም ለዚህም ነው ጴጥሮስ ነቢያት ቅዱሳት መጽሐፍት ሲጽፉ ያደርጉት የነበረውን ይህንኑ እንደነበረ የገለጸው (**1 ጴጥሮስ 1፡10–12** ይመልከቱ)!

በዕብራይስጥ መጽሐፍ ውስጥ "የነቢያት መጻሕፍት" ከመዝሙር መጽሐፍ በፊት መቀመጣቸው ተገቢ ነው። ይህም የዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻ አዘጋጅ አንባቢውን "የነቢያትን" ትምህርት በአእምሮው ይዞ መዝሙረ ዳዊትን እንዲያነብ እንደሚፈልግ የሚያሳይ ነውና።

— **መዝሙረ ዳዊት በአምስት “መጻሕፍት” የተከፋፈለ ነው።** እነዚህም፡- **መጽሐፍ 1 (ከመዝሙር 1–41); መጽሐፍ 2 (42–72)፣ መጽሐፍ 3 (73–89)፣ መጽሐፍ 4 (90–106) እና መጽሐፍ 5 (ከመዝሙር 107–150)** ናቸው። በአምስት ምድብ የተመደቡት መጽሐፍት ልክ እንደ መዝሙረ ዳዊት ቅደም ተከተል የኣርታኢውን ሥራ ያንፀባርቃሉ። እንደዚሁም ደግሞ አምስቱ የመዝሙረ ዳዊት መጻሕፍት አምስቱን የሕግ መጻሕፍት (ዘፍጥረት፣ ዘጸአት፣ ዘሌዋውያን፣ ዘኁልቁ እና ዘዳግም) ለማንፀባረቅ ታስቦ የተጋጁ ሳይሆን አይቀርም። መዝሙረ ዳዊት አምስቱንም የሕጉን መጻሕፍት እንደሚያንጸባርቁ የሚያሳዩ ማስረጃዎች ከሕጉ የተወሰኑ ክፍሎችን በመጥቀስ በሕጉ ውስጥ የሚገኙትን ቃላት ከክርስቶስና ከወንጌል ክንውን ጋር በማያያዝ መመልከት ይቻላል።

— **የመጀመሪያዎቹ አራት የመዝሙር መጽሐፍት ሁሉም የሚያበቁት በቡራኬ ነው (መዝሙር 41፡13፤ 72፡18–20፤ 89፡52 እና 106፡48 ይመልከቱ)**። ቡራኬዎቹ ምናልባት መዝሙረ ዳዊትን በመጨረሻ ቅደም ተከተላቸው ባዘጋጀው አርታኢ የተጻፉ ሊሆን ይችላል። የአርታኢውንም ጥልቅ እምነት ያሳያሉ። ነገር ግን አምስተኛው መጽሐፍ እንደ መጀመሪያዎቹ አራት መጻሕፍት በቡራኬ አይጨርስም። ይሁን እንጂ መጽሐፍ አምስት በተለየ አኳኋን ይጨርሳል ይህ ማለት ያለ ቡራኬ ይጨርሳል ማለት አይደለም። የመጽሐፍ አምስት የመጨረሻዎቹ አምስት ምዕራፎች ሁሉም የሚያበቁት “ሃሌ ሉያ” ወይም “እግዚአብሔር ይመስገን” በሚል ተመሳሳይ ቃላት ነው። እነዚህ ምዕራፎች ለአምስተኛው መጽሐፍ እና ለመላው የመዝሙር መጽሐፍ ተስማሚ መደምደሚያ እንደሆኑ ተድረጎ ሆን ተብሎ አንድ ላይ የተቀመጡ ይመስላል። እንግዲህ የክርስቶስ ታሪክ በሆነው በመዝሙረ ዳዊት መልዕክት ላይ በመመስረት የእግዚአብሔር ሕዝብ ደግሞ “እግዚአብሔርን ያመስግኑ!”

— **መዝሙራት ግጥሞች ናቸው።** ቅኔ ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙ የሥነ ጽሑፍ ዓይነቶች አንዱ ነው። መልዕክቶች (እንደ ሮሜ ሰዎች ወይም 1 ጴጥሮስ) እና ትረካዎች (እንደ ሳሙኤል ወይም አስቴር ያሉ) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ሊሎች ሁለት ዓይነት ጽሑፎች ናቸው። እያንዳንዱ የሥነ ጽሑፍ ዓይነት የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። ደግሞም እያንዳንዱ ዓይነት ሥነ ጽሑፍ የራሱ ዓላማ አለው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ግጥም ትይዩ በሚባለው የግጥም መልክ የተጻፈ ነው። ይህ ዓይነቱ ቅርጽ በብሉይ ኪዳን በሙሉ ጥቅም ላይ ውሏል። ትይዩነት አንድ አንቀጽ አንድ ነገር የሚናገርበት

መዋቅር ነው፣ እና ቀጥሎ ያለው አንቀጽ ወዲያውኑ የመጀመሪያውን ሀሳብ ያስተጋባል እንደዚሁም በተለምዶ የመጀመሪያውን አንቀጽ በሆነ መንገድ ያጠናክራል።

ግጥም ስሜትን በመንካት ኃይለኛ ነው። ልክ እንደ መዝሙር ቅኔ ወይም ግጥም ልብን ለማንቀሳቀስ በሚታሰቡ መንገዶች ቃላትንና የቃላት ዘይቤን ይጠቀማል። ይህ ማለት አብዛኛው የግጥም ኃይል አንባቢው እንዲነካ በሚያደርግ መንገድ የሚዘጋጅ ነው።

ቅኔ ወይም ግጥም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት የሥነ ጽሑፍ ዓይነቶች የተለየ ነው፤ ምክንያቱም ግጥም የማይረሳ ነው። ቃላቶችንና ዘይቢያዊ አነጋገሮችን ለማስታውስ ቀላል እንዲሆን ለማደረግ የታሰቡ ናቸው። ለዚህም ነው መዝሙራት ለሺህ ዓመታት እጅግ ከተሸመደዱት የእግዚአብሔር ቃል ክፍል አንዱ የሆኑት።

— **መዝሙራት በትልቅ ትረካ (ታሪክ) መካከል የተቀመጡ ግጥሞች ናቸው።** ምንም እንኳን የመዝሙር መጽሐፍ ምንም ትረካዎችን (ታሪኮችን) ባያካትትም አንባቢው የመዝሙር መጽሐፍ በሁሉም የእግዚአብሔር ቃል በተነገረው እጅግ በጣም ትልቅ ትረካ የተከበበ መሆኑ ያለማቋረጥ ማስታውስ ይኖርበታል። በመዝሙራት ውስጥ የተካተተው ትልቅ ትረካ ክርስቶስ ሕዝቡን ለማዳን በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ እንዲኖሩና እንዲያመልኩ ስለመጣበት ታሪክ በተመለከተ ነው። የዚህ ትልቅ ትረካ ማስረጃ በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ ይገኛል። ስለዚህ በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ ያሉት ሁሉም ግጥሞች ከትልቅ ታሪክ ጋር የተገኛኙ ናቸው። አንዳቸውንም ብቻቸውን የቆሙ አይደሉም።

— **ገጣሚዎች ተጨባጭ የሆኑ ቃላትን ይጠቀማሉ።** ተጨባች ቃላቶች ሊታዩ፣ ሊዳሰሱ፣ ሊቀመሱ፣ ሊደመጡ ወይም ሊሸተቱ ከሚችሉ እውነተኛ ነገሮች ጋር የተገናኙ ቃላቶች ናቸው። ገጣሚዎች ተጨባጭ ያልሆኑ ሃሳቦችን በሚጽፉበት ጊዜ እንኳን ተጨባጭ ቃላትን ይጠቀማሉ። ለምሳሌ መዝሙረኛው በ**መዝሙር 18፡34** ላይ “የናስ ቀስት መታጠፍ” እንደሚችል  ተናግሯል። የናስ ቀስት በአንድ እጅ ሊያዝ የሚችል እውነተኛ ነገር ነው። ይሁን እንጂ ገጣሚው ከነሐስ የተሠራ ቀስት መወንጨፍ ይቻላል ማለቱ አይደለም። እንዳውም ስለ እውነተኛ የጦር መሳሪያዎች እየጻፈም አይደለም። ነገር ግን “የናስ ቀስት” ጠላቶቹ እንዳያሸንፉት እግዚአብሔር የሰጠውን ታላቅ ኃይል የሚገልጽ ተጨባጭ መንገድ ነው እንጂ።

— (በዕብራይስጡ) **አንዳንድ መዝሙራት በፊደል ቅደም ተከተል ተቀምጠዋል።** ይህም በ**መዝሙር 9–10፣ 25፣ 34፣ 37፣ 111–112 እና 119** ላይ ያለውን ሁኔታ መመልከት ይቻላል። በዚህ መንገድ የተደረደሩት መዝሙራት ሙሉነትን የሚያጎሉ ይመሳል። ለምሳሌ፡- መዝሙር 119 በእግዚአብሔርን ቃል (ከ “ሀ” እስከ “ፐ”) በተሟላ መንገድ ይደሰታል። ሆኖም መዝሙረ ዳዊት ወደ ሌላ ቋንቋ (ለምሳሌ ወደ አማርኛ) ሲተረጎም የፊደል ቅደም ተከተሉ ግልጽ ላይሆን ይችላል።

— **መዝሙራት መጀመሪያ የተጻፉት በዕብራይስጥ ቋንቋ ነው።** መዝሙረ ዳዊት የተፃፈው በጥንት ቋንቋ ስለሆነ፣ ሊቃውንት ስለጥቂቶቹ ቃላት ትርጉም እርግጠኛ አይደሉም። አብዛኛውን ጊዜ ሊቃውንት ለመረዳት ጥረት የሚያደርጉት የሙዚቃ መመሪያዎች ቃላት ላይ ነው። ለምሳሌ፡- *ሴላ* የሚለው መመሪያ ምን ትርጉም እንዳለው ሊቃውንት እርግጠኛ አይደሉም። በእርግጥ የመዝሙረ ዳዊት ትርጉም ለመረዳት የግድ የዕብራይስጥ ቋንቋ ማወቅ አስፈላጊ አይደለም።

— **ብዙዎቹ መዝሙራት መዝሙሩን ለማስተዋወቅ መጀመሪያ ላይ የተጻፉ ለየት ያሉ ጽሑፎችን ያካትታሉ።** እነዚህ ለየት ያሉ ቃላት የሚያመለክቱት በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ ካሉት የግጥም ቃላት በፊት ያሉትን ቃላት ነው (ማለትም *“የዳዊት መዝሙር ከልጁ ከአቤሴሎም በሸሸ ጊዜ” ወይም ለመዘምራን አለቃ የዳዊት መዝሙር”*) የሚሉና ሌሎችም ናቸው። እነዚህ ጽሑፎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለሚገኙ በስብከትና በማስተማሩ ሥራ ላይ መካተት አለባቸው። ከላይ ለየት ባለ መልኩ የተጻፈ ጽሑፍ የሌላቸው ጥንታዊ የእጅ ጽሑፎች የሉም። ከላይ የሚጨመሩ ጽሑፎች አንባቢውን ለመርዳት የታሰቡ ናቸው። እነዚህ ከላይ የሚጨመሩ ጽሑፎች በሐዋሪያት በተነበቡት የመዝሙር እትሞችም ውስጥ ነበሩ። ይሁን እንጂ ሐዋሪያቶች ጽሑፉ የመዝሙሩ ትርጉም በሚወስንበት መልኩ አልተጠቀሙበትም። ስለዚህ አንባቢው የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች እንዴት እንደሚጠቀሙበትና ደግሞ እንደ ማይጠቀሙበት በጥንቃቄ መመርመር አለበት። ከላይ የሚጻፉቱ ተጨማሪ ጽሑፎች አንዳንድ የሙዚቃ ዓይነት መመሪያዎችንም ያካትታሉ። እነዚህ መመሪያዎች መዝሙራት ለጋራ አምልኮ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የታሰቡ መሆናቸውን በዚህ ዘመን ያሉትንም የእግዚአብሔር ሕዝቦች ሊያስታውሱ ይገባል።

— **የብዙ መዝሙራት ዋና ርዕሰ ጉዳይ “ክርስቶስ” ነው።** መዝሙራት የተጻፉት በብዙ መቶ ዓመታት እርቀት ውስጥ ነው። በዚህ የተራራቀ ጊዜ በመሀከል ብዙ ነገሥታት ነግሰዋል። ይሁን እንጂ

መዝሙራት በእነዚያ ነገሥታት ላይ የሚያተኩሩ አይደሉም። ነገር ግን በዋንኛነት አትኩሮት የሚሰጡት በአንድ የተወሰነ ንጉሥ ላይ ነው። የዚህም ንጉሥ ማንነት ለመጀመሪያ ጊዜ የተነገረው በመዝሙር 2 ላይ ነው። እርሱ በጌታ የተቀባው—ክርስቶስ ነው።

ይህ ማለት ደግሞ የመዝሙራት ርዕሰ ጉዳይ ክርስቶስ ብቻ ነው ማለት አይደለም። እንደዚሁም እያንዳንዱ መዝሙር በተመሳሳይ መንገድ ስለ ክርስቶስ እና ስለ ወንጌል ክስተት ነው ማለት አይደለም። ይህ ማለት ግን የክርስቶስ እና የወንጌልን ክስተት መረዳት እያንዳንዱ መዝሙር እንዴት እንደሚታይ ላይ ተጸኖ ይኖረዋል ማለት ነው። የመዝሙር ዋና ዕርሰ ጉዳይ ክርስቶስ ለመሆኑ ማስረጃዎች በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይገኛሉ። ለምሳሌ:- **ሉቃስ 24፡44፣ ዮሐንስ 5፡46፣ የሐዋሪያት ሥራ 3፡18–24፣ እና 1 ጴጥሮስ 1፡10–12** ይመልከቱ።

በሌላ በኩል ደግሞ አንድም ክርስቶስን ሙሉ በሙሉ የሚገልጽ  መዝሙር የለም። መዝሙር 2 ምንም እንኳን ክርስቶስን ቢያስተዋውቅም እንደዚሁም ስለክስቶስ ብዙ ቢያስተምርም ሙሉ በሙሉ ግን አይደለም። ሌሎችም መዝሙሮች ስለክርስቶስ ብዙ መረጃዎችን ያካትታሉ። ስለዚህም አንባቢው ከአንድ መዝሙር ወደ ሌላኛው መዝሙር በመሸጋገር የክርስቶስን ነገረ መለኮት መገንባት አለበት። አንባቢው በሁሉም መዝሙረ ዳዊት ውስጥ “ንጉሡን ለማግኘት” መጣጣር የለበትም። ይልቅስ ለምሳሌ አንባቢው በመዝሙር 2 ላይ ስለንጉሥ የተማረውን መዝሙር 3ን ሲያነብ ማስታውስ ይኖርበታል እንጂ። በየ መዝሙሩ የሚገኙትን በጣም የተለያየ የክርስቶስ መግለጫዎች አንዳንድ ጊዜ ለማስታረቅ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን እነዚህ የተለያዩ መግለጫዎች ማስታረቅ የአንባቢው ደስታ እና የሰባኪ ደግሞ ግዴታዎች ናቸው።

— **መዝሙረ ዳዊት ብዙ ዓይነት አማራጮችን የያዘ ነው።** ልክ የብዙ ዓይነት ሙዚቃዎች ቅንብር እንዳሉበት የመዝሙር ዝግጅት (ኮንሰርት)፣ እንደዚሁም የመዝሙር መጽሐፍ የተለያዩ የመዝሙር ዓይነቶች ያካተተ ነው። እነዚህም የተለያዩ መዝሙሮች ክርስቶስን፣ ሕዝቡንና የወንጌልን ክስተት ከብዙ አቅጣጫ ያቀርባሉ።

— **አንባቢዎች ሐዋሪያት መዝሙረ ዳዊትን እንዴት እንደሚጠቅሱ በጥንቃቄ ሊያስቡበት ይገባል።** ሐዋሪያቶች ለብሉይ ኪዳን ትርጉም ታማኝ መሪዎች ናቸው። ለዕራት በሰገነቱ ላይ በተቀመጡ ጊዜ

ከእርሱ ጋር ለነበሩት ሐዋሪያት በተናገረው ቃል፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮቹ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ተመዝግበው የሚገኙት የሐዋሪያት ትምህርት እውነት እና አስተማማኝ መሆኑን እንዲያውቁ እንደሚፈልግ ግልጽ ነው (**ዮሐንስ 14፡26 እና ዮሐንስ 16፡12–15** ይመልከቱ)። ኢየሱስ እና ሐዋሪያት መዝሙርን መሲሃዊ በሆነ መንገድ አንብበውታል። አንባቢው ኢየሱስና ሐዋሪያቱም እንዴት እንድሚጠቅሱ በጥንቃቄ መመርመር ይኖርበታል ማለት ነው። የሚጠቅሷቸው መዝሙራት ሁሉ ከኢየሱስ ክርስቶስ፣ ወይም ከእግዚአብሔር ሕዝብ፣ ወይም ከእግዚአብሔር ጠላቶች፣ ወይም ከወንጌል ክስተት ጋር ይዛመዳሉ። ሐዋሪያት መሲሃዊ ያልሆነና ወንጌልን የማይመለከት መዝሙር ሲተረጉሙ የሚያሳይ ምንም ምሳሌ የለም። ሐዋሪያት የመዝሙረ ዳዊት የመጨረሻ ትርጉም መዝሙር በተጻፈበት ወቅት በእስራኤል ውስጥ ስለተፈጸሙ ክንውኖች የሚመለከት ነው ብለው አይደመድሙም።

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት በወንጌላት ውስጥ የሚገኙ ከመዝሙረ ዳዊት ቀጥታ የተጠቀሱ ጥቅሶች ናቸው። ከዚህ በታች የተጠቀሱት መዝሙራት በሙሉ ከኢየሱስ ክርስቶስ፣ ወይም ከእግዚአብሔር ሕዝብ፣ ወይም ከእግዚአብሔር ጠላቶች፣ ወይም ደግሞ ከወንጌል ክስተት ጋር እንደሚዛመዱ ማስተዋል አስፈላጊ ነው።

በወንጌለ ማቴዎስ፡- ማቴዎስ 4፡6 ከመዝሙረ 91፡11–12 ያነጻጽሩ፤ እንደዚሁም ማቴዎስ 7፡23 ከመዝሙር 6፡8፣ ማቴዎስ 13፡32 ከመዝሙር 104፡12፣ ማቴዎስ 13፡35 ከመዝሙር 78፡2፣ ማቴዎስ 16፡27 ከመዝሙር 62፡12፣ ማቴዎስ 21፡9 ከመዝሙር 118፡25–26 እና ከመዝሙር 148፡1፣ ማቴዎስ 21፡16 ከመዝሙር 8፡2፣ ማቴዎስ 21፡42 ከመዝሙር 118፡22–23፣ ማቴዎስ 22፡44፣ ከመዝሙር 110፡1፣ ማቴዎስ 23፡39 ከመዝሙር 118፡26፣ ማቴዎስ 26፡38 ከመዝሙር 42፡5–6፣ ማቴዎስ 27፡35 ከመዝሙር 22፡18፣ ማቴዎስ 27፡46 ከመዝሙር 22፡1 ጋር ያነጻጽሩ።

በወንጌለ ማርቆስ፡- ማርቆስ 4፡32 ከመዝሙር 104፡12፣ ማርቆስ 11፡9 ከመዝሙር 118፡25–26፣ ማርቆስ 11፡10 ከመዝሙር 148፡1፣ ማርቆስ 12፡10 ከመዝሙር 118፡22–23፣ ማርቆስ 12፡36 ከመዝሙር 110፡1፣ ማርቆስ 14፡34 ከመዝሙር 42፡5–6፣ ማርቆስ 15፡24 ከመዝሙር 22፡18፣ ማርቆስ 15፡34 ከመዝሙር 22፡1 ጋር ያነጻጽሩ።

በወንጌለ ሉቃስ፡- ሉቃስ 4፡10–11 ከመዝሙር 91፡11–12፣ ሉቃስ 13፡19 ከመዝሙር 104፡12፣ ሉቃስ 13፡27 ከመዝሙር 6፡8፣ ሉቃስ 13፡35 ከመዝሙር 118፡26፣ ሉቃስ 19፡38 ከመዝሙር 118፡26፣ ሉቃስ 20፡17 ከመዝሙር 118፡22፣ ሉቃስ 20፡42 ከመዝሙር 110፡1፣ ሉቃስ 23፡34 ከመዝሙር 22፡18፣ ሉቃስ 23፡46 ከመዝሙር 31፡5 ጋር ያነጻጽሩ።

በዮሐንስ ወንጌል ደግሞ፡ ዮሐንስ 2፡17 ከመዝሙር 69፡9፣ ዮሐንስ 6፡31 ከመዝሙር 105፡40፣ ዮሐንስ 10፡34 ከመዝሙር 82፡6፣ ዮሐንስ 12፡13 ከመዝሙር 118፡25–26፣ ዮሐንስ 15፡25 ከመዝሙር 35፡19፣ ዮሐንስ 19፡24 ከመዝሙር 22፡18፣ ዮሐንስ 19፡36 ከመዝሙር 34፡20 ጋር ያነጻጽሩ።

— ***ሐዋሪያት እያንዳንዱ መዝሙር አይጠቅሱም።*** *ይህ ማለት ደግሞ የዚህ ዘመን አንባቢዎች ከእነዚህ መዝሙሮች መጠቀም፣ መተርጎም ወይም መስበክ አይችሉም ማለት አይደለም። አንባቢ መረዳት ያለበት ነገር ቢኖር ሐዋሪያት እያንዳንዱን መዝሙር ወንጌልን ለመስበክና ክርስቶስንና የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንዲደሰትባቸው ይጠቀሙበት እንደ ነበር ነው።*

— ***ሐዋሪያት የመዝሙርን አንድ ክፍል ሲጠቅሱ አንባቢው ስለመዝሙረ ዳዊት እንዲያስብ ይፈልጋሉ።*** *ሐዋሪያት መዝሙረ ዳዊትን ሲጠቅሱ አንባቢው ሙሉውን መዝሙር እንዲያነብና ያንን መዝሙር በዐውደ ጽሑፉ በጥንቃቄ እንዲያጠናው እየጠበቁ ነው። ለምሳሌ በ***ማቴዎስ 27*** ሐዋሪያው ማቴዎስ ***መዝሙር 22***ን ደጋግሞ ተናግሯል። ስለዚህ ማቴዎስ አንባቢው እሱ የጠቀሳቸውን ጥቂት ጥቅሶች ብቻ ሳይሆን ወደ መዝሙር 22 ሄደው ሙሉውን መዝሙር እንዲያጠና ይፈልጋል። መዝሙረ ዳዊት በመስቀል ላይ ስለ ተፈጽሙት ክንውኖች የሚመለከት መሆኑን ለአናባቢዎቹ ምልክት እያስተላለፈ ነው ማለት ነው።*

— **የብዙ *መዝሙሮች* ደራሲያን *ዳዊት* ስለ ክርስቶስ *እየጻፈ መሆኑን* ያውቁ ነበር።** *ዳዊት ነቢይ ነበርና (***የሐዋሪያት ሥራ 2፡30***)። ሐዋሪያው ጴጥሮስ እንዳለው ሁሉም ነቢያት የክርስቶስን ቀናትና የወንጌልን ክንውን እየተነበዩ ነበር (***የሐዋሪያት ሥራ 3፡18–24*** እና ***10፡43*** ይመልከቱ)። እንደ ጴጥሮስ ገለጻ ከሆነ ነቢያት ቃላት ገና ወደ ፊት ለሚመጡ ሰዎች ታላቅ እርዳታ እንደሚሆን ያውቁ ነበር (***1 ጴጥሮስ 1፡10–12*** ይመልከቱ)። ይህ ማለት ዳዊት ነቢይ እንደመሆኑ መጠን ስለ ክርስቶስ እንደጻፈ*

ያውቅ ነበር፤ እንደዚሁም ቃሉም ቢሆን ከእርሱ በኋላ ለሚመጣው ትውልድ እርዳታ እንደሚሆን ያውቅ ነበር (**የሐዋሪያት ሥራ 2፡29–36** ይመልከቱ)። ኢየሱስ እንዳለው ዳዊት ከእግዚአብሔር በተጨማሪ በእርሱ ላይ የሆነ ሌላ ንጉሥ እንዳለ ያውቅ ነበር። ለዚህም ይመስላል መዝሙር 110ን ሲጀመር "እግዚአብሔር ጌታዬን፡— ጠላቶችህን ለእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው" ብሎ የጀመረው ( **መዝሙር 110፡1** እና **ማርቆስ 12፡35–37** ይመልከቱ)። እነዚህ ጥቅሶች ዳዊት ከእርሱ የሚበልጥ ሌላ ንጉሥ እንዳለ እንደሚያውቅ ያሳያሉ። ስለዚህ ሁሉም መዝሙራት በዚህ ብርሃን መነበብ አለባቸው።


— **መዝሙራት በእግዚአብሔር ጠላቶችና በክርስቶስ ጠላቶች ላይ ትልቅ ትኩረት ያደርጋሉ።** ይህም የሚጀመረው በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ ባለው የመጀመሪያው መዝሙር የመጀመሪያው ቁጥር ላይ ነው። በእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች ላይ የሚያተኩረው በመዝሙራት ጽሑፍ ላይ ብቻ አይደለም። እንደዚሁም ከመዝሙሩ መጀምሪያ ላይ እንደ አርዕስት ሊታይ ይችላል። ለምሳሌ፡- ከመዝሙረ ዳዊት 3 አናት ላይ እንደ አርዕስት የተጻፈው ጽሑፍ *"ከልጁ ከአቤሰሎም በሸሸ ጊዜ የዳዊት መዝሙር"* ይላል።

— **በመዝሙራት ውስጥ የክርስቶስ መከራ ዋና ጭብጥ ነው።** በመዝሙር መጽሐፍ 1 (መዝሙር 1–41) ባለው ላይ  ከሚገኙት የመጀመሪያዎቹ 41 መዝሙሮች መካከል ቢያንስ 30 የሚሆኑቱ ስለ አንድ ሰው (ስለ የተቀባ ንጉሥ) መከራና ከመከራውም ለመዳን ያቀረበውን ጩኸት በዝርዝር ይናገራሉ። ክርስቲያኖች የክርስቶስን መከራዎች ማስታውስና ኢየሱስ ደግሞ ለደረሰበት መከራ ምን ምላሽ እንደሰጠ ቢያንስ ሁለት ምክንያቶች ማየት ያስፈልጋል። በመጀምሪያ፤ የክርስቶስ መከራና ሞት ለሁሉም የእግዚአብሔር ሕዝቦች ይቅርታንና ሕይወትን አስገኝቷል። ስለዚህ መከራው ወደ ምስጋና፣ አምልኮና ውዳሴ ሊመራን ይገባል ማለት ነው። ሁለተኛ፤ ክርስቲያኖች በክርስቶስ መከራ እንዲካፈሉ ተጠርተዋል። ስለዚህም ክርስቲያኖች ሲሰቃዩ አንድ አዲስ እንግዳ ነገር እንደ ሆነባቸው እንዳይመስላቸው የክርስቶስ መከራዎች የማያቋርጥ ማሳሰቢያነት አስፈላጊ ናቸው (**1 ጴጥሮስ 4፡12–17** ይመልከቱ)።

— **በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ ያለው "ዋና ገጸ ባሕርይ" ምሳሌ መከተል።** በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ የሚናገረው ሰው ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላቸው ወንድ ወይም ሴት እንዴት እንደሚኖሩ፣

መከራ እንደ ሚቀበሉ፣ እንደሚጸልዩ፣ እንደሚያመልኩ፣ በእግዚአብሔርም እንደሚታመኑ እና እንዴት ንስሐ መግባት እንድለባቸው ያሳያል።

— **ክርስቶስ የእግዚአብሔር ሕዝብ የአምልኮ መሪ ነው።** ይህ የክርስቶስ አገልግሎት ገጽታ ለኛ መሥዋዕት መሆኑ፣ አዳኝነቱ፣ ንጉሥነቱ እና የክህነት አገልግሎቱ ሚና በተመለከተ ብዙ ጊዜ ችላ ይባላል። መዝሙራት ደግሞ ክርስቶስ እግዚአብሔርን በማምለክና የእግዚአብሔርንም ሕዝብ ወደ አምልኮ በመምራት እንደሚደሰት በግልጽ ያሳያሉ፤ ይህ አምልኮ በለቅሶ፣ በመታመን፣ በምስጋና ይታያል። ስለዚህም መዝሙረ ዳዊት ኢየሱስ ለእግዚአብሔር አብ ያለውን ፍቅር እና ሁሉም የእግዚአብሔር ሰዎች እግዚአብሔርን በመንፈስ እና በእውነት ሲያመልኩ ለማየት ያለውን ታላቅ ፍላጎት የሚያሳዩ መሆናቸውን ሊታዩ ይገባል (**ዮሐንስ 4፡23–24** ይመልከቱ)። ደግሞም መዝሙረ ዳዊት ዛሬ ኢየሱስ በምድር ላይ ከቤተክርስቲያን ጋር ቢሆን ኖሮ ሕዝቡን በአምልኮ እንዴት እንደሚመራ ያስተምረናል።



## 15. አብዛኛዎቹ መዝሙሮች ለማንበብ ሁለት መንገዶች አሉ

በመዝሙረ ዳዊት መጽሐፍ ውስጥ 150 ያህል መዝሙሮች ተካትተዋል። እነዚህም መዝሙራት አንዱ ከሌላኛው አንድ አይደለም። አንዳንዶች የምስጋናና የጸሎት፣ ቅሬታ የሚያሰሙ ጸሎቶች፣ ሊሎች ደግሞ ጥቅል የሀዘን መዝሙራት (እነዚህም የሀዘን እንጉርጉሮ መዝሙሮች ይባላሉ)፣ ጥቂት መዝሙሮች ደግሞ በጠላቱ እጅ እጅግ እየተሰቃየ ያለ ሰው ጸሎቶች ሲሆኑ፤ ሌሎች ደግሞ ፈጽሞ ጸሎት ያልሆኑ ነገር ግን የአንድ ሰው ሕይወትና ድርጊቶቹ የሚያውሱ ናቸው።

በእያንዳንዱ መዝሙር ውስጥ የሚጸልይ፣ የሚያጉረመርም፣ መከራን የሚቀበል እና የሚያመልክ ሰው በእግዚአብሔር ላይ ታላቅ እምነት ያለው ሰው መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። እንደዚሁም ደግሞ ሕይወቱና ተግባሮቹ እየተገለጹ ያሉት ሰውም በእግዚአብሔር ላይ ታላቅ እምነት ያለው ሰው ነው። ስለዚህ በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ የሚገኘው “ዋና ገጸ ባሕሪ” ምሳሌ መሆን የሚችል ሰው ነው።

ይህ በእግዚአብሔር ላይ እምነት የተሞላ የእግዚአብሔር ተከታይ የሆነ በመዝሙራት ላይ ያለው ማነው? ለምሳሌ በመዝሙረ 1 ላይ “ምስጉን ነው” የሚለው ሰው ማን ነው? ወይም በመዝሙር 3 ላይ በኃጢአተኞች እየጠጨነቅ ያለው ሰው ማን ነው? በመዝሙር 23 ውስጥ እግዚአብሔርን እንደ እረኛው ቆጥሮ ወደ እግዚአብሔር የሚመለከት ሰው ማን ነው? በእነዚህ ሦስት መዝሙሮችና በብዙ ሌሎች መዝሙሮች ውስጥ ለእንደነዚህ ዓይነት ጥያቄዎች ሁለት መልሶች አሉ?

### 1. በመዝሙራት ላይ የሚገኘው በእምነት የተሞላው የእግዚአብሔር ተከታይ ክርስቶስ ነው።

ለምሳሌ መዝሙር 1 ይመልከቱ፡- ይህ መዝሙር ክፉ ስለማያደርግና “ቀንና ሌሊትም” የእግዚአብሔርን ሕግ ላይ ስለሚያሰላስለው ስለ “ምስጉን ሰው” ነው የሚናገረው። ይህ ሰው ፍጹም ፍሬያማ ነው። ነገር ይህ ፍጹም ሰው ማን ነው? በዚህ በመዝሙር አንድ ላይ ያለው “ምስጉን ሰው” ገለጻ ጋር የሚስማማው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ እንደ ሆነ ክርስቲያኖች ይስማማሉ። ኢየሱስ ቀንና ሌሊት በእግዚአብሔር ሕግ ላይ የሚያሰላስል “የተባረከ ሰው” ነው። እርሱ ፈጽሞ ኃጢአት አልሰራም። ለክፉ ሰዎች አንድም ጊዜ እንኳን ታልፎ አልተሰጠም። ደግሞም ፍጹም ፍሬያማ ነው። የሚሰራው ሁሉ የሚከናወንለት ነው። ኢየሱስ በእግዚአብሔር የተባረከና በበረከቱም ሙሉ ኃይል የሚመላለስ ፍጹም ሰው ነው። ወደ ምድር ለምን እንደ መጣ ተረድቶ ትክክል የሆነውን ብቻ እያደረገ ነው። ስለዚህ ክርስቶስ “ በመዝሙራት ውስጥ እምነት የተሞላው የእግዚአብሔር ተከታይ ማን ነው?” ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ የመጀመሪያው መልስ ነው።

ይሁን እንጂ የመዝሙረ ዳዊት ደራሲዎች ክርስቶስን በማሰላሰል ብቻ እንድናነብ አይፈልጉም። መዝሙረ ዳዊት የሚነበበው በዚህ መንገድ ብቻ አይደለመና። መዝሙረ ዳዊት የሚነበብበት ሁለተኛው መንገድ እንደ ሚከተለው ነው።

2. **በመዝሙራት ውስጥ እምነት የተሞላው ሌላኛው የእግዚአብሔር ተከታይ ክርስቲያን ነው።**

በጌታ ኢየሱስ የሚያምኑ አማኞች፣ "በክርስቶስ" ስላሉ በእውነት መዝሙራት ስለእነሱ እየተናገሩ መሆኑን መናገር ይቻላሉ፤ እንደገና መዝሙር 1 ን ይመልከቱ። ለብዙ ሺህ ዓመታት አማኞች በመዝሙር 1 ላይ ያለውን ቃል አንብበው በራሳቸው ላይ ተግባራዊ አድርገውታል። በክርስቶስ የሚያምን ወንድም ሆነ ሴት፣ ክፉ ሰዎችን ለመቃወም ሆነ "ቀንና ሌሊት" በእግዚአብሔር ሕግ ለመደሰት ይጥራል። በክርስቶስ የሚያምን ወንድም ሆነ ሴት፣ በእግዚአብሔር "የተመሰገነ" እና "ፍሬያማ ነው። በክርስቶስ የሚያምን "በፍርድ መቆም" ይችላል፤ ይህም አማኙ "በክርስቶስ" ስለሆነ ነው።

ክርስቲያኖች እሱ ወይም እሷ "በክርስቶስ" በመሆናቸው ምክንያት ከብዙ መዝሙራት ገጸ ባህሪ ጋር በትክክል ሊመሳሰሉ ይችላሉ። እንደገናም ይህ የእግዚአብሔር ሰዎች ለሺህ ዓመታት፣ መዝሙረ ዳዊትን ከራሳቸው ጋር እንደ ርዕሰ ጉዳይ ያነበቡት ለምን እንደሆነ ያብራራል። ክርስቲያኖች ከክርስቶስ ጋር ተመሳስለዋል። የክርስቶስ ሕይወት የክርስቲያኖች ሕይወት ነውና። ይህንንም ሐዋሪያው ጳውሎስ በ **ሮሜ 6፡1–11**፣ **ኤፌሶን 2፡4–6**፣ **ቆላስይስ 3፡1–4** እና በሌሎችም ብዙ ቦታዎች ላይ ያስረዳል። ክርስቲያን "በክርስቶስ" ስለሆነ ስለ ክርስቶስ እውነት የሆኑት ነገሮች በእርግጥም ስለ ክርስቲያን ሊነገሩ ይችላሉ።

ስለዚህ በወንጌል ክስተት ምክንያት፣ ሐዋሪያት ለክርስቶስ ልዩ የሆኑ ነገሮች ወስደው "በክርስቶስ" ላሉት ተግባራዊ ያደርጋሉ። ይህም ማለት ስለ ክርስቶስ በልዩ ሁኔታ የሚነገሩ መዝሙራት ስለ ቅዱሳን ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ ማለት ነው። ለምሳሌ በመዝሙር 2 ላይ ክርስቶስ የእግዚአብሔር "ልጅ" ተብሎ ተጠርቷል። መዝሙር 2 ብዙውን ጊዜ የተጠቀሰው ስለ ክርስቶስ ብቻ ነው። ስለ ኢየሱስ የሚናገር መዝሙር ነውና።

ይሁን እንጂ መዝሙር 2 አብዛኛውን ጊዜ በኢየሱስ ክርስቶስ ያተኮረ ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ ስለ ቅዱሳን ጉዳይም በማጣቀስ ጠጠቅሷል። በኢየሱስ ሕይወት፣ ሞትና ትንሣኤ ምክንያት ኢየሱስ ብቸኛው "የእግዚአብሔር ልጅ" አይደለም፤ ምክንያቱም ብዙ "ልጆችን ወደ ክብር" አምጥቷል ( **ዕብራውያን 2፡10** እና **ሮሜ 8፡14** ይመልከቱ)። ለዚህም ይመስላል በኋላ ጸሐፊዎች በመዝሙረዳዊት ምዕራፍ 2 ላይ ስለክርስቶስ የተነገረውን ጥቅሶች ወስደው ከቅዱሳን ጋር መተግበር የቻሉት። ለምሳሌ፡- **መዝሙር 2፡9** የሚመለከተው ክርስቶስን ነው፤ ሆኖም በ**ራእይ 12** እና **እራይ** 19፡**15**። በሌላ በኩል ደግሞ በ**ራእይ 2፡26–27** ይህ ጥቅስ ቅዱሳንን በሚመለከት ተጠቅሷል! **መዝሙር 2፡7** ክርስቶስን የሚመለከት ሌላው ጥቅስ

ነው። ሆኖም ሐዋሪያው ዮሐንስ በ **ራእይ 21፡7** ላይ ቅዱሳንን በተመለከተ ይጠቀምበታል። ማስታውስ ያለብን ነገር ቢኖር በኢየሱስ ሕይወት፣ ሞትና፣ ትንሣኤ አማኝ በእርግጥ ከክርስቶስ ጋር ተመሳስሏል። ለዚህም ነው እንግዲህ መዝሙረ ዳዊት ስለ ክርስቶስና በክርስቶስ ለሚያምኑ ሰዎች ጥቅም ላይ ሊውል የቻለው።

ስለዚህ መዝሙረ ዳዊት በእነዚህ ሁለት መንገዶች ብቻ ማንበብ የተለመደ ነው። ለምሳሌ ሰዎች ብዙውን ጊዜ ዳዊት በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ ዋና ገፀ ባህሪ እንደሆነ አድርገው ያስባሉ። ስለኢየሱስ ክርስቶስ ያተኮረው ጢቂት ስለ ኢየሱስ በሚያስተምሩ መዝሙራት ላይ ነው። ሐዋሪያት ደግሞ መዝሙረ ዳዊትን የተጠቀሙት በዚህ መንገድ አይደለም።ነገር ግን ስለ ክርስቶስ ለመናገር ወይም ለመጻፍ ደጋግመው መዝሙረ ዳዊትን ተጠቅመዋል። በእርግጥ እውነት ነው ዳዊት በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ ዋና ገፀ ባህሪ ነው፤ ሆኖም እሱ ዋና ገፀ ባህሪ የሆነው "በክርስቶስ" ስለሆነ ብቻ ነው። እርሱ ከቅዱሳን አንዱ ነው። ዳዊት ከቅዱሳን አንዱ ስለሆነ መዝሙራት በእሱ ላይ ሊተገበር የቻለው። ሆኖም በመዝሙራት ውስጥ እንደ ዋና ገፀ ባህሪ ክርስቶስ መሆኑን ችላ ማለት የለብንም። በተጨማሪም በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ እንደ ዋና ገፀ ባህሪ ቅዱሳን መሆናቸውን ችላ ማለት የለብንም። ሁለቱም እውነት ናቸው! አማኞች በተለይም ሰባኪዎችና አስተማሪዎች መዝሙረ ዳዊትን እንዴት መጠቅም እንደሚችሉ ለመማር በሁለቱም "ርዕሰ ጉዳዮች" ላይ ትኩረት መስጠት አስፈላጊ ነው።

ለምሳሌ፡- ሰባኪ ወይም አስተማሪ መዝሙር 1ን እንዴት እንደሚጠቀም ተመልከት። ሰባኪው ኢየሱስ "ምስጉን ሰው" በሚለው ላይ ሊያተኩር ይችላል። ሰባኪው በኢየሱስ ሕይወት ኃጢአት ያልሠራ ብቸኛው ሰው እና በእግዚአብሔርም ሕግ ላይ ቀንና ሌሊት በትክክል ያሰላስል የነበረው እሱ ብቻ መሆኑን በማተኮር ሊያከብረው ይችላል። ሰባኪው በውሃ ዳር እንደተተከለ ፍሬያማ ዛፍን አስመልክቶ በመናገር በክርስቶስ ፍሬያማነት ላይ ማተኮር ይችላል። ወይም ደግሞ ሰባኪው መዝሙር 1ን በጌታ ኢየሱስ ከሚያምኑቱ ጋር በማዛመድ ሊጠቀምበት ይችላል። ሰባኪው አማኞችን ከክፍ እንዲመለሱና የእግዚአብሔርን ሕግ ቀንና ሌሊት እዲያሰላስሉ ሊጠራቸው ይችላል። እንደዚሁም በክርስቶስ ስላሉት አማኞች ፍሬያማነት ሊናገር ይችላል።

በተጨማሪም ሰባኪው መዝሙር 3ን እንዴት ሊጠቀም እንደሚችል እንመልከት። ይህ መዝሙር መከራ ስለሚቀበል ስለ አንድ ንጹሕ ሰው ነው የሚናገረው። ይህ ሰው እግዚአብሔር እንዲያድነው ይጣራል። እግዚአብሔር ደግሞ የዚህ ንጹሕ ሰው ጽሎት ሰምቶ ምላሽ በመስጠት "ይታደገዋል"። የሚጸልይ ሰው እግዚአብሔር ጠላቶቹን ሁሉ እንደሚያጠፋ ያውቃል። በክፉዎች ላይ ፍርድ ያመጣል። ሰባኪው እነዚህን ሁሉ ነገሮች በማጤን በጌታ ኢየሱስ መከራ ላይ ሊያተኩር ይችላል። ኢየሱስ

ከማንኛውም ከመቼውም ጊዜ በላይ ከኖሩት ሰዎች ሁሉ በላይ በክፉ ሰዎች እጅ መከራ ተቀብሏል። እግዚአብሔር ከጠላቶቹ እንዲያድነው ለምኖ ከጠላቶቹም አድኖታል።

ነገር ግን ሰባኪው ይህንኑ መዝሙር ተጠቅሞ ስለአማኞች ሊናገር ይችላል። በእውነትም በክርስቶስ ያሉትን አማኞች ሁሉ ይሰደዳሉና (**2 ጢሞቴዎስ 3፥12** ይመልከቱ)። በተመሳሳይ እግዚአብሔር ክርስቶስን "ባንቀላፋ" ጊዜ ደግፎታል (ይህ ምናልባት ሞቱን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል!) ስለዚህ "በክርስቶስ ያሉትንም" ሁሉ ይደግፋል ማለት ነው። እንደ ክርስቶስም ሲያንቀላፉ ይጠብቃቸዋል። ይህ በእረግጥም እግዚአብሔር ቅዱሳንን በአስጨናቂ ወቅት እንኳን ሲያንቀላፉ እነደሚጠብቃቸው የሚያመልክት ነው። እግዚአብሔር ሕዝቡን እጅግ በጣም ጨለማ በሆነበት ዘመን እንኳን ማዳን ይችላል። እደዚሁም እግዚአብሔር ቅዱሳኑን በሞት ጊዜ እንኳን ቢሆን እንደሚጠብቅ ቅኔአዊ ገለጻ ሊሆን ይችላል (ለምሳሌ የእስጢፋኖስ ሞት በ**ሐዋሪያት ሥራ 7፥60** እንዴት እነደተገለጸ ይመልከቱ)። ስለዚህ ሰባኪው ወይም አስተማሪው በዚህ መዝሙር ምእመናንን ማስተማር እና ማበረታታት መቻል አለበት።


በ**መዝሙር 8** ላይ ያለው "የሰው ልጅ" ማን ነው? ሰባኪው እርሱ ክርስቶስ መሆኑን መግለጽ አለበት። ይህ አዲስ ኪዳን ውስጥ በግልጽ ተመልክቷል። ይሁን እንጂ መዝሙረ ዳዊትን ለማንበብ ግን ይህን መንገድ ብቻ በቂ አይደለም። ሰባኪው "የሰው ልጅ" ደግሞ የእግዚአብሔር ሕዝብ መሆኑን ማወቅና ማወጅ አለበት። በቤተክርስቲያን ላሉት ይህን ማሳየት አስፈላጊ ነው። ይህም በቤተክርስቲያን ያሉትን በእግዚአብሔር አጽናፈ አለም ውስጥ ያላቸውን ጠቃሚ ሚና ያስታውሳቸዋል! የዚህ መዝሙር ሁለቱም ገጽታዎች በ**ዕብራውያን 2፥1–13** ውስጥ ሊታዩ ይችላሉ።


ሰባኪው በ**መዝሙር 23** ላይ የሚናገረው ክርስቶስ ስለመሆኑ ላይ ሊያተኩር ይችላል። ይሁን እንጂ ሰባኪው መዝሙር 23 የሚናገረው "በክርስቶስ" ስላሉት መሆኑን ማስገንዘብ ይኖርበታል።

መዝሙረ ዳዊት ለምን በዚህ መንገድ ተጻፈ? ለምንድር ነው በክርስቶስና በአማኞች ላይ የሚያተኩረው? ለዚህ ጥያቄ በዙ መልሶች አሉ።

መዝሙረ ዳዊት በክርስቶስ ላይ በማተኮር አማኞች የክርስቶስ ሕይወትና ሞት እንዲያስታውሱ ያድረጋል። የክርስቶስን መከራ "እንዲሰማን" ያደርጋል፣ ኢየሱስ ሰው እንደነበረ እንድናስታውስ ያደርገናል፣ በስደት ወቅት እርሱ እንዴት እንደጸለየ ያሳየናል፣ እንደዚሁም ደግሞ የክርስቶስን ጽድቅ ያስታውሰናል። መዝሙረ ዳዊት በክርስቶስ ላይ በማተኮር እግዚአብሔር ከመከራው ሁሉ እንዴት እንዳዳነው በማየት እንድንደሰት ያስችለናል። በመዝሙረ ዳዊት ስለ መዳናችን ታሪክ እናነባለን! መዝሙረ ዳዊት በዚህ መንገድ ማንበቡ የዚህ ዘመን አማኞችም ቢሆን በክርስቶስ ላይ እንዲያተኩሩ እና በሥራውና በፍሬያመነቱ ላይ እንዲድሰቱ ይረዳቸዋል።

እንደሚሰቃዩ ያሳየናል። መዝሙረ ዳዊት እንድንጸልይ ያሳስበናል። አንዳንድ ጊዜ በእምነታችን ግራ ስንጋባና ስንጠራጠር፤ ጥርጣሬን በመጋፈጥ በእምነት ወደ እግዚአብሔር መዞር እንዳለብን ያሳስበናል። ወደ መድኃኒታችን ወደ እግዚአብሔር ዘንድ እንድንመልከት ያበረታታናል።





## 16. መጽሐፈ ኢዮብ ለእግዚአብሔር ሕዝቦች ስለ እግዚአብሔርና ስለእግዚአብሔር ጥበብ ያስተምራል።

በብሉይ ኪዳን ሁሉም መጻሕፍት በጥበብ የተሞሉ እና "በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን ለመዳን ጥበበኞች ሊያደርጉ የሚችሉ" (**2 ጢሞቴዎስ 3፡15** ይመልከቱ)፤ ሲሆኑ በተለይም ከጥበብ ጋር የተያያዙ አምስት መጻሕፍት ደግሞ አሉ። አምስቱ "የጥበብ" መጻሕፍት መዝሙረ ዳዊት፣ ኢዮብ፣ ምሳሌ፣ መክብብ እና መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን ናቸው። እነዚህ አምስቱ መጻሕፍት በአንድ ላይ በጽሑፎች ውስጥ ተካተዋል። እነዚህ መጻሕፍት እያንዳንዳቸው በዚህ ዘምን ስለ ሕይወት ጥበብ ለአንባቢ ያስተምራሉ። እያንዳንዱ መጽሐፍ ስለ ጥበብ ከተለያየ አቅጣጫ ያስተምራሉ።

በእነዚህ አምስቱ የጥበብ መጻሕፍት ውስጥ የተሰጠው የጠበብ ትምህርት እግዚአብሔር በፀጋው ያደረገው ነጻ ስጦታ ነው። የመዝሙር፣ የኢዮብ፣ የምሳሌ፣ መክብብ እና መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን የጥበብ መጻሕፍት እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመርዳት ያደረገው "የፀጋ መንገዶች" ናቸው። እነዚህ መጻሕፍት በአሁኑ ዘመን ባለው መከራና ክፋት በእግዚአብሔር ፊት በመልካም እንዲኖሩ ለእግዚአብሔር ሕዝቦች ጥበብን ይሰጣሉ።

አምስቱም የጥበብ መጻሕፍት የሚያተኩሩት በዚህ ዘመን በጥበብ ለመኖር የእግዚአብሔር ሕዝብ ማወቅ በሚያስፈልጋቸው በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ነው። በሌላ አነጋገር ምንም እንኳን ደራሲው ፈጽሞ **ባይናገርም** "በኢዮብ ውስጥ የተሰጠው የጥበብ ትምህርት ሰዎች ስለ እግዚአብሔር በዚህ መንገድ ሊያስቡበት ይገባል" የሚል ነው። ነገር ግን ደራሲው "ሰዎች በኢዮብ ውስጥ በተሰጠው የጥበብ ትምህርት ልዩ መንገድ መንቀሳቀስ አለባቸው" ብሎ አይናገርም። ይሁን እንጂ ደራሲው ጥበቡ ምን እንደሆነ ለአንባቢ ከመናገር ይልቅ ጥበቡ ምን እንደሆነ ለአንባቢው በተግባር **ያሳያል**።

ደራሲው ስለ እግዚአብሔር እና ድርጊቶቹ የተለያዩ ሰዎች ሲናገሩ አንባቢው "እንዲያደምጥ" በማድረግ በኢዮብ ውስጥ እየተማረ ያለውን እውነተኛ ጥበብ ለአንባቢ **ያሳያል**። አንባቢው ኢዮብ ስለ እግዚአብሔርና ድርጊቶቹ ሲናገር "ያዳምጣል"። እንደዚሁም አንባቢው የኢዮብ ሚስት ስለ እግዚአብሔርና ድርጊቶቹ ስትናገር ያዳምጣል። ደግሞም አንባቢው ኤልሁ የሚባል አንድ ወጣት ስለ እግዚአብሔርና ሥራዎች ሲናገር ያዳምጣል። በእነዚህ ሁሉ ንግግሮች ውስጥ ሰዎች የሚናገሩት እግዚአብሔርና እርሱ የሚያደርገውን ለምን እንደሆነ ነው። እነዚህ ሰዎች ኢዮብ ምን ማድረግ እንዳለበት እየነገሩት ነው።

ምንም እንኳን ሰው ሁሉ ስለ እርሱ ቢናገር እግዚአብሔር ግን በዝምታ ላይ ነበር። አንባቢው በኢዮብ ምዕራፍ 1 እና 2 ያለውን የእግዚአብሔር ቃል ያዳምጣል። እነዚህ ሁለት የመጀምሪያ ምዕራፎች አንባቢው በኢዮብ መጽሐፍ ውስጥ የተናገሩት ሰዎች ሁሉ እውቀት እንደ ጎደላቸው እንዲረዳ ያስችሉታል። ነገሮች ለምን እንደ ሚከሰቱ በቀላሉ መረዳት አይቻልም፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ያውቃል። ሆኖም እግዚአብሔር በኢዮብ ጉዳይ ዝም ሲል እንመለከታለን። መጽሐፉ በዚህ ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔር በሚያደርገው ወይም በሚያስብበት ጉዳይ ላይ አያተኩርም። ከዚህ ይልቅ አንባቢው ሌሎች ሰዎች ስለ እግዚአብሔርና ኢዮብ ሊያደርጋቸው ስለሚገቡ ነገሮች ሲናገሩ “ያዳምጣል”። የኢዮብ ወዳጆች ብዙ እውነትነት ያላቸው ነገሮች ቢናገሩም እውቀታቸው ግን ሙሉ አልነበርም። የኢዮብ ወዳጆች እግዚአብሔር ስላልሆኑ ሁሉንም አያውቁም ነበርና። እግዚአብሔር ኢዮብን ለምን መከራ መቀበል እንዳስፈለገው እንደፈቀደ አንዳቸውም አልተረዱም ነበር። ስለሰው ጥበብ በኢዮብ ምዕራፍ 3–37 ላይ ተጽፎ ይገኛል። በዙ ጠቃሚ የሆነ ነገር ቢኖረውም ነገር ግን ሙሉ አይደለም። ሰዎች በቀላሉ እግዚአብሔር የሚያውቀውን ተመሳሳይ ነገር ማወቅ አይችሉም። በተለይም እግዚአብሔር ዓላማውን ከሰዎች ለመሰወር ከመረጠ አንድም ነገር ለምን እንደሚከሰት በትክክል ለማወቅ አስቸጋሪ ነው።

በመጨረሻም በዙ ሰዎች ከተናገሩ በኋላና ከእነዚህም የተለያዩ ሰዎች ብዙ የተለያዩ ነገሮች ከተሰሙ በኋላ (ሁሉም በግጥም መልክ) እግዚአብሔር በኢዮብ ምዕራፍ 38–41 ስለ ራሱ ይናገራል። በዚህ በኢዮብ ምዕራፍ 38–41 ያለው የእግዚአብሔር ቃል በጣም አስገራሚ ነው። ኢዮብ ስለ እግዚአብሔር የተነሱት ጥያቄዎች ለአንዱንም መልስ አልሰጠም ነበር። ከዚህ ይልቅ ኢዮብ ጥያቄዎችን ይጠይቅ ነበር።

*እግዚአብሔርም በአውሎ ነፋስ ውስጥ ሆኖ ለኢዮብ መለሰ እንዲህም አለ።*
*ያለ እውቀት በሚነገር ቃል ምክርን የሚያጨልም ይህ ማን ነው?*
*እንግዲህ እንደ ሰው ወገብህን ታጠቅ፤*
*እጠይቅሃለሁ አንተም ተናገረኝ።*
*ምድርን በመሰረትሁ ጊዜ አንተ ወዴት ነበርህ?*
*ታስተውል እንደሆን ተናገር።* **ኢዮብ 38፡1–4**

በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ኢዮብ የሚሰቃይበትን ምክንያት እግዚአብሔር በፍጹም አልገለጸም። እንዳውም እስከነ ጭራሹ በኢዮብ መጽሐፍ ውስጥ ኢዮብ ለምን መከራ እንደ ድረሰበት አልተነገረም። እግዚአብሔር ሰይጣን ኢዮብን እንዲፈትነው የፈቀደው የእግዚአብሔርን ታላቅነት እና ኢዮብ

ለእግዚአብሔር ያለውን ፍቅር እውነታ ለማሳየት እንደሆነ ፍጽሞ አልነገረውም። ለምን እንደ ሆነ አሁን አንባቢው ያውቃል ነገር ግን በወቅቱ ለኢዮብ ይህ መረጃ አልተነገረውም ነበር። በግልጽ ለመረዳት እንደሚቻለው እግዚአብሔር ይህን መረጃ ማወቁ ለኢዮብ አስፈላጊ ነው ብሎ ያሳብም ነበር ማለት ነው። ማለትም በምድር ላይ እግዚአብሔርን በመምሰል ለመኖር ይህን መረጃ ለኢዮብ አያስፈልገውም ነበር።

እንግዲህ ኢዮብ መከራው ለምን እንደሆነ መርጃ የማያስፈልገው ከሆነ ምን ሊያስፈልገው ይችላል? ኢዮብ ማወቅ የነበረበት ስለእግዚአብሔር ታላቅነት፣ ስለ እግዚአብሔር ጥበብ፣ ስለ እግዚአብሔር ፈጥራ፣ እና እግዚአብሔር በነገር ሁሉ ስላለው የበላይነትና እውነተኛ እውቀት ነበር። ደግሞም ኢዮብ ስለራሱ ድክመት፣ ስለ ራሱ ኃይል ውስንነት እና ስለ ራሱ እውቀት ማነስ እውነተኛ ግንዛቤ ያስፈልገው ነበር። እግዚአብሔር ግን ስለኢዮብ ሁሉንም ነገር ያውቃል። ኢዮብ ከምዕራፍ 38–41 ባለው ይህንን ጥበብ ከእግዚአብሔር ተምሯል።

ኢዮብ እግዚአብሔርን ሲሰማ ጥበብን ያገኛል። ኢዮብም ራሱ የተማረውን ትምህርት በ**ኢዮብ 42፡2–6** ባለው ክፍል ጠቅለል አድርጎ ገልጿል። ኢዮብ ከተሞክሮ የተማረው ይህ ጥበብ ነው። የተማረውንም ትምህርት በሚከተለው መልኩ አጠቃሎታል።

***ኢዮብም መለሰ እግዚአብሔርንም አለው።***

***ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደ ሆንህ አሳብህም ይከለከል ዘንድ ከቶ እንደማይቻል አወቅሁ።***

*ያለ ዕውቀት ምክርን የሚሰውር ማን ነው?*

*ስለዚህ እኔ የማላስተውለውን፣ የማላውቀውንም ድንቅ ነገር ተናግሬያለሁ።*

*እባክህ ስማኝ እኔም ልናገር፤ እጠይቅህማለሁ አንተም ተናገረኝ።*

*መስማትስ በጆሮ በመስማት ሰምቼ ነበር፤*

*አሁን ግን ዓይኔ አየችህ፤*

*ስለዚህ ራሴን እንቃለሁ፤*

*በአፈርምና በአመድ ላይ ተቀምጬ እጸጸታለሁ።*

ኢዮብ ከእግዚአብሔር ጋር ምንም ሊነጻጸር የማይችል እውቀት እንዳለው ተማረ። ደግሞም ኢዮብ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ማድረግ እንደሚችል ሃሳቡንም ማንም መከለክል እንደማይችል ተረዳ። ኢዮብ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር ሲያንጻጽር ምንም እንዳልሆነ ተገነዘበ።

በመጽሐፈ ኢዮብ ላይ ስለ እግዚአብሔርና ስለ ታላቅነቱ የተነገርው ጥበብ በዚህ ዘመን ሰዎች ላይ የሚሠራው እንዴት ነው? መጽሐፈ ኢዮብ የእምነት ሰዎች ልክ እንደ ኢዮብም ከእግዚአብሔር የተለዩ

መሆናቸውን ያስተምራል። እንደ ኢዮብ ያሉ የእግዚአብሔር ሕዝቦች እግዚአብሔር ሁሉን እንደ ሚያውቅና ከሁሉ በላይ እንደሆነ ማወቅ አለባቸው። ክርስቲያን በመጽሐፈ ኢዮብ የተገለጠው "ጥበብ" ማወቅና በእርሱም መደሰት አለበት። ክርስቲያኖችም ቢሆኑ ምን እየተከሰተ እንዳለ ወይም ለምን እየሆነ እንዳለ የማያውቋቸው ሁኔታዎች እንደሚኖሩ ማውቅ አለባቸው። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሊናገረው የማይፈልጋቸው ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ። ኢዮብም ያጋጠመው ይኸው ነበር። እግዚአብሔር ኢዮብ መከራ እንዲቀበል የፈቀደው ለምን እንደሆነ አላወቀም ነበር። እግዚአብሔር በተለየ መንገድ ኢዮብ እንዲሰቃይ ፈቀደ (ለዚህም ምክንያቱ በኢዮብ ምዕራፍ 1 እና 2 ለአንባቢው ተብራርቶለታል) ነገር ግን እግዚአብሔር ለምን ይህን እያደረገ እነደነበር ለኢዮብ ሊገልጽለት አላስፈለገውም። ስለዚህ አንዱ የጥበብ ክፍል ስለ እግዚአብሔር እና አለ እግዚአብሔር ድርጊቶች የማናውቃቸው ነግሮች እንዳሉ ማወቅ ነው። በዚህ እውቀት ውስጥ "ማረፍ" መቻል አለብን።

ሙሴም ስለእግዚአብሔር "ምስጢራዊ ነገሮች" በሚከተለው መንገድ ተናግሯል።

*"ምስጢሩ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው፤ የተገለጠው ግን የዚህን ሕግ ቃሎች እናደርግ ዘንድ ለእኛ ለዘላለም ለልጆቻችን ነው።"* **ዘዳግም 29፡29**

የዚህ ዘመን ክርስቲያኖች እንደ መሆናችን መጠን በሕይወታችን ውስጥ ያልተረዳናቸው ነገሮች እንደሚኖሩ ማወቅ አለብን። በእንደዚህም ዓይነት ጊዜ የኢዮብን ጥበብ ማስታወስ አለብን።

*"ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደ ሆንህ*
*አሳብህም ይከለከል ዘንድ ከቶ እንደማይቻል አወቅሁ።*
*ያለ ዕውቀት ምክርን የሚሰውር ማን ነው?*
*ስለዚህ እኔ የማላስተውለውን፣ የማላውቀውንም ድንቅ ነገር ተናግሬያልሁ።*
*እባክህ ስማኝ እኔም ልናገር፤ እጠይቅህማለሁ አንተም ተናገረኝ።*
*መስማትስ በጆሮ በመስማት ሰምቼ ነበር፤*
*አሁን ግን ዓይኔ አየችህ፤*
*ስለዚህ ራሴን እንቃለሁ፤*
*በአፈርምና በአመድ ላይ ተቀምጬ እጸጸታለሁ።"*

በመጽሐፈ ኢዮብ ውስጥ ከሚገኘው የጥበብ ትምህርቶች በተጨማሪ መጽሐፈ ኢዮብ ክርስቲያኖች ሊጠቀሙባቸው የሚችሉባቸው ሌሎች መንገዶችም አሉ።

1. ይህ መጽሐፍ አማኞችን የክርስቶስን መከራ እና ነጻ መውጣት ለማስታወስ ጥቅም ላይ መዋል አለበት። ስለ ክርስቶስ ስቃይ፣ ሞት እና ትንሳኤ ማሰብ ወደ ኢየሱስ ክብር እና ምስጋና ይመራል። ኢዮብ የክርስቶስ **ምሳሌ** ነው። በንጉሥ ሥዕላዊ አምሳል ቀርቧል። እንደዚሁም እንደካህን አምሳያ ነው። እንደካህን በየዕለቱ ስለልጆቹ የሚማልድ ጻድቅ ሰው ነበር። ኢዮብ መከራ ተቀብሏል ነገር ግን መከራ የተቀበለው በኃጢአቱ ምክንያት እንዳልሆነ ልብ ሊባል ይገባል። መከራ የተቀበለው እግዚአብሔር ለራሱ ዓላማ ሲል መከራ እንዲቀበል ስለፈቀደ ነው። እግዚአብሔር ኢዮብ ፈተናውን እንደሚያልፍ እያወቀ እንዲሰቃይ ፈቀደ። እግዚአብሔር አድኖታል ካዳነውም በኋላ ከበፊቱ የበለጠ አድርጎለታል። ኢዮብ ነጻ ከውጣም በኋላ ካህን ሆኖ አገልግሏል። ወዳጆቹ በሕይወት እንዲኖሩ ስለወዳጆቹ ማልደ
ል። ኢዮብ ይህን ባያደርግ ኖሮ ይሞቱ ነበር። በእነዚህ ሁሉ መንግዶች ኢዮብ ክርስቶስን ይመስላል። ሕይወቱ የክርስቶስን ሕይወት ትንሽ “ጥላ” ነው። ኢዮብ ክርስቶስን እንዴት እንደሚመስል መመርመሩ ትልቅ ጥቅም አለው። ሰባኪዎች በውነት በኢዮብ መጽሐፍ ወንጌልን ሊሰብኩ ይችላሉ።


2. ምክንያቱም አማኞች “በክርስቶስ” ስለሆኑ “ኢዮብ ደግሞ” የአማኝ “ምሳሌ” ነው። አማኞች በክርስቶስ ጻድቃን ቢሆኑም በዚህ ዓለም ሲኖሩ በሰይጣን እጅ መከራ ሊቀበሉ ይችላሉ። ነገር ግን አማኞች እስከ መጨረሻው መጽናት ይኖርባቸዋል። እንደ ኢዮብም በመጽናታቸው ታላቅ ሽልማት ይቀበላሉና። አማኞች እንደ ኢዮብም ንጉሥና ካህን ናቸው (**ራእይ 1፡6** ይመልከቱ)። ስለሆነም ኢዮብ እንደ አማኝ ነው። የኢዮብ ሕይወት በአማኝ ሕይወት ሊገለጥ የሚገባውን ምሳሌ ያስተላልፋል (**ያዕቆብ 5፡11** ይመልከቱ)። ኢዮብ በመከራም ቢሆን የጸና ነበር። ስለዚህ አማኞች ከኢዮብ በመከራ መጽናት መማር አለባቸው።


3. የኢዮብ ሦስቱ ጓደኞችና የኢዮብ ሚስት አማኞች ሊከተሉዋቸው የማይገባ ምሳሌዎች ናቸው! ስለእግዚአብሔር ስንናገርና ሊሎች ሰዎች ደግሞ እንዲጸኑ እንዴት እንደምናበረታታ መጠንቀቅ አለብን። ስለእግዚአብሔር የምንናገራቸው ቃላት ትክክል መሆናቸውን ማረጋገጥ አለብን (**ኢዮብ 42፡7** ይመልከቱ)። ሰዎችን በተሳሳተ ጥበብ መምራት የለብንም።

4. ሰይጣን ኃይለኛ ነው። ይህም በኢዮብ ሕይወት ውስጥ ታይያል። ሆኖም የኢዮብ መጽሐፍ አማኞችን ያበረታታል ማለትም ሰይጣን በእግዚአብሔር ሥልጣን ሥር መሆኑን እና እግዚአብሔር

ካልፈቀደለት ምንም ማድረግ የማይችል መሆኑን ያስገነዝባል። ይህም ለቅዱሳን ታላቅ ማበረታቻ ማምጣት አለበት ምክንያቱም እግዚአብሔር መልካምና አፍቃሪ አምላክ ነውና።

5. የኢዮብ መጽሐፍ ለሚጸኑ ቅዱሳን ታላቅ ሽልማት እንዳለ ያስተምራል። ለቅዱሳን የተባለውን ተስፋ የሚወርሱት እነዛ ድል የሚነሱት ብቻ ናቸው (ራእይ 2፡7፤ 2፡10–11፣ 2፡17፣ 2፡26፤ 3፡5–6፣ እና 3፡21–22)





## 17. መጽሐፍ ምሳሌ በተሳሳተ “መንገድ” እንዳይሄዱና ትክክለኛውን “መንገድ” እንዲከትሉ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ጥበብን ያስተምራል

በብሉይ ኪዳን ያሉት ሁሉም መጻሕፍት በጥበብ የተሞሉ እና “ክርስቶስ በማመን መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡ የሚችሉ” (**2 ጢሞቴዎስ 3፡15**) ሲሆኑ፤ በተለይም ደግሞ ከጥበብ ጋር የተያያዙ አምስት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አሉ። እነዚህም የጥበብ መጻሕፍት መዝሙረ ዳዊት፣ ኢዮብ፣ ምሳሌ፣ መክብብ እና መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን ናቸው። እነዚህም አምስቱ መጻሕፍት በአንድ ላይ በጽሑፎች ውስጥ ይገኛሉ። እነዚህም መጻሕፍት እያንዳንዳቸው የእግዚአብሔር ሕዝብ በሚያስፈልገው የጥበብ ዘርፍ ላይ ያተኩራሉ።

በእነዚህ አምስቱ የጥበብ መጽሐፍ ውስጥ የተሰጠው ትምህርት የእግዚአብሔር ቸር ስጦታ ነው። በመዝሙር፣ ኢዮብ፣ ምሳሌ፣ መክብብ እና መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን የጥበብ መጻሕፍት እግዚአብሔር በዚህ መከራና ክፋት በበዛበት ዘመን ሕዝቡ ቅዱስና ፍሬያማ ሕይወት እንዲኖር የረዳበት “የቸርነቱ መንገዶች” ናቸው።

በሁለተኛው የጥበብ መጽሐፍ (ኢዮብ) እና በሦስተኛው የጥበብ መጽሐፍ (ምሳሌ) መካከል ትልቅ ልዩነት አለ። ቀደም ሲል እንደተገለጸው የኢዮብ ጸሐፊ በመጽሐፉ ውስጥ የተማረውን ጥበብ ለአንባቢው **አይናገርም**። ይልቁንም ደራሲው እየተማረ ያለውን ተግባራዊ ጥበብ ለአንባቢ **ያሳያል**። ይህንንም የሚያደርገው በብዙ ግጥሞች ነው። በኢዮብ ውስጥ እየተማረ ያለውን ጥበብ ለመወሰን አንባቢው ግጥሞቹን እና የኢዮብን የመጨረሻ ቃላት ማንበብ ያስፈልገዋል።

የመጽሐፈ ምሳሌ ጸሐፊ ግን እየተማረ ያለውን ጥበብ ለአንባቢ ይነግራል። በመጽሐፉም መጀመሪያ ላይ ደራሲው መጽሐፉ ለሚያነቡት ሰዎች ጥበብን ለማስተማር ያለመ እንደሆነ በግልጽ ተናግሯል።

*የእሥራኤል ንጉሥ የዳዊት ልጅ የሰሎሞን ምሳሌዎች፤*

*ጥበብንና ተግሣጽን ለማወቅ*

*የእውቀትንም ቃል ለማስተዋል፤*

*የጥበብን ትምህርት ጽድቅንና*

*ፍርድን ቅንነትንም ለመቀበል፤*

*ብልሃትን ለአላዋቂዎች ይሰጥ ዘንድ*

*ለጎበዛዝትም እውቀትንና ጥንቃቄን፤*

*ጠቢብ እነዚህን ከመስማት ጥበብን ይጨምራል፤*

*አስተዋይም መልካም ምክርን ገንዘቡ ያደርጋል።*

*ምሳሌንና ትርጓሜን የጠቢባንን*

*ቃልና የተሸሸገውን ነገር ለማስተዋል።* **ምሳሌ 1፡1–6**

የመጽሐፉን ዓላማ ከሚገልጹት ከእነዚህ የመጀመሪያዎቹ ስድስት ጥቅሶች በኋላ ደራሲው ጥበብን ማስተማር ጀመረ። መጽሐፉ “እግዚአብሔርን መፍራት” የጥበብ መጀመሪያ እንደሆነ በማወጅ ይጀምራል።

*“የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፤*

*ሰነፎች ግን ጥበብንና ተግሣጽን ይንቃሉ።”* **ምሳሌ 1፡7**

ስለ እግዚአብሔርን መፍራት ይህን ጥቅስ በማስቀመጥ በመጀመሪያ ጸሐፊው የጥበብ መመሪያዎችን መማር እና በእነዚያም ሕጎች ለመኖር መሞከር ብቻውን ጥበበኛ ሰው ለመሆን በቂ እንዳልሆነ በግልጽ አሳይቷል። ብልሕ ሰው እግዚአብሔርን ይፈራል ይላል። ያ የጥበብ ሁሉ መነሻ ነው።

ስለዚህ እግዚአብሔርን መፍራት ማለት ጠቢብ ሰው እግዚአብሔር ማን እንደሆነ ያውቃል፣ ስለ እግዚአብሔር ያስባል፣ እግዚአብሔርን ይወዳል፣ በእግዚአብሔር ያምነ እና እግዚአብሔር የሚለውን ያደርጋል ማለት ነው። ሰው እግዚአብሔርን የማይፈራ ከሆነ ያ ሰው በእውነት ጥበበኛ ተብሎ ሊጠራ አይችልም።

ስለ እግዚአብሔርን መፍራት የተነገረው በምሳሌ መጀመሪያ ላይ ብቻ አይደለም። እንዳውም በመጽሐፈ ምሳሌ ውስጥ እግዚአብሔርን መፍራት ዋንኛ ጭብጥ ነው። እግዚአብሔርን መፍራት በ**ምሳሌ 1፡29፣ 3፡7፣ 8፡13፣ 9፡10፣ 10፡27፣ 14፡26–27፣ 15፡16፣ 15፡33፣ 16፡6፣ 19፡23፣ 22፡4፣ 23፡17** እና **29፡25** ላይ ይናገራል።

የምሳሌ ዋናው “ትንታኔ” የሚጀምረው አባት እና እናት ለልጃቸው በሚሰጡት መመሪያ ነው።

***ልጄ*** *ሆይ* ***የአባትህን*** *ምክር ስማ*

***የእናትህንም*** *ሕግ አትተው፤*

*ለራስህ የሞገስ ዘውድ*

*ለአንገትህም ድሪ ይሆንልሃልና፤* **ምሳሌ 1፡8–9**

ሰሎሞን የአብዛኛው የመጽሐፈ ምሳሌ ደራሲ ነው፣ ስለዚህ ንጉሱ እና ንግስቲቱ በንጉሳዊ ቤተሰብ ውስጥ ላደገው ንጉሣዊ ልጅ የተነገረ ቃል ነው። ይህ አንባቢዎች ሊገነዘቡት የሚያስፈልግ ጽንሰ ሀሳብ ነው። ይህ መጽሐፍ "የንጉሥ ልጆች" የሚኖሩበትን ትክክለኛ መንገድ ይዘረዝራል። ንጉሣዊውን ልጅ በማስተማር ላይ ያለውን ይህ የወላጅ ትኩረት በምሳሌ መጨረሻ ላይም ይታያል። በመጨረሻውም ምዕራፍ ላይ ይህ መጽሐፍ ከንጉሣዊ ወላጆች ለንጉሣዊ ልጆች የተሰጠ ምክር እንደሆነ ተጨማሪ ማስረጃዎች አሉ። ምሳሌ 31፡1–9 ላይ እናቱ ልሙኤል ለተባለ ንጉሥ ያስተማረችውን ስለአንድ "ትረካ" ይዘግባል።

*ልጄ ሆይ ምንድር ነው? የሆዴ ልጅ ሆይ ምንድር ነው?*

*የስለቴ ልጅ ሆይ ምንድር ነው?* **ምሳሌ 31፡2**

የንጉሥ ልሙኤል እናት ለንጉሣዊ ልጇ ስለ ምግባሩ እንዲያስብ እየነገረችው ነው። ምግባሩ አስፈላጊ መሆኑን እያታወሰችው ነው። ንጉሥ ነውና።

***ለነገሥታት አይገባም፤*** *ልሙኤል ሆይ፤*

***ነገሥታት የወይን ጠጅ ይጠጡ*** *ዘንድ አይገባም።*

*መሳፍንትም ብርቱ መጠጥ ወዴት ነው? ይሉ ዘንድ፤*

*እንዳይጠጡና ሕግን እንዳይረሱ*

*የድሀ ልጆችንም ፍርድ እንዳያጎድሉ።* **ምሳሌ 31፡4–5**

የልሙኤል እናት ልሙኤልን እንደ ንጉስ ሊፈጽመው የሚገባ ጠቃሚ ተግባር እንዳለው ታስታውሰዋለች።

*አፍህን ስለ ዲዳው ክፈት፤*

*ተስፋ ስለሌላቸውም ሁሉ ተፋረድ።*

*አፍህን ክፈት በእውነትም ፍረድ፤*

*ለድሃና ለሚስኪን ፍረድ።* **ምሳሌ 31፡8–9**

በዚህ ዘመንም ቢሆን የክርስቶስ ተከታዮች የሆኑቱ በክርስቶስ በመሆናቸው በእውነትም ንጉሣዊ ወንዶችና ሴቶች ልጆች መሆናቸውን ማስታውስ አለባቸው (**1 ጴጥሮስ 2፡5** እና **ራዕይ 1፡6** ይመልከቱ)። በንጉሣዊ ስም ወንዶችንም ሆኑ ሴቶች "የእግዚአብሔር ልጆች" ተብለው ሊጠሩ ይችላሉ።

*በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና።* **ሮሜ 8፡14**

ስለዚህ በመጽሐፈ ምሳሌ ውስጥ የተሰጠው ጥበብ ንጉሣዊ ዓላማ ላላቸው "ለንጉሣውያን ልጆች" ነው። እንደዚሁም የሰሎሞን ልጅ የአባቱንና የእናቱን ቃል መስማት አስፈልጎታል፤ እንደዚሁም ንጉሥ ልሙኤልም የእናቱን ቃል መስማት አስፈልጎታል፤ ስለዚህ አማኞች በመጽሐፈ ምሳሌ ውስጥ የሚገኘውን የሰማዩ አባታችንን ቃል መስማት ይኖርብናል ማለት ነው።

በመጽሐፈ ምሳሌ ላይ ያተኮሩ ብዙ ርዕሰ ጉዳዮች አሉ። በዋናነት መጽሐፈ ምሳሌ የሚያተኩርባቸው ሀሳቦች በሚከተሉት ላይ ነው።

- አንድ ሰው ከገንዘብ ጋር ሊኖረው ስለሚገባ ግኑኝነት
- ጋብቻ
- እውነተኛነት
- ወሲባዊ ንጽሕና
- ቁጣ
- ራስን መግዛት
- ስንፍና
- ጠንክሮ የመሥራት አስፈላጊነት
- ክፋትን የማስወገድ አስፈላጊነት
- ጥበበኛ ጓደኞችን የመምረጥ አስፈላጊነት

እነዚህን ሁሉና ሌሎችም ብዙ ርዕሰ ጉዳዮች በምሳሌ ላይ የሚያተኩሩ ናቸው። ጠቢብ ክርስቲያን እነዚህን ቃላቶች በማንበብ በጥበብ እንዲራመድ እንዲረዳው መሣሪያ አድርጎ ይጠቀምባቸዋል። ክርስቲያን እንደ ሞኝ መኖር የለበትም።


በመጽሐፈ ምሳሌ ውስጥ ሁለት የተለያዩ "መንገዶች" ተጠቅሰዋል። "የጻድቃን መንገድ" እና "የኃጥኣን መንገድ"። "የጻድቃን መንገድ" የአንድ ሰው ሕይወት የሚመራበት መንፈሳዊ አቅጣጫ ነው። ስለዚህ መጽሐፈ ምሳሌ የእግዚአብሔር ተከታዮች "ከክፉዎች መንገድ" እንዲርቁና "በጻድቃን መንገድ እንዲሄዱ ለመርዳት ታስቦ የተጻፈ ነው። እግዚአብሔር የአንድን ሰው ተግባር ወይም ድርጊት እንደ ሚመለከት የሚያሳይ ግልጽ ማስረጃ ስለ ወንድ ወይም ሴት "መንገዶች" የሚገልጹ ጥቅሶች በብዛት ይገኛሉ። **ምሳሌ 1፡15፤ 1፡19፤ 1፡31፤ 2፡8፤ 2፡12–15፤ 2፡20፤ 3፡6፤ 3፡17፤ 3፡23፤ 3፡31፤ 4፡11፤ 4፡14; 4፡19፤ 4፡26፤ 5፡6፤ 5፡8፤ 5፡21፤ 6፡6፤ 6፡23፤ 7፡25፤ 7፡27፤ 8፡2፤ 8፡13፤ 8፡20፤ 8፡32፤ 9፡6፤ 9፡15፤ 10፡9፤ 10፡29፤ 11፡5፤ 11፡20፤ 12፡15፤ 12፡26፤ 13፡6፤ 13፡15፤ 14፡2፤ 14፡8፤ 14፡12፤ 14፡14፤ 15፡9–10፤ 15፡19፤ 16፡ 2፡ 16፡7፤ 16፡9፤ 16፡17፤ 16፡25፤ 16፡29፤ 17፡23፤ 19፡2–3፤ 19፡16፤ 20፡24፤ 21፡8፤ 21፡16፤ 21፡29፤ 22፡ 5–6፤ 22፡25፤ 23፡19፤ 23፡26፤ 28፡6፤ 28፡10፤ 28፡18፤ 29፡27፤ 30፡19–20፤ 31፡3** እና **31፡27** ይመልከቱ።


በምሳሌ ውስጥ ብዙ የቃሉ ደራሲዎች ቢኖሩም በዋናነት መጽሐፈ ምሳሌ ከሰሎሞን ጋር የተያያዘ ነው። ሰሎሞን እስከ ዛሬ ከኖሩት ሰዎች ሁሉ ይልቅ ጥበበኛ ሆኖ ስለተገለጠ ከሰሎሞን ጋር መያያዙ ተገቢ ነገር ነው (**1 ነገሥት 3፡12፣ 4፡31፣ 5፡7** እና **2 ዜና 2፡12** ይመልከቱ)። ሰሎሞን የክርስቶስ "ጥላ" ነው። የሰሎሞን ታላቅ ጥበብ የክርስቶስ ታላቅ ጥበብ ምሳሌ ነው። ይሁን እንጂ ክርስቶስ እንደ ሰሎሞን "መንገዱን" አልለወጠም ይልቅስ እንደ ሞኝ ይመላለስ ነበር። ኢየሱስ በመጽሐፈ ምሳሌ ውስጥ ያለውን ጥበብ በፍጹም ሁኔታ ተግብሮታል። ኢየሱስ ደግሞ የመጨረሻው ጥበበኛ ልጅ ነው። ኢየሱስ በመጽሐፈ ምሳሌ ለተጻፈው ጥበብ ሁሉ ዋና ምሳሌ ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ከጥበበኛው ንጉሣቸው ሥር መኖር ታላቅ ደስታ ሊያመጣላቸው ይችላል!

መጽሐፈ ምሳሌ ስለመልካም ሚስት በግጥም መልክ በመናገረ ያበቃል (**ምሳሌ 31፡10–31** ይመልከቱ)። ይህ በመጽሐፉ መጨረሻ ላይ መሆኑ በጥበብ ለሚመላለስ የንጉሥ ልጅ የሚሰጠው "ሽልማት" እግዚአብሔርን የመምሰል ባሕርይና ታላቅ ዋጋ ያላት ሙሽራ መሆኑ የሚያመለክት ይመስላል። ይህም ስለክርስቶስ እውነት ነው። ክርስቶስ ፍጹም ጥበበኛ ሰው ነው። የእርሱ መንገድ ሁልጊዜም ፍጹም ነው። ስለዚህ ኢየሱስ ከሌሎች ሚስቶች ሁሉ በላይ ማለትም ቤተክርስቲያን እሷም "መልካም ሚስት ተሸልሟል" (**ኤፌሶን 5፡22–33** ይመልከቱ)! ክርስቶስ የመጨረሻው "ጥበበኛ ልጅ" እንዴት እንደሆነ

ማሰብ ለሰባኪው ወይም ለአስተማሪው ትልቅ ጥቅም አለው። እንደዚሁም  በምሳሌ 31 ላይ ያለችውን "ክቡር ሚስት" እንዴት ቤተክርስቲያን እንደምትመስል ማሰብ ለሰባኪው ወይም ለአስተማሪው ትልቅ ዋጋ ይኖረዋል።

መጽሐፈ ምሳሌ ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አንዱ ነው። ይሁን እንጂ ክርስቲያኖች ለብሉይ ኪዳን ቅዱሳን ብቻ የተጻፈ አድርገው ሊመለከቱት አይገባም። መጽሐፈ ምሳሌ በዚህ ዘመንም ላሉ አማኞች ትልቅ ዋጋ አለው። አዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ጥበብን እንዲጠይቁ ጥሪ ያቀርባል (**ቆላስያስ 1፡9** እና **ያዕቆብ 1፡5** ይመልከቱ)። ክርስቲያኖች "ጥበብኞች እንዲሆኑ" ታዝዘዋል ( **ኤፌሶን 5፡15–17** እና **ቆላስያስ 4፡5** ይመልከቱ)። ስለዚህ መጽሐፈ ምሳሌ እግዚአብሔር ሕዝቡን በጥበብ እንዲመላለሱ የሚረዳበት አንዱ መንገድ ነው ማለት ነው።





## 18. መጽሐፈ መክብብ በዚህ ዘመን በዚህ ምድር ስላለው ሕይወት የሚናገር ስብከት ነው

በብሉይ ኪዳን ያሉት ሁሉም መጽሐፍት በጥበብ የተሞሉ እና "በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን ለመዳን ጥበበኛ ሊያደርጉ የሚችሉ" ሲሆኑ (**2 ጢሞቴዎስ 3፡15** ይመልከቱ)፤ በተይም ከጥበብ ጋር ቀጥታ የተያያዙ አምስት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አሉ። እነዚህም መጻሕፍት፡- መዝሙረ ዳዊት፣ መጽሐፍ ኢዮብ፣ ምሳሌ፣ መክብብ፣ እና መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን ናቸው። እነዚህ አምስት መጻሕፍት በአንድ መደዳ በጽሑፎች ውስጥ ይገኛሉ። ደግሞም እነዚህ አምስት መጻሕፍት እያንዳንዳቸው አንባቢን በዚህ ዘመን ስላለው የሕይወት ጥበብ ከተለያየ አቅጣጫ ያስተምራሉ።

በእነዚህ አምስቱ የጥበብ መጽሐፍት ውስጥ የተሰጠው ትምሕርት የእግዚአብሔር ቸር ስጦታ ነው። መዝሙረ ዳዊት፣ መጽሐፈ ኢዮብ፣ ምሳሌ፣ መክብብ እና መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን፤ እነዚህ የጥበብ መጻሕፍት እግዚአብሔር ሕዝቡን በዚህ በመከራና በክፋት ዘመን ቅዱስና ፍሪያማ ሕይወት እንዲኖሩ የረዳበት "የቸርነት መንገዶች" ናቸው።

በእነዚህ አምስት የጥበብ መጽሐፍት መካከል ጉልህ ልዩነቶች አሉ። ለምሳሌ መጽሐፈ መክብብ ከሌሎቹ መጽሐፍት የሚለየው ሰባኪው በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የሚሰብከው ረጅም ስብከት በመሆኑ ነው።

መክብብ የሚለው ስም "ሰባኪው" ማለት ነው። ይህ ርዕስ አንባቢዎች መክብብ እንዴት ማንበብ እንዳለባቸው እንዲገነዘቡ ይረዳቸዋል። ማለትም አንባቢ ስብከትን በሚያዳምጥበት መንገድ መጽሐፈ መክብብ ማንበብ አለበት። መጽሐፈ መክብብ በዚህ ዘመን በዚህ ምድር ስላለው ሕይወት የሚናገር ስብከት ነው። ሰባኪው በስብከቱ ጊዜ ሁሉ የራሱን የሕይወት ተሞክሮ ያካትታል። ሰባኪው  በመጽሐፉ ውስጥ ማን እንድሆነ በግልጽ ባይገለጽም ነገር ግን ሰሎሞን ሳይሆን አይቀርም የሚል ግምት አለ።

በተመሳሳይ ሁኔታ በመክብብ ውስጥ ያለው ሰባኪ አንድ ዋና ጭብጥ እንዳለው ሁሉ አንድ ሰባኪ በስብከት ውስጥ አንድ ዋና ጭብጥ ሊኖረው ይገባል። በመክብብ ውስጥ የሚገኘው ሰባኪ ጭብጥ በመጀመሪያ የታወጀው በ**መክብብ 1፡2** ላይ ነው፤ (በተጨማሪም መክብብ 12፡8 ይመልከቱ)።

*ሰባኪው፤ ከንቱ ከንቱ የከንቱ ከንቱ፤*

*ሁሉ ከንቱ ነው ይላል።* **መክብብ 1፡2**

የሰባኪው ጭብጥ የሕይወት “ከንቱነት” ነው። ከንቱነት ግራ አጋቢውን ተፈጥሮ፣ ትርጉም አልባ የሚመስለው ከንቱነት እና የሕይወትን አጭርነት የሚመለከት ይመስላል። ሰባኪው ኃጢአት ወደ ዓለም ከመግባቱ በፊት እግዚአብሔር ያሰበውን ዓይነት ሕይወት እየተናገረ አይደለም። እየተናገረ ያለውም በዚህ የተረገመች ዓለም ውስጥ “ከፀሐይ በታች” ስላለው ሕይወት ነው።

በESV እንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ “ከንቱነት” የሚለው ቃል በዕብራይጥ ሲተረጎም “ትነት” ወይም “እስትፋንስ” እንደ ማለት ነው። “ትነት” እና “እስትፋስ” በዚህ ምድር ላይ ስላለው ሕይወት ተፈጥሮ ፍጹም መገለጫ ነው። በእጅ ለመዝገን እንደማይቻል እንደ ሚተን ጉም ማለት ነው። አንድ ሰው የቱንም ያህል ጠንካራ፣ ጥበበኛ፣ ችሎታ ያለው ወይም ሃብታም ቢሆን ሕይወትን መቆጣጠር የሚችል ኃይል ሊኖረው አይችልም። ልክ እንደ ሚበንን ጉም በዚህ ምድር ላይ ያሉ ነገሮች ሁሉ ለጥቂት ጊዜ በዚህ ምድር ላይ ይኖራሉ ከዚያም ይጠፋሉ። በዚህ ምድር ላይ ቋሚና ዘላቂ የሆነ ምንም ነገር የለም። ሁሉም ነገር ጥሩም ይሁን መጥፎ ይጠፋል፣ የሚታወስ ቢመስልም እንኳን ነገር ግን አይታወስም ይረሳል።

በESV በዕብራይስጥ “ከንቱነት” ተብሎ የተተረጎመው ቃል የአዳም ሁለተኛ ልጅ “አቤል” ከሚለው ስም ጋር ተመሳሳይ ነው። ይህ ማለት የጥንት ዕብራውያን በመክብብ ውስጥ ስለ “ከንቱነት” ሲያነቡ የአቤልን ሕይወት ያስታውሳሉ ማለት ነው። የአቤል አጭር ሕይወት በዚህ ዘመን የሕይወት “ከንቱነት” ምሳሌ ነው። ሕይወቱ በጣም አጭር ስለነበረ እንደ ጉም ወይም ነፍሶ እንደሚያልፍ ነፋስ ይመስላል ማለት ነው። የአቤል ሕይወት ዘላቂ ውጤት ያላስገኘለት ይመስላል። ከምድራዊ እይታ አንጻር ጽድቁ ምንም ዋጋ አልነበረውም፤ ምክንያቱም በክፉ ሰው እጅ ተገደለ። አቤል የተናገረው ምንም የተመዘገበም ነገር የለም። መታሰቢያ የሚሆን ትልቅ ሀውልትም አልገነባም። ስለዚህ ከአቤል ሕይወት ምንም ነገር የዘለቀ አይመስልም። ሕይወት በዚህ መልኩ ስንመለከተው ከንቱነነት ነበር። ምንም ትርጉም የሌለው ይመስላል። ነገር ግን እርግጥ ነው ክርስቲያኖች የአቤል ሕይወት “ከንቱ” እንዳልሆነ ያውቃሉ። ከንቱ ቢመስሉም ነገር ግን ንግግሩና ድርጊቶቹ ዘላቂ ውጤት እንዳስገኙ ያውቃሉ።

*አቤል ከቃየል ይልቅ የሚበልጥ መሥዋዕት ለእግዚአብሔር በእምነት አቀረበ*
*በዚህም እግዚአብሔር ስለ ስጦታው ሲመሰክር እርሱ ጻድቅ እንደ ሆነ ተመሰከረለት፤*
*ሞቶም ሳለ በመሥዋዕቱ እስከ አሁን ይናገራል።* **ዕብራውያን 11፡4**

ነገር ግን ሰባኪው ምንም እንኳን በግልጽ የእምነት ሰው ቢሆንም በዋናነት በእምነት ላይ አያተኩርም። ስለሚመጣውም ዘመን አንስቶ አይናገርም። ይልቁንም በዚህ ዘመን በዚህ ምድር ላይ ባሉ ነገሮች ተፈጥሮ ላይ ያተኩራል። በዚህ ምድር ላይ ያሉት ነገሮች ሁሉ "ከንቱ" መሆናቸውን ሰባኪው አንባቢዎቹ እንዲገነዘቡ ይፈልጋል። በዚህ ምድር ላይ ያለ አንዳችም ነገር ቢሆን በራሱ ጠንካራ እና ቋሚ አይደለም። ከዚህ አንፃር ስንመለከት ሁሉም ነገር ትርጉም የለሽ ይመስላል። ዓለምና ታላቅነቷ እንደ ማይዘገን ጉም ወይም እነደ ምድጃ ጢስ የሚያልፍ ነውና።

በመሠረቱ እግዚአብሔር ሕይወት "ከንቱ" እንዲሆን አላደረገም። ነገር ግን ሕይወት "ከንቱ" እንዲሆን ያደረገው **የውድቀት** ውጤት ነው (ወድቀት የሚለው ክርስቲያኖች የአዳምን የመጀመሪያ ኃጢአትና ውጤቱን ለማመልከት ይጠቀሙበታል)። ሰዎች የተፈጠሩት ፍሬያማ እንዲሆኑና እንዲበዙ ነው (**ዘፍጥረት 1፡26–28** ይመልከቱ)። ይልቁንም ድካማቸው ነው እንደ ደመና እንደ ጭስ የሚበንን የሚመስለው። ምክንያቱም ምድር ከእግርማገን በታች ነችና። ሁሉም ነገር ወደ ሞት ይሄዳል። ነገሮች መሥራት እንዳለባቸው አይሰሩም። ነገር ግን እንደ የምድጃ ጭስ በነፍስ እንደ ሚበተን ይበተናሉ። ከእርግማኑም የተነሳ ሁሉም ከንቱ ሆነው ይታያሉ። ትኩረታችን በዚህ ምድር ላይ ብቻ ከሆነና ዘላቂ መሠረት የማንገነባ ከሆነ ሁሉም ነገር ከንቱ ነው።

ሰዎች ስለ ሕይወት ከንቱነት ከልምድ ይማራሉ። ለምሳሌ አንድ ልጅ አባቱን እንዲህ ሊለው ይችላል " አባቴ ሆይ ጤፉ ተዘርቷል ድካማችንንም ጨርሰናል!" ይህ ሕጻን ልጅ እንዲህ የሚናገረው "ከፀሐይ በታች" ስላላው የሕይወት ከንቱነንት ስለማይገነዘብ ሊሆን ይችላል። ጠቢብ አባት ግን "እንደገና ማጨድና መዝራት እንደሚያስፈልገው ያውቃል። ማለትም ድካም መቼም ቢሆን አያልቅምና።

እንደዚሁም ያው ትንሽ ልጅ "በቃ ጤፉ ተዘርቷል ጥሩ ምርት ደግሞ እናገኛለን!" ሊል ይችላል፤ ጠቢብ አባት ደግሞ "ጥሩ ምርት እናገኝ ይሆናል ነገር ግን አዝመራው ሊወድቅ ይችላል፤ ስለዚህ የተሳካ ምርት ለማግኘት ዋስትና የለም" ብሎ ሊመልስ ይችላል።

በዚህች የተረገመች ዓለም የሕይወት ከንቱነት ይህ ነው። ምንም ነገር ዘላቂ ወይም ቋሚ የሆነ ዋስትና ያለው ነገር የለመና። ሁሉም ነገር ምንም ያህል ታላቅ ቢመስልም በነፋስ እንደሚወሰድ ጉም ነው።

ጌታ ኢየሱስም በተራራው ስብከቱ ላይ ተመሳሳይ ሐሳብ እያስተማረ ነበር።

*"ብልና ዝገት በሚያጠፉት ሌቦችም ቆፍረው በሚሠርቁት ዘንድ*

*ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ . . ."* **ማቴዎስ 6፡19**

እንደዚሁም ሐዋሪያው ጳውሎስም በተመሳሳይ መንገድ የሙታን ትንሣኤ ከሌለ ሁሉም በእውነት ከንቱ ነው በማለት ተናግሯል።

*“. . . ሙታን የማይነሡ ከሆነ ምን ይጠቅመኛል? ነገ እንሞታለንና እንብላና እንጠጣ”*

**1 ቆሮንቶስ 15፡32**

ለአማኖች ግን ሁሉም ነገር ከንቱ አይደለም። የአማኝ ሕይወት ትርጉም እንዳለው ያውቃልና። ይህንንም ደግሞ የመጽሐፈ መክብብ ደራሲ ያውቃል። የመጽሐፈ መክብብ ሰባኪ አላማ የእግዚአብሔር ሰዎች በዚህ ዘመን ስላለው ሕይወት በትክክል እንዲያስቡ መርዳት ነው። ተስፋቸው ሁሉ በዚህ የምድር ዘመን ከሆነ ሁሉም ነገር ያጣሉ በዚህ ምድር ላይ የሚቆይ ምንም ነገር የለምና።

ጌታ ኢየሱስም ተከታዮቹን የጠራቸው ሀብታቸውን በሰማይ እንዲያከማቹ ነው።

*“. . . ነገር ግን ብልም ዝገትም በማያጠፉት ሌቦችም ቆፍረው በማይሰርቁት*

*ዘንድ ለእናንተ በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ፤*

*መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ በዚያ ይሆናል።”* **ማቴዎስ 6፡20–21**

መጽሐፈ መክብብ ለእግዚአብሔር ሕዝብ የጥበብ መጸሐፍ ነው። ተስፋችን በመጨረሻው ከንቱ በሚሆነው ነገር ላይ እንዳናደርግ የሚያስጠነቅቅ መጽሐፍ ነው።

*“ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም። ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራል።”* **1 ዮሐንስ 2፡15–17**

መጽሐፈ መክብብ የተደራጀው እንዴት ነው?

መጽሐፈ መክብብ የሚጀምረው **በመቅደም** ሲሆን (**መክብብ 1፡1**) የሚደመደመው ደግሞ የነገር ሁሉ ፍጻሜ **በማተት** ነው (**መክብብ 12፡9–14**)። መቅደም ከሥነ ጽሑፍ ሥራ በፊት መጀመሪያ ላይ

ጥቅም ላይ የሚውል ሥነ ጽሑፋዊ ሃተታ ነው። በመቅደም ላይ የሚጻፉቱ ቃላቶች የሥነ ጽሑፉ አካል ቢሆኑም ከዋናው ሥነ ጽሑፍ ለየት የሚል ሃተታ ነው። ዓላማውም አንባቢው ቀጥሎ ለሚያነበው ሥነ ጽሑፍ የሚያዘጋጅ ነው። የመጽሐፈ መክብብ መቅደም አስፈላጊ ላይመስል ይችላል። ነገር ግን እንደሱ መገመት ትክክል አይደለም። በመቅደሙ ላይ ባሉት ቃላቶች ተመስርቶ ማንበብ በጣም በጣም አስፈላጊ ነው።

*በኢየሩሳሌም የነገሠ የሰባኪው የዳዊውት ልጅ ቃል።* **መክብብ 1፡1**

በእነዚህ ቃላት አማካይነት ደራሲው ከዳዊት ዘር የሆነ ከዳዊት ቃል ኪዳን ጋር የተያያዘ ንጉሥ መሆኑን እያወጀ ነው (**2 ሳሙኤል 7፡ 1–17**)። ይህ ደግሞ አንባቢው ወደ መጽሐፈ መክብብ እንዴት መቅረብ እንዳለበት ያዘጋጀዋል ማለት ነው። ይህ ቃል እግዚአብሔር በቀባው ንጉሥ ለእግዚአብሔር ሕዝብ የተሰጠ ጥበብ ነው።

ስለዚህ መቅደሙ በመክብብ ውስጥ ያለውን ቃል ከሰሎሞን ጋር ያገናኘዋል (በተጨማሪም **መክብብ 1፡12** እና **መክብብ 2፡1–11** ይመልከቱ)። ሰሎሞን የዳዊት ልጅ ደግሞም የክርስቶስ ምሳሌ ነው። ይህ ማለት ከነገሥታት ሁሉ በላይ የነበረው የሰሎሞን ጥበብ የእውነተኛው "የዳዊት ልጅ" የኢየሱስ ክርስቶስ ጥበብ ትንሽ ምሳሌ ነው።

መደምደሚያ ደግሞ ከሥነ ጽሑፍ ሥራ በኋላ የተጻፈውን በአጭሩ ለማጠቃለል ጥቅም ላይ የሚውል ሥነ ጽሑፋዊ ቃል ነው። በመደምደሚያው ላይ የሚጻፈው ጽሑፍ ልክ እንደ መቅደሙም የሥነ ጽሑፉ ሥራ አካል ቢሆንም ነገር ግን ደግሞ ለየት ያለ ባሕሪይ አለው። ማለትም ልክ እንደ መቅደሙም መደምደሚያም ከሥነ ጽሑፉ ለየት የሚል ክፍል ነው። አንባቢው በዋናው ጽሑፍ ውስጥ ምን እንደ ተባለ ባአጭሩ የሚገነዘብበት ነው። ስለዚህ አንባቢው ዋናውን መልዕክት እዳላመለጠው የሚያረጋግጥ ክፍል ነው። የመጽሐፈ መክብብ መደምደሚያ እንደ ሚከተለው ቀርቧል።

*ሰባኪውም ጠቢብ ስለ ሆነ ለሕዝቡ እውቀትን አስተማረ፤ እርሱም ብዙ ምሳሌዎችን መረመረና ፈላለግ አስማማም። ሰባኪው ያማረውን በቅንም የተጻፈውን እውነተኛውን ቃል መርምሮ ለማግኘት ፈለገ።*

*የጠቢባን ቃል እንደ በሬ መውጊያ ነው፤ የተሰበሰቡትም ከአንድ እረኛ የተሰጡት ቃላት እንደ ተቸነከሩ ችንካሮች ናቸው። ከዚሁም ሁሉ በላይ፤ ልጄ ሆይ ተግሣጽን ስማ፤ ብዙ መጻሕፍትን ማድረግ ፍጻሜ የለውም፤ እጅግም ምርምር ሰውነትን ያደክማል።*

*የነገሩ ሁሉ ፍጻሜ እንስማ፤ ይህ የሰው ሁለንተና ነውና፤ እግዚአብሔርን ፍራ ትእዛዙንም ጠብቅ። እግዚአብሔር ሥራን ሁሉ የተሰወረውንም ነገር ሁሉ መልካምም ቢሆን ክፉም ቢሆን ወደ ፍርድ ያመጣዋልና።* **መክብብ 12፡9–14**

የመጽሐፈ መክብብ መደምደሚያ "የጠቢባን ቃል" "እንደ በሬ መውጊያ " መሆኑን አጽንዖት ይሰጣል። በተመሳሳይም ገበሬው እንዲንቀሳቀስ በሬውን በሾለ በትር እንደሚወጋው፤ የጠቢባንም ቃል የእግዚአብሔርን ሕዝብ በትክክለኛው መንገድ እንዲንቀሳቀስ ያግዛል። የእግዚአብሔር ሕዝቦች ከሌሎች ቦታዎች መመሪያ መፈለግ የለባቸውም። በሚመራቸው በእረኛቸው መታመን አለባቸው እንጂ።

መደምደሚያው የሚያበቃው በዚህ ዘመን ሊሆን በሚገባው የሰባኪው መመሪያ ነው፡- "እግዚአብሔርን ፍራ ትእዛዙንም ጠብቅ።" ከዚያም ሰባኪው የእግዚአብሔር ሕዝቦች እነዚህን ሁለት ነገሮች ማድረግ ያለባቸው ለምን እንደሆነ ይገልጻል፡- እግዚአብሔር ፈራጅ እንደሆነና "ሥራን ሁሉ የተሰወረውንም ነገር ሁሉ መልካምም ቢሆን ክፉ ወደ ፍርድ ያመጣዋል" ይላል።

በመቅደሙና በመደምደሚያው መካከል የሰባኪው ስብከት ይገኛል። የሰባኪው ስብከት በዚህ ምድር ላይ ያለው ሕይወት " ከንቱ" መሆኑን ያረጋግጣል። በስብከቱም ጊዜ ሁሉ ሰባኪው በዚህ ዘመን ስላለው የቅርብ የሕይወት ጥናት ይናገራል። ከንቱ ያልሆነ ነገር ለማግኘት ስላደረጋቸው ነገሮችና ስለ ሞከረው ነገር ይናገራል።በዚህ ዓለም ከንቱ ያልሆነ ነገር ማግኘት ግን  እንዳልቻለ ይናገራል። ሰባኪው ለአንባቢዎቹ "ሁሉም ከንቱ" መሆኑን ለማረጋገጥ "ከፀሐይ በታች" ስላደረጋቸው ልምምዶች ሁሉ ይነገራል። ንጉሡ ስለ "እግዚአብሔር ለሰው ልጆች እንዲደክሙበት ስለ ሰጣቸው ደስ የማይል ሥራ አንስቶ ይናገራል (**መክብብ 1፡13**)። በሰባኪው ግንዛቤ "ሁሉም ነገር ከንቱና ነፋስንም እንደ መከተል ነው።" (**መክብብ 1፡14**)

ንጉሡ ጥበብን አብዝቶ ይፈልግና ይጨምርም ነበር፤ ነገር ግን እርካታ አላገኘም (**መክብብ 1፡16–17**)። እንደዚሁም ደግሞ "እብደትንና ስንፍናን" ይከተል ነበር (**መክብብ 1፡17**)፤ ይህም ከንቱ ነገር ሆነበት። ትምህርትን፣ በወይን ጠጅ መርካትን፣ ግንባታዎችን ማካሄድ፣ ብዙ ባሪያዎችን ማሳደር፣ የበግ መንጎችንና

ሌሎችንም እንስሳቶችን ለራሱ አበዛ፣ ሃብት በማካበትና በግብረሥጋ ግኑኝነት ለመርካት ጣረ፤ ነገር ግን ሰባኪው ከርሱ ተሞክሮ ሲናገር እነዚህ ሁሉ ነገሮች ከንቱ መሆናቸውን ተረዳ። ከእነዚህ መካከል አንዱንም እንኳን ቢሆን “ከፀሐይ በታች” ያለውን የከንቱነት ችግር ሊፈታ እንደ ማይችል ተረዳ።


ሰባኪው ታሪኩን ከመናገር ያለፈ ነገር በማደርግ ወደ መደምደሚያው ያመራል። እነዚህም መደምደሚያዎች በመጽሐፉ ውስጥ ይገኛሉ። ስለዚ ሰባኪው ስብከቱን ለሚሰሙ ሰዎች በዚህ ዘመን “ከፀሐይ በታች” እንዴት መኖር እንዳለባቸው ይነግራቸዋል።


በመጽሐፈ መክብብ ውስጥ ዋናው ጭብጥ “ከፀሐይ በታች” ያለው ሕይወት ተፈጥሮ የሚመለከት ነው (**1፡3፣ 1፡9፣ 1፡14፣ 2፡11፣ 1፡17–20፣ 3፡16፣ 4፡1፣ 4፡3፣ 4፡7፣4፡15፣ 5፡13፣ 5፡18፣ 6፡1፣ 6፡12፣ 8፡9፣ 8፡15፣ 8፡17፣ 9፡3፣ 9፡6፣ 9፡9፣ 9፡11፣ 9፡13** እና **10፡5** ይመልከቱ)። “ከፀሐይ በታች” የሚለው ሐረግ በዚህ “ የተረገመች” ዘመን ያለውን ሕይወት ያመለክታል። እንደዚሁም ደግሞም ከ“ውድቀት” በኋላ ያለውን ጊዜ (የአዳም ኃጢአት) የሚያመለከት። ደግሞ ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት በፊት ያለውን ጊዜም ያመለክታል ከዚያም ማለትም ከዳግም ምጽአት በኋላ እረግማን አይኖርም።

የመጽሐፈ መክብብ የክርስቲያን አንባቢዎች ሕይወት ሁልጊዜ “ከፀሐይ በታች” እንደ ማይሆን ያውቃሉ። በሌላ አነጋገር እርግማን የማይኖርበት ዘመን ይመጣልና፤ እንዳውም አማኞች በሚመጣው ዘመን ፀሐይ እንደማያስፈልግ ማስታወስ አለባቸው (**ራዕይ 21፡23** ይመልከቱ)። ሕይወት በዚያን ጊዜ “ከፀሐይ በታች” መሆኑን ይቀርና ከእውነተኛው የእግዚአብሔር ክብር ብርሃን ስር ይሆናል። ሰዎችም በእግዚአብሔር ልጅ “ብርሃን” ይሄዳሉ። ከእንግዲህ እርግማን ስለማይኖር ሕይወት በዚያን ጊዜ ከንቱ አይሆንም። ይሁን እንጂ እስከዚያች ቀን ድረስ አማኞች በዚህ ዘመን ለመኖር ጥበብ ያስፈልጋቸዋል። መጽሐፈ መክክብብ ደግሞ የዚህን ጥበብ ክፍል ያቀርባል። ይህም ጥበበ አማኞችን ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ የሚያመልከት ልክ እንደ በሬ መውጊያ ነው (**መክብብ 12፡11** ይመልከቱ)።

በ**መክብብ 1፡1፣ 1፡12፣** እና **2፡1–12** ባለው መሠረት ሰሎሞን የመጽሐፈ መክብብ ደራሲ ነው። ይህም ደግሞ መክብብ በምሳሌ እና በመኃልይ መኃልይ መካከል የተቀመጠው ለምን እንደሆነ ያብራራልናል። ከሰሎሞን ጋር የተያያዙት ሦስቱ መጻሕፍት በአንድ መደዳ እንዲደረደሩ ተድረጓልና። ሰለሞን በመጽሐፈ መክብብ ላይ ከገለጻቸው ተሞክሮዎች በመነሳት ይህ የሰሎሞን ስብከት የተጻፈው

በሕይወቱ ዘግይቶ ሳይሆን አይቀርም። ስብከቱም ሰሎሞን ከዓመታት ኃጢአት በኋላ ንስሐ እንደገባ ያሳያል። አንባቢዎቹ እሱ ያደርገውን እንዲያደርጉ አይመክርም። ይልቅስ እግዚአብሔርን እንዲፈሩና እግዚአብሔርም ለሰዎች በሰጣቸው ስጦታ እንዲደሰቱ ያበረታታል (**2፥24–25፣ 3፥11–14፣ 5፥1–7፣ 5፥18–20, 7፥13–14፣ 8፥12, 8፥15 –9፥1፣ 9፥9–10** እና **12፥13–14** ይመልከቱ)።





## 19. መኃልይ መኃልይ ዘሰለሞን የመጨረሻ ቅልጥ ያለ የፍቅር ታሪክ ያወሳል

በብሉይ ኪዳን ያሉት ሁሉም መጽሐፍት በጥበብ የተሞሉ እና “በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን ለመዳን ጥበበኛ ሊያደርጉ የሚችሉ” ሲሆኑ (**2 ጢሞቴዎስ 3፡15** ይመልከቱ)፤ በተይም ከጥበብ ጋር ቀጥታ የተያያዙ አምስት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አሉ። እነዚህም መጻሕፍት፡- መዝሙረ ዳዊት፣ መጽሐፍ ኢዮብ፣ ምሳሌ፣ መክብብ፣ እና መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን ናቸው። መኃልይ መኃልይ ዘሰለሞን ደግሞ በአጭሩ መኃልይ መኃልይ ተብሎም ይጠራል።እነዚህ አምስት መጻሕፍት በአንድ መደዳ በጽሑፎች ውስጥ ይገኛሉ። ደግሞም እነዚህ አምስት መጻሕፍት እያንዳንዳቸው አንባቢን በዚህ ዘመን ስላለው የሕይወት ጥበብ ከተለያየ አቅጣጫ ያስተምራሉ።

በእነዚህ አምስቱ የጥበብ መጻሕፍት ውስጥ የተሰጠው ትምሕርት የእግዚአብሔር ቸር ስጦታ ነው። መዝሙረ ዳዊት፣ መጽሐፈ ኢዮብ፣ ምሳሌ፣ መክብብ እና መኃልይ መኃልይ ዘሰሎሞን፤ እነዚህ የጥበብ መጻሕፍት እግዚአብሔር ሕዝቡን በዚህ በመከራና በክፋት ዘመን ቅዱስና ፍሬያማ ሕይወት እንዲኖሩ የረዳበት “የቸርነት መንገዶች” ናቸው።

በእነዚህ አምስት የጥበብ መጽሐፍት መካከል ጉልህ ልዩነቶች አሉ። መኃልይ መኃልይ ዘሰሎሞን ከሌሎቹ መጽሐፍት የሚለየው በወንድና በሴት መካከል ባለው ፍቅር ላይ ያተኮረ መጽሐፍ መሆኑ ነው።

መኃልይ መኃልይ ዘሰሎሞን ወይም መኃልይ መኃልይ ልክ እንደ መጽሐፈ ምሳሌና መጽሐፍ መክብብ ከሰሎሞን ጋር የተያያዘ ነው። መጽሐፉም በሰሎሞን የተፃፈው በሕይወቱ መገባደጃ ላይ ሳይሆን አይቀርም (**መኃልይ መኃልይ 1፡1** ይመልከቱ)። ልክ እንደ መጽሐፈ መክብብም፤ ይህ መጽሐፍ ሰሎሞን በሕይወቱ መጨረሻ ንስሐ እንደገባና የኖረበትንም የኃጢአት መንገድ በትክክል እንደተረዳ የሚያሳይ ማስረጃ ነው። የሰሎሞን መጽሐፎች ሰሎሞን እውነተኛውን ጥበብ ለመከተል ልቡን እንዳቀና የሚያመላክቱ ናቸው። ለዚህ ማስረጃ የሚሆነን ሰሎሞን በሕይወቱ መገባደጃ ላይ ንስሐ እንደገባ የሚያመላክት ቃል በ**2 ዜና 9፡22–31** ላይ ተጽፎ ይገኛል። የዜና መዋዕለ ካልዕ ጸሐፊ ስለ ሰሎሞን ኃጢአት አይነግረንም። ይልቁንም ሰሎሞን በእግዚአብሔር (በያሕዌ) ፊት ትክክል እንደ ነበር አድርጎ ነው የጻፈው። የዜና መዋዕለ ካልዕ ጸሐፊ በሰሎሞን ላይ በመፍረድ አልጻፈም ይልቅስ ሰሎሞንን በተመለከተ የፍርድ ቃል መጨረሻ ሊሆን እንደሚገባው የወሰነ ይመሳላል። ይህም ደግሞ ሰሎሞን በራሱ ላይ እንደፈረደና ስለኃጢአቱም ንስሐ እንደገባ የሚያሳይ ማስረጃ ሊሆን ይችላል። ምናልባት ይህ አንዱ

ምክንያት ሲሆን ሌላው ደግሞ የዜና መዋዕለ ጸሐፊ የሰሎሞንን ኃጢአት መዘርዘር አላስፈለገውም ነበር ሊሆን ይችላል።

መኃልይ መኃልይ ስለ ፍቅርና ጋብቻ የተጻፈ የሰሎሞን ቃል ይመስላል። በመሆኑም ይህ መጽሐፍ **የሕይወት ታሪክ** አይደለም። ደግሞም ከአንዲት ወጣት ልጃገረድ ጋር የነበረው የፍቅር ታሪክ አይደለም። በ **1 ነገሥት 11** በተገለጸው መሠረት ከሆነ ሰሎሞን ከአንዲት ልጃገረድ ጋር ስላደረገው የፍቅር ግኙኝነት በማንሳት ሊጽፍ አይችልም ነበር። ደግሞም ሰሎሞን ብዙ ሴቶችን ይወድድ ነበር ስለዚህም ነው ብዙ ሚስቶችንና ቁባቶችን ያገባው (**1 ነገሥት11፡ 1–8** ይመልከቱ)።

በዚህ መጽሐፍ የተገለጸው ፍቅር ሰሎሞን እንደ ሌላ ሴት እንደነበረው ዓይነት "ፍቅር" አይደለም። በመኃልይ መኃልይ ፍቅር ንፁህ ነው ሊመሰገንም የሚገባው ነው። በ**ዘፍጥረት 2** ላይ አዳምና ሔዋን ለእርስ በርሳቸው የነበራቸው ፍቅር የሚያሳይ ዓይነት ነው፤ እንደዚሁም በ**ዘፍጥረት 3** እና ከዚያም በኋላ አንዳቸው ለሌላቸው ይህን ዓይነት ፍቅር ሊኖራቸው ይገባ ነበር። ሆኖም ሰሎሞን ስለራሱ ፍቅር ሳይሆን የጻፈው፤ ይልቅስ ሰሎሞን የጻፈው በአንድ የገጠር ወንድ እረኛና አንዲት የገጠር ልጃገርድ መካከል ስለተመለከተው የፍቅር ግኙኝነት አስመልክቶ ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት በመኃልይ መኃልይ የተገልጹትን ገጸ ባሕሪያት ብዛት በተመለከተ የተለያየ ሐሳብ ሲሰነዝሩ ይስተዋላል። ስለዚህ ታሪኩን ለማንበብ የሚቻልበት አንዱ መንገድ እንደሚከተለው ነው።

በመኃልይ መኃልይ ውስጥ አራት ዋና ዋና ገጸ ባሕሪያት ያሉ ይመስላል። የመጀምሪያዋ ገፀ ባሕሪ ሱላማጢስ የተባለች ወጣት ሴት ነች። እሷም መልካምና ንጹህ ሴት ነች። እንዳውም ሔዋን መሆን የነበረባትን ምሳሌ የምታመልክት ነች። ሁለተኛው ገፀ ባህሪ ወጣት ወንድ እረኛ ነው። እርሱም መልካምና ንጹህ ሰው ነው። ስለዚህ አዳም ሊሆን የሚገባውን ሊወክል የሚቸል ዓይነት ሰው ነው። ሦስተኛው ገፀ ባሕሪይ በእርግጥ የሰዎች ስብስብ ነው። እነዚህ ሰዎች ይህን የፍቅር ግኙኝነት እየተመለከቱ እና እየተከናውኑም ስለነበሩት ክስተቶች አስተያየቶችን ሲሰጡ እንመለከታለን። አራተኛው ገፀ ባህሪ ሰሎሞን ራሱ ነው። በእነዚህ ግጥሞች ውስጥ ሰሎሞን "ጀግና" አይደለም። ይልቁንም ሰሎሞን በወጣትዋ የገጠር ልጃገረድ ሱላማጢስና በወጣቱ የገጠር እረኛ መካከል ያለውን ፍቅር እንቅፋት ነው። በሌላ አነጋገር፤ ሰሎሞን ታማኝነትና ሥነምግባር የጎደለው መሆኑን ሲያሳይ የእረኛውና የሱላማጢስ ሥነምግባርና ታማኝነት ደግሞ ያጎላል። ሰሎሞን በብዙ ሴቶች ፍቅር የተነደፈ ሲሆን የገጠሩ እረኛ ግን ለአንድዋ ለገጠርዋ ልጃ ገረድ ለሱላማጢስ ያለውን ብቸኛ ፍቅር ጎላ አድርጎ ያሳያል።

የገጠርዋ ልጃገረድ ሱላማጢስ ሰሎሞን ቢወስዳት ኖሮ ከነንበሩት ሴቶች መካከል እንደ አንድ ተጨማሪ ሴት ትሆን ነበር። ሰሎሞን በመቶዎች የሚቆጥሩ ሴቶች ይመኝ እንደነበረው ሁሉ ወጣትዋ ልጃገረድ ሱላማጢስንም የማግኘት ፍላጎት ነበረው። እንዳውም ወደ እልፍኙ ወስዶ ለጋብቻ እያዘጋጃት እንደ ነበርም ይመስላል። ሆኖም ወጣትዋ የገጠርዋ ልጃገርድ ሰሎሞንን አልፈለገችውም። ልቧ የሰጠቸው ለወጣቱ እረኛ ነበርና።

ይህ "ከመዝሙር ሁሉ የሚበልጥ መዝሙር" መኃልይ መኃልይ ዘሰሎሞን ተብሎ ቢገለጽም ለመዘመር ታስቦ የተጻፈ መሆኑ በእርግጠኛነት መናገር አይቻልም። በእርግጥ ደግሞ ከብዙ መዝሙሮች የበለጠ ረዥም ነው። ደግሞ በሌሎች መዝሙራት የሙዚቃ መመሪያ እንደሚካተት ሁሉ እዚህ ላይ ግን ምንም መመሪያ አልተካተተም ወይም የለም። ይህ እንግዲህ ስለፍቅር ግጥም ይመስላል። ግጥሙም በጣም ቆንጆ ነው ደግሞም ከመዝሙር ሁሉ የሚበልጥ መዝሙር ተብሏል። ስለዚህ ከሌሎች መዝሙሮች ይበልጣል ማለት ነው። እንደዚሁም በተመሳሳይ መልኩ በእብራይስጥ በተዋቀሩ መዝሙሮች ውስጥ በሌሎች ቦታዎች ጥቅም ላይ ውሏል። በቤተ መቅደሱ ውስጥ ያለው ቅዱስ ስፍራ " ቅድስተ ቅዱሳን" ተብሏል። ኢየሱስም ደግሞ "የነገሥታት ንጉሥ" ተብሎ ተጠርቷል።

*መኃልይ መኃልይ የሰሎሞን ነው።* **መኃልይ መኃልይ 1፡1**

ይህ "መዝሙር" በጣም እንዲያምር ያደርገው ምንድር ነው? በአንድ ወንድና ሴት መካከል ያለውን ፍቅር ስለሚያከብር ውብ ነው። ይሁን እንጂ ይህ መጽሐፍ በቀኖና ውስጥ የተካተተበት ምክንያት የፍቅር እና ምድራዊ ጋብቻን ለማክበር ብቻ አይደለም። በክርስቶስ እና በቤተ ክርስቲያን መካከል ያለውን ጋብቻ ማለትም ወደ መጨረሻው ጋብቻ ትኩረትን ለመሳብ ምድራዊ ጋብቻን ስለሚጠቀምም ነው በቀኖና ውስጥ የተካተተው።

እንደገና ለማስታውስ ያህል በመኃልይ መኃልይ ውስጥ አራት ዋና ዋና ገፀ ባህሪያት እንዳሉ ይመስላል፤ እነሱም የገጠርዋ ወጣት ልጃገረድ ሱላማጢስ፣ ወጣቱ እረኛ፣ የሰዎች ስብስብ እና ንጉሥ ሰለሞን ናቸው።

ወጣትዋ ልጃገረድ ሱላማጢስ ከምድራዊው ዝነኛ ንጉሥ (ሰሎሞን) ጋር መሆን ትችል ነበር። ታላቅ ሃብትና ክብርም ይሰጣት ነበርና። ይሁን እንጂ ወጣትዋ ሱላማጢስ በእረኛው ወጣት ልጅ ላይ ትልቅ ዋጋ ያለው ነገር ሰለተመለከተችና ከልብ ስለምትወደው ከንጉሡ ይልቅ ችግረኛውን እረኛ መረጠች። ሱላማጢስ በምርጫዋ ምክንያት ችግር ሊደርስባት ይችል ይሆናል። ከንጉሡ ጋር መቀራረብ ምናልባት ይቀልላት ነበር ይሆናል።

ይህ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው፤ ምክንያቱም መኃልይ መኃልይ በመጨረሻ በክርስቶስ እና በቤተ ክርስቲያን መካከል ያለውን “ጋብቻ” የሚያሳይ ነውና። ቤተክርስቲያን ልክ እንደ ወጣትዋ ሱላማጢስ ከዓለም ጋር የመጋባት እድል ሊገጥማት ይችላል። አብዛኛውንም ሰው ልታደርግ የሚጠብቀው ይህንኑ ነው። ሰሎሞን ለወጣትዋ ሱላማጢስ ሀብትና ክብር ማቅረብ ይችል እነደ ነበረ ሁሉ ዓለምም ለቤተክርስቲያን ጊዜያዊ ሀብትና ክብር መስጠት ትችላለች። ወጣትዋ ሱላማጢስ ግን ሰሎሞንን አልመረጠችም። እንደዚሁም ቤተ ክርስቲያንም ዓለምን መምረጥ የለባትም። ይልቁንም “ያልታወቀውን” እረኛ ትመርጣለች እንጂ። ቤተ ክርስቲያን ከአለም ጋር ምንም ቅርርብ ሊኖራት አይገባም። በዚህ ጊዜም ከእረኛው ጋር ያላትን ቅርርብ ትታደጋለችና። ይህ በመኃልይ መኃልይ ውስጥ የሚገኝ የመጨረሻ የሚያስደስት ታሪክ ነው።

በመኃልይ መኃልይ በዘፍጥረት 2 እና 3 መካከል ብዙ ተቀራራቢ ነገሮች አሉ። ዘፍጥረት 2 እና 3 የተጻፉት ከመኃልይ መኃልይ ዘሰሎሞን በፊት ነው። ስለዚህ እነዚህ ሁለት ምዕራፎች ከመኃልይ መኃልይ ምንም ዓይነት ቋንቋ አይበደሩም። ነገር ግን መኃልይ መኃልይ ዘሰሎሞን ከዘፍጥረት 2 እና 3 ብዙ ቋንቋዎችን ይዋሳል። ሰሎሞን ከዘፍጥረት 2 እና 3 ቃላትን እና ሀሳቦችን የተዋሰ ይመስላል ምክንያቱም ምናልባት አናባቢዎቹ ከዘፍጥረት ጋር ያለውን ግኑኝነት እንዲያገናዝቡት ይሻ ይሆናል። መኃልይ መኃልይ ዘሰሎሞን ልክ እንደ ዘፍጥረት 2 እፅዋትን፣ ፍራፍሬን፣ ወንዞችን፣ የከበሩ ድንጋዮችን ይጠቅሳል። በእነዚህ ምክንያት በመኃልይ መኃልይ ዘሰሎሞን የተገለጸው እረኛና ወጣትዋ ሱላማጢስ የአዳምና የሄዋን አንባቢያን ለማስታውስ የታሰበ ይመስላል።

መኃልይ መኃልይ ግን የአዳምንና የሔዋንን ታሪክ በግጥም መልክ ብቻ እየተናገረ አይደለም። ይልቁንም ይህ የአዳምና የሄዋን ታሪክ አዲስ “ስሪት” ነው። በዚህኛው የአዳምና የሔዋን አዲስ ታሪክ “ስሪት” ውስጥ ወንድና ሴት ለኃጢአት እጅ አይሰጡም። አንዳቸው ከአንዳቸው ውጪ የሆነ ግኑኝነት የላቸውም። እርስበርሳቸው ይተማመናሉ፤ ግኑኝነታቸውን ከፍ አደርገው ይመለከታሉ፣ እንደዚሁም ሁለቱም ግዴታቸውንም ይወጣሉ።

### ጠቢብ ሰባኪ ወይም አስተማሪ በመኃልይ መኃልይ እንዴት ሊጠቀምበት ይችላል?

1. መኃልይ መኃልይ በሰው ጋብቻ ላይ የሚደሰት መጽሐፍ ነው። ይህ መዝሙር በቀኖና ውስጥ መገኘቱ ጋብቻ በጣም አስፈላጊ መሆኑን ያሳያል። መዝሙሩ በአንድ ወንድና በአንድ ሴት መካከል ያለውን መልካም ጋብቻ በጎ እደሆነና ሊከበርም እንደሚገባ ያሳያል። ይህ **ከውድቀት** በፊት እውነት ነበር (ውድቀት የአዳምን ኃጢአትና ውጤቱን ለማመልከት ሊቃውንት የተጠቀሙበት ቃል ነው)። ጋብቻ ከውድቀት በኋላም እውነት ነው።

2. መኃልይ መኃልይ ዘሰሎሞን በአንድ ወንድና በአንድ ሴት መካከል ያለውን ጤናማ ግኑኝነት የሚያሳይ ነው። ወንዱ ሴቲቱን ያከብራል ሴቲቱም ወንዱን ታከብራለች። የወንዱ ጥልቅ ፍላጎት ለሴት ሲሆን የሴቷም ጥልቅ ፍላጎት ለወንድ ነው። በዚህ ግኑኝነት ውስጥ የትኛውም ሰው የተጨቆነ አይደለም።


3. መኃልይ መኃልይ ዘሰሎሞን በባልና ሚስት መካከል የሚድረገውን የግብረ ሥጋ ግኑኝነት ያከብራል። መዝሙሩ ወሲብ እግዚአብሔር ለተጋቡ ሰዎች ከሰጣቸው መልካም ስጦታዎች አንዱ እንደ ሆነ ያሳያል። ይህ ስጦታ ለባልና ለሚስት የተሰጠ ሲሆን ለወንዱም ለሴትየዋም ደስ እንዲሰኙበት ታስቦ ነው።


4. መኃልይ መኃልይ ዘሰለሞን በእግዚአብሔር ፈጣሪነት ይደሰታል። እግዚአብሔር ሰዎችን ሆን ብሎ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠረ። ደግሞም ጋብቻን ፈጥረ። ስለዚህ በትዳር ውስጥ ያለው ደስታ ሁሉ የእግዚአብሔር መልካምነትና በፈጠራ ሥራው እንድንደሰት ያደርገናል።

5. መኃልይ መኃልይ ዘሰሎሞን በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መካከል ያለውን እውነተኛ ግኑኝነት የሚያሳይ ስዕል ነው። ክርስቲያኖች ስለ ሰው ጋብቻ ከመናገር ወደ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን ጋብቻ መነጋገር በፍጥነት መሸጋገራቸው በጣም ተፍጥሮአዊ ነው። በ**ኤፌሶን 5፡22–33** ላይ ሐዋሪያው ጳውሎስ ስለ ጋብቻ ሲናገር ያደረገው ይህንኑ ነው። ስለ ሰው ጋብቻ ማውራት ጀመረ፤ ይሁን እንጂ ስለ ሰው ጋብቻ ከመናገር ወደ በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መካከል ስላለው “ጋብቻ” ወደ መናገር ሄደ። መኃልይ መኃልይ ዘሰሎሞን ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንዴት እንደሚወድ እና ቤተ ክርስቲያንን እንደሚናፍቅ እንደዚሁም ስለ ቤተክርስቲያን እንደሚዋጋ ያሳያል። መኃልይ መኃልይ ዘሰሎሞን ቤተ ክርስቲያን ለንጉሷ ያላትን ወበት እና ጥንካሬ እንደዚሁም በመገዛትዋ ላይ ይደሰታል። ቤተ ክርስቲያን ከአለም ጋር አታመነዝርምና።

6. መኃልይ መኃልይ ዘሰሎሞን በጣም አስፈላጊ መጽሐፍ ነው፤ ምክንያቱም ክርስቲያኖች ካላቸው **የመጨረሻዎቹ ዘመን** ግንዛቤ ጋር የሚዛመድ ስለሆነ (የመጨረሻው ዘመን ጥናት አንዳንድ ጊዜ ፍጻሜ ተብሎ ይታወቃል)። በመኃልይ መኃልይ ዘሰሎሞን ውስጥ የሚነገረው ታሪክ የጋብቻ ታሪክ ነው—የሰው ጋብቻ እና በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መካከል ያለውን ጋብቻ። ምድራዊ ጋብቻ ጊዜያዊ ነው። ሞት ሁሉንም ምድራዊ ጋብቻዎች ወደ ፍጻሜ ያመጣቸዋል። ይሁን እንጂ በክርስቶስና

በቤተ ክርስቲያን መካከል ያለውን ጋብቻ ዘላለማዊ ነው። ሱላማጢስ ከእረኛው ወጣት ጋር ለመጋባት እየጠበቀች ነበር። ያንን ቀን ስትጠብቅ ብዙ መከራ ተቀብላለች። አሁን ክርስቲያኖች እጅግ የላቀ የጋብቻ ሥነ ሥራዓት የሚካሄድበትን ቀን እየጠበቁ ናቸው። ክርስቲያኖችም ብዙ ጊዜ የወሰደውን የጋብቻ በዓል በመጠበቅ ላይ ስለሆኑ መከራ እየተቀበሉ ናቸው። የክርስቶስና የቤተ ክርስቲያን ጋብቻ በተመለከተ **ራዕይ 19፡6–9** ይመልከቱ።





## 20. ሰቆቃው ኤርምያስ የሚያወሳው ስለ ኢየሩሳሌም ውድምት ነው

ማዘን **ከውድቀት** በፊት ያልነበረ የሰው ስሜት ነው (ውድቀት የአዳምን ኃጢአትና ውጤቱን ለማመልከት ሊቃውንት የተጠቀሙበት ቃል ነው)። ነገር ግን በአዳም ኃጢአት ምክንያት ሁሉም ሰዎች ማዘን ደርሶባቸዋል። ማዘን በጣም የበዛ ሀዘን በሰው ላይ ሲፈስስ ነው፤ ይህም በጣም አስፈላጊ የሆነ ነገር ስለጠፋ፣ ስለተለወጠ፣ ስለተወሰደ፣ ስለወደመ ወይም ስለሞተ ሊሆን ይችላል።

በእርግጥም ማዘን ሲኖር ልቅሶም አለ ማለት ነው። ልቅሶ ደግሞ **የሀዘን** ሥነ ጥበባዊ መገለጫ ነው። ልቅሶ ልክ እንደ ማዘንም ከውድቀት በፊት አልነበረም። ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት በኋላ ቢያንስ በተመሳሳይ የማዘን መንገድ አይኖርም። (ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት በኋላ፣ ልቅሶ ክርስቶስ ስለሕዝቡ ድል የነሳበትን ለማስታወስ የደስታ እንባ በመሆን ሊያገለግል ይችል ይሆናል!) አብዛኛውን ጊዜ ልቅሶ በግጥም ወይም በዜማ መልክ ይቀርባል። ልቅሶ በጣም በኃይለኛ በሆነ የልብ ሀዘን በመሞላት ጊዜ የሚከሰት ነው። እንደዚሁም ልቅሶ ሰዎች የጸሐፊውን ውስጣዊ ጭንቀት እና ህመም እንዲሰማቸው ለመርዳት ተብሎ በጥንቃቄ የሚሠራ ነው።

የሰቆቃው ኤርምያስም መጽሐፍ የተጻፈውም ለዚህ ነው። የኢየሩሳሌምን ውድመት በተመልከተ የጸሐፊውን ሀዘን መግለጫ ነው። አንባቢው የጸሐፊውን ህመም እንዲሰማው ተፈቅዶለታል። ይሁን እንጂ ይህ የአንድ ሰው ሀዘን ሥነ ጥበባዊ መግለጫ ብቻ አይደለም። ሰቆቃው ኤርምያስ የመላው እሥራኤል ሀዘን ጥበባዊ መግለጫ ነው። ይህ የወል ልቅሶ ነው (ይህም ማለት ሁሉም የእግዚአብሔር ሰዎች የተጋሩት የሀዘን ልቅሶ ነው ማለት ነው)።

ሰቆቃው ኤርምያስ ውስጥ የሚጀምረው “እንዴት” በሚል ቃል ነው። እዲያውም ሰቆቃው ኤርምያስ ምዕራፍ 1፣ 2፣ እና 4 ሁሉም የሚጀምሩት “እንዴት” በሚለው ቃል ነው።

*ሕዝብ ምልቶባት የነበረች ከተማ*

*ብቻዋን እንዴት ተቀመጠች!* **ሰቆቃው ኤርምያስ 1፡1**

*ጌታ በቁጣው*

*የጽዮንን ሴት ልጅ እንደ ምን (እንዴት) አደመናት!* **ሰቆቃው ኤርምያስ 2፡1**

*ወርቁ እንዴት ደበሰ!*

*ጥሩ ወርቅ እንዴት ደበሰ!* **ሰቆቃው ኤርምያስ 4፡1**

“እንዴት” የሚለው የዕብራይስጥ ቃል ወደ አማርኛ ፊደላት ሲተረጎም “ኢቻ” ይባላል። ይህ አይሁዳውያን አንዳንድ ጊዜ ሰቆቃው ኤርምያስን “የኢቻ ጥቅልል” ( የእንዴት ጥቅልል”) ብለው እንደሚጥሩት ያብራራል።

በሰቆቃው ኤርምያስ ውስጥ አምስት ግጥሞች አሉ። አምስቱም ግጥሞች አንድ ወጥ በሆነ ሁኔታ የተዋቀሩ ስለሆኑ በግልጽ አንድ ላይ ናቸው ማለት ነው። በመጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ግጥሞች የተጻፉት በ586 ዓክልበ በባቢሎናውያን አማካይነት የኢየሩሳሌምና የቤተ መቅደሱ በፍጹም መውደም ተከትሎ ነው።

በሰቆቃው ኤርምያስ ውስጥ የሚገኙትን ልቅሶዎች በዚህ ዘመን በሚኖሩ አይሁዶች በአብ ወር በዘጠነኛው ቀን ይነበባል። ይህም በሐምሌ ወር ላይ የሚከበረው የአይሁድ የጾም ቀን ነው። ሰቆቃው ኤርምያስ የሚነበበው በ586 ዓክልበ በባቢሎናውያን የተፈጸመውን የኢየሩሳሌምን ውድቀት ለማሰብ፣ በ70 ዓ/ም በሮማውያን የተደረገውን የኢየሩሳሌም ወድቀት ለማስታውስ እና እንደዚሁም ሌሎችም በአይሁድ ሕዝብ ላይ የተከሰቱ አደጋዎችና ጥፋቶች ለምሳሌ በ20ኛው ክፍለ ዘመን በአይሁዳውያን ላይ የተፈጸመውን እልቂት በማስታውስ ይነበባል።

በተለምዶ ሰቆቃው ኤርምያስ ከነቢዩ ኤርምያስ ጋር የተያያዘ ነው። በዘመናዊው የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱሶች ውስጥ የሰቆቃው ኤርምያስ መጽሐፍ ከኤርምያስ በኋላ ወዲያውኑ የተቀመጠበት አንዱ ምክንያት ይህ ነው። ሴፕቱጀንት (አንዳንድ ጊዜም LXX ተብሎ የሚጠራው) መጽሐፍ ቅዱስ **በሰቆቃው ኤርምያስ 1፡1** ላይ ኤርምያስን የመጽሐፉ ደራሲ እንደሆነ ያመላክታል። በእርግጥ ኤርምያስ የመጽሐፉ ደራሲ ሊሆን ይችላል። በአገልግሎት በነበረባቸው ዓመታትም ብዙ መከራ ተጋፍጧልና። የኢየሩሳሌምንም ውድመት ተመልክቷል። ስለዚህ ኤርምያስ በዚህ መጽሐፍ በሥዕል 20 የሚታየውን ልቅሶ ጠንቅቆ ያውቅ ነበር ማለት ይቻላል። ነጉሥ ኢዮሲያስ ሲሞት እንኳ ለንጉሡ ለኢዮስያስ “የልቅሶ ግጥም እንደ ገጠመለት” ይተርካል (2 ዜና 35፡25 ይመልከቱ)። በኢየሩሳሌም ላይ ሊመጣ ስለነበረው ጥፋት ሕዝቡ “እንዲያለቅሱ” ይጠራቸው ነበር (**ኤርምያስ 4፡8፣ 6፡26፣ 7፡29፣ 9፡20፣** እና **49፡3** ይመልከቱ)። ይህም ኤርምያስ የሰቆቃው ኤርምያስ ደራሲ እንደሆነ ይጠቁማል። ይሁን እንጂ ደራሲው ኤርምያስ መሆኑን በእርግጠኛነት መናገር አይቻልም።

ሰቆቃው ኤርምያስ የተጻፈው በየትኛውም ነብይ ቢሆን ደራሲው እግዚአብሔርን የሚወድ፤ በእግዚአብሔርም ቸርነት ላይ እምነት እንደነበረው ይታያል (**ሰቆቃው ኤርምያስ 3፡22–24** ይመልከቱ)። ደራሲው የእግዚአብሔርን ቦታ እንደሚወድና የእግዚአብሔርንም ሕዝብ ወደዚያ ቦታ ሲመለሱ ለማየት እንደሚፈልግ ግልጽ ነው።

የሰቆቃው ኤርምይስ ገጣሚ የግጥም ተሰጥኦ ያለው ገጣሚ ነው። እያንዳንዱ አምስቱ ግጥሞች በጥንቃቄ የተሠሩ ናቸውና። በመሠረቱ የመጀመሪያዎቹ አራት ምዕራፎች የተጻፉት **በቃላት ጨዋታ ንድፍ** ነው። በዚህ ልዩ ዘይቤ የግጥሙ የመጀምሪያ ቃል የሚጀምረው ከዕብራይስጥ ፊደላት በመጀመሪያው ፊደል ነው። በግጥሙ ውስጥ ያለው እያንዳንዱ አዲስ “ጥቅስ” የሚጀምረው በሚቀጥለው በዕብራይስጥ ፊደል ነው። በዕብራይጥ የፊደል ገበታ 22 ፊደላት አሉ። ስለዚህ የሰቆቃው ኤርምያስ ምዕራፍ 1፣ 2፣ እና 4 እያንዳንዳቸው 22 ቁጥሮች ቢኖራቸው አያስደንቅም። እያንዳንዳቸው እነዚህ ሦስት ግጥሞች ንድፉን እንደገና ይጀምራሉ። ለምሳሌ **ሰቆቃው ኤርምያስ 2፡1** የሚጀምረው በዕብራይስጥ የመጀመሪያው ፊደል ነው። **ሰቆቃው ኤርምያስ 2፡22** የሚጀምረው ደግሞ በዕብራይስጥ የመጨረሻው ፊደል ነው።

በቃላት ጨዋታ ንድፍ የተጻፍ ግጥሞች ለአንባቢ መልዕክት ያስተላልፋሉ። መልዕክቱ **የፍጹምነት** መልዕክት ይመስላል። ሰዎች ሁሉንም የፊደል ሆሄያት በሌሎች ቋንቋዎችም በመጠቀም መልዕክት ይልካሉ። ለምሳሌ በአማርኛ የዕብራይስጥ የመጀመሪያ ፊደል “አሌፍ” ነው። የመጨረሻው የዕብራይስጥ ፊደል ደግሞ “ታው” ነው። በዚህ መሠረት አንድ ሰው ስለ አንድ ርዕሰ ጉዳይ ሁሉንም ነገር ለማወቅ ከፈለገ፣ “ከ ሀ እስከ ፐ ያለውን ሁሉ አስተምረኝ” እንደሚል ሊሆን ይችላል። እነዚህ የሰቆቃው ኤርምያስ ግጥሞች የሚያደርጉት ይህንኑ ይመስላል። የእሥራኤልን ሕዝብ ሙሉ የሀዘን መግለጫዎች ናቸውና። የኢየሩሳሌምን አጠቃላይ ውድመት መግለጫዎች ናቸው። የእግዚአብሔር ሕዝብ በሰላም የሚኖርበት ቦታ በሙሉ ፍርሷል። ኢየሩሳሌምና በኢየሳሌም የነበረው ቤተመቅደስ ከዛ በኋል በሥፍራቸው አልነበሩምና።

የሰቆቃው ኤርምያስ ጸሐፊ ለኢየሩሳሌም ውድመት እግዚአብሔር ተጠያቂ አላደረገም። ነገር ግን እሥራኤል ኃጢአት እንደሠራችና በላይዋ ላይ የወረደው ቁጣ ሁሉ የሚገባት መሆኑን ያውቃል።

*“ኢየሩሳሌም እጅግ ኃጢአት ሠርታለች፤*

*ስለዚህ ረከሳለች፤*

*ያከብሯት የነበሩ ሁሉ*

*ኅፍረተ ሥጋዋን አይተዋታልና አቃለሉዋት፤*

*እርስዋም እየጮኸች ታለቅሳለች*

*ወደ ኋላም ዘወር አለች።*

*አደፍዋ በልብስዋ ዘርፍ ነበረ፤*

*ፍጻሜዋን አላሰበችም፤*

*ስለዚህ በድንቅ ተዋርዳለች*

*የሚያጽናናትም የለም፤*

*አቤቱ ጠላት ከፍ ከፍ ብሎአልና*

*መከራዬን ተመልከት!"* **ሰቆቃው ኤርምያስ 1፡8–9**

ይሁን እንጂ ጠንቃቃ አንባቢዎች ሰቆቃው ኤርምያስ 3 ከሰቆቃው ኤርምያስ 1፣ 2፣ እና 4 የተለየ መሆኑን ያስተውላሉ። በእርግጥ ይህም ምዕራፍ በዕብራይስጥ ውስጥ ያሉትን ፊደላት በመጠቀም የቃላት ጨዋታ ግጥም ዘዴ ይከተላል። ሆኖም ምዕራፍ 3 በ66 ቁጥሮች የተከፈለ ነው። በዚህ ልዩ ምዕራፍ በእያንዳንዱ ቁጥር መጀመሪያ ላይ ፊደላትን ከመቀየር (ማለትም እንደ ሰቆቃው ኤርምያ 1፣ 2፤ እና 4) ወደ ቀጣዩ የዕብራይስጥ ፊደላት መለወጥ የሚከናወነው በእያንዳንዱ ሶስተኛ ቁጥር መጀመሪያ ላይ ነው። ይህ ከፍ ያለ ንድፍ በምዕራፍ 3 ላይ ልዩ ትኩረት ይሰጣል። ከዚህ ውጪ ሰቆቃው ኤርምያስ 1፣2 እና 4 "እንዴት" (ኢቻ) በሚለው ቃል አይጀምርም።

ሰቆቃው ኤርምያስ 3 ለየት የሚያደርገው ምንድር ነው? በዚህኛው ምዕራፍ ውስጥ ጸሐፊው በከተማዋ ላይ በሚመጣው የእግዚአብሔር ቁጣ ላይ ያተኮረ አለምሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል። ከዚህ ይልቅ የእግዚአብሔር ቁጣ በራሱ ላይ እንዴት እንደ ወረደ የሚናገር ነው። የመጀመሪያው ጥቅስ ስለከተማው አይደለም። ነገር ግን የሚናገረው ስለ አንድ "መከራ ስላየ ሰው" ነው።

*በቁጣው በትር*

*መከራ ያየ ሰው እኔ ነኝ።*

*ከፊቱ አስወጣኝ*

*በብርሃን ሳይሆን በጨለማ እንድሄድ አደረገኝ።*

*በእርግጥ ቀኑን ሁሉ በመደጋገመም*

*እጁን በላዬ ላይ መለሰ።* **ሰቆቃው ኤርምያስ 3፡1** *(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)*

ይህ ምዕራፍ ልክ በመዝሙረ ዳዊት በብዙዎቹ መዝሙሮች እንደ ምንመለከተው አንድ ሰው ብቻውን ሲሰቃይ የሚያሳይ ምስል ነው። ይህ ሰው ወደ እግዚአብሔር ይጮኻል እናም እርሱም ይታደገዋል።

*"ጌታ ሆይ ለእኔ ተሟገተኸልኝ፤*

*ሕይወቴን ተቤዠህ።*

*እግዚአብሔር ሆይ በእኔ ላይ የተደረገውን ግፍ አየህ*

*ፍርዴን ፍረድልኝ!*

*በቀላቸውን ሁሉ በእኔም ላይ ያሰቡትን ዐድማ አየህ።*

*እግዚአብሔር ሆይ ስድባቸውን ሁሉ*

*በእኔ ላይ ያሰቡትን ዐድማ ሁሉ ሰማህ።*

*ይህም ቀኑን ሙሉ በእኔ ላይ*

*ጠላቶቼ የሚያውጠነጥኑትንና*

*የሚያሾካሹኩትን ነው።*

*ተመልከታቸው! ቆመውም ሆነ ተቀምጠው*

*በዘፈናቸው ይሳለቁብኛል።* **ሰቆቃው ኤርምያስ 3፡58–63** *(አዲሱ መደበኛ ትርጉም)*

መዝሙረ ዳዊትን ላነበቡ ሰዎች ይህ ዓይነቱ ግጥም በጣም ግልጽ መሆን አለበት። አንድ ሰው ብቻውን እንደሚሰቃይ ስናነብ ስለክርስቶስ ማሰብ አለብን። እነዚህ ልዩ የሰቆቃው ኤርምያስ ቃላት በሐዋሪያት ያልተጠቀሱ ቢሆንም ነገር ግን ሐዋሪያት ይህን የመሰለ ቅኔ ከመዝሙረ ዳዊት ሲጠቅሱና ግጥሞቹንም ስለክርስቶስ ሲተገብሩ ይስተዋላል። ሰቆቃው ኤርምያስ እንደ መዝሙረ ዳዊት ከሆነ ይህም

ማለት የሰቆቃው ኤርምያስ ቁልፍ ክፍል ወደ ክርስቶስ መከራና ከመከራውም ወደ መዳን ትኩረት እየሳበን ነው ማለት ነው።

ነገር ግን የክርስቶስ መከራና መዳን ስለ ኢየሪሳሌም ጥፋት በሚናገረው መጽሐፍ መካከል የሆነው ለምንድር ነው? መልሱ በመላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሊታይ ይችላል! አስተዋይ አንባቢ በዚህ ነጥብ መረዳት ያለበት የክርስቶስ መከራ እና ነጻ መውጣት ለእግዚአብሔር ሕዝብ መፈጠር እና ለእግዚአብሔር ሕዝብ አስተማማኝ ቦታ መመስረት ቁልፍ ነው! ያለ እሱ መከራና መዳን "አዲስቷ" ኢየሩሳሌም አትኖርም።

ሰቆቃው ኤርምያስ በምዕራፍ 5 ላይ በጸሎት ይደመድማል። ይህ ምዕራፍ በቃላት ጨዋታ ዘይቤ አልጻፈውም። ፀሐፊው ለምን እዚህ ላይ ሲደርስ ንድፉን እንደለወጠ አይናገርም። ፀሐፊው ንድፉን ረስቶት እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ምዕራፉ በጥንቃቄ የተደረደረ ሲሆን አንባቢው የዕብራይስጥ ፊደላትን እንዲያስታውስ ታስቦ ይመስላል። ምክንያቱም በሰቆቃው ኤርምያስ 5 ላይ 22 ቁጥሮች አሉ፤ ደግሞም የዕብራይስጥ ፊደላት 22 ናቸው፤ ስለዚህ ይህ ግልጽ ያደርገዋል። ሰቆቃው ኤርምያስ 5 ከሌሎቹ የሰቆቃው ኤርምያስ ምዕራፎች ጋር እንደሚስማማ ግልጽ ነው። በሌላ መልኩ ደግሞ የተልየም ነው። ደራሲው በዕብራይስጥ ፊደላት ውስጥ ያሉትን ፊደሎች እዚህ ላለመጠቀም የወሰነው ለምንድር ነው? ምናልባትም አንባቢዎቹ እንዲጸልዩ ስለሚፈልግ ይሆናል።

ያለፉትን ምዕራፎች ያስታውሱ በሙሉነት ላይ አጽናዖት ይሰጣሉ። ይህም የዚህ ዓይነቱ የቃላት ጨዋታ ምልክት ይመስላል። ምክንያቱም በዕብራይስጥ ፊደላት የመጀመሪያ ፊደል ጀምረው በመጨረሻም የዕብራይስጥ ፊደላት ስለሚጨርሱ የተሟላ መልዕክት ላይ ያተኩራሉ።

ይህ ጸሎት ግን ሙሉ አይደለም። ቅዱሳኑ ለኢየሩሳሌም መመሥረት መጸለይን መቀጠል አለባቸው። ለዚህ ሊሆን ይችላል ደራሲው የቃላት ጨዋታ ንድፍ እዚህ ላይ የማይጠቀምበት። ቅዱሳን መጸለይ አለባቸውና። ስለ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም መመሥረት የቅዱሳን ጸሎት መቀጠል አለበት።

በሰቆቃው ኤርምያስ ውስጥ ያሉትን ግጥሞች በጥንቃቄ ማሰላሰል ትልቅ ዋጋ አለው። የዚህን መጽሐፍ የቅርብ ጥናት አምስት ጥቅሞች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. **ይህ መጽሐፍ ክርስቲያኖች የኃጢአትን ክብደትና የእግዚአብሔርን ቃል እውነትነት ያሳስባቸዋል።** እግዚአብሔር እሥራኤልን በጣዖት አምልኮት ኃጢአታቸው ምክንያት ቀጥቷቸዋል (**ሰቆቃው ኤርምያስ 1፡5** ይመልከቱ)። ቀደም ሲል በሙሴ ሕግ ሕዝቡ ጣዖትን ቢያመልኩ ይህ እንደሚደረግባቸው አስጠንቅቆዋቸው ነበር (**ዘዳግም 4፡15–28** ይመልከቱ)። ሰቆቃው ኤርምያስ

እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ቃሉን እንደሚጠብቅ ያሳያል። እንደዚሁም ዛሬም ሰዎች እግዜብሔር እንደማይለወጥ ማወቅ አለባቸው።

2. ***ሰቆቃው ኤርምያስ ለክርስቲያኖች ይህን ዓለም መኖሪያቸው እንዳልሆነ ያስታውሳል። ከዚህኛው ዓለም ይልቅ የላይኛቱን ኢየሩሳሌም መወደድና ዋጋ መስጠት እንዳለባቸው ያሳስባል።*** ደራሲው ለኢየሩሳሌም ያለውን ጥልቅ ፍቅር በግጥሙ ውስጥ ማየት ቀላል ነው። ነገር ግን ኢየሩሳሌም ስትፈርስ ሕይወቱ ተረባብሾዋል። ዛሬ አማኞች ግን ስለ እውነተኛ ከተማቸው አያስቡም። የኢየሩሳሌም ጥልቅ ፍቅርና በመጨረሻም ወደ ቤት የመሄድ ጉጉት በዚህ ዘመን በሁሉም አማኞች ውስጥ መሆን አለበት (***መዝሙር* 137፥6** እና ***ገላትያ* 4፥26** ይመልከቱ)። በዚህ ዘመን ያሉ አማኞች "አዲሲቷን ኢየሩሳሌም" እየጠበቁ ናቸው። በእርግጥ አዲስቷ ኢየሩሳሌም "የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ከተማ" ስለሆነች በሰቆቃው ኤርምያስ ዘመን ሕዝቡ ምድራዊ ኢየሩሳሌምን ከወደዳት ይልቅ አዲሲትዋን ኢየሩሳሌምን ልንወድ እና ልንከባከብ ይገባናል። ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ዋና ጭብጥ ነው (***ዕብራውያን* 11፥9–16፤ 12፥22–24** እና ***ራዕይ* 21፥1–22፥5** ይመልከቱ)። የሰቆቃው ኤርምያስ መጽሐፍ ለአዲስቷ ኢየሩሳሌም ያለንን ፍቅር ለመጨመር ልንጠቀምበት እንችላለን።


3. ***የኢየሩሳሌምና የቤተ መቅደሱ ጥፋት የክርስቶስን መገደል ትንሽ ምስል ነው።*** ስለዚህም ደራሲው ኢየሩሳሌም በወደመች ጊዜ የተሰማው ከፍተኛ ሀዘን ዓይነት ኢየሱስ ሲሞት የኢየሱስ ተከታዮች ተስምቷቸው ነበር። ለዚህም ነው (በ***ሰቆቃው ኤርምያስ* 2፥15**) ላይ ያለውን ቃል በክርስቶስ ስቅለት ጊዜም (**በ*ማርቆስ* 15፥29**) ላይ በተመሳሳይ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለው። ማርቆስ አንባቢዎቹን የክርስቶስን ስቅለት ሲያስቡ ሰቆቃው ኤርምያስንም እንዲያነቡ የሚፈልግ ይመስላል!


4. ***በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን ልቅሶዎች የእግዚአብሔርን ሕዝብ ወደ ምስጋና ሊመራው ይገባል።*** ነገሩ እንግዳ ሊመስል ይችላል ነገር ግን ጥልቅ ልቅሶ ወደ ጥልቅ ደስታና ምስጋና ሊመራ ይችላል። ጸሐፊው በእውነት "መሰማት" የተሰማውን ሥቃይ ዛሬ አማኞች የሚሰማቸውን ምስጋና መጨመር አለበት። ኢየሩሳሌም ለዘለለም አትጠፋም! እግዚአብሔር በሰቆቃው ኤርምያስ 5 (እና በሌሎችም ብዙ ቦታዎች) የተጸለዩትን ጸሎቶች ሰምቷልና። ስለዚህ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ መሠረትዋ የጸና ከተማ አለችን!

5. ***ይህ መጽሐፍ በክርስቶስ ዳግም ምጽአት የሚመጣውን ሙሉ ድል ያስታውሰናል።*** ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው ሀዘንና እንባን ሁሉ ለማስወገድ ነው። ሆኖም እስከ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት

ድረስ ሀዘን የሕይወት አንዱ ክፍል ይሆናል።ይህ የልቅሶ መጽሐፍ ልቅሶ የማይኖርበትን መጪውን ቀን ያስታውሰናል። በዚያ ቀን ልቅሶዎች  እንኳን ወደ ደስታ የክርስቶስ ድል መታሰቢያ መዝሙር ይቀየራሉ።

> *እንባዎችንም ሁሉ ከዓይናቸው ያብሳል፤ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም ኀዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፤ የቀደመው ሥራዓት አልፎአልና ብሎ ሲናገር ሰማሁ።* **ራዕይ 21፥4**





## 21. ዳንኤል በባዕድ አገር ለሚኖሩ ታማኝ ሰዎች ተስፋ ሰጥቷል

ዳንኤል ነቢይ ቢሆንም የዳንኤል መጽሐፍ ግን በብሉይ ኪዳን ነቢያት ተብሎ በሚጠራው ክፍል ውስጥ አይገኝም። ይልቁንም ዳንኤል ከጽሑፎች መደዳ ነው የተደረደረው። ነገር ግን ዳንኤል ከጽሑፎች ጋር የተደረደረው ለምንድር ነው? ትንቢተ ዳንኤል በጽሑፎች ውስጥ እንዲገኝ ካድረጉት ምክንያቶች አንዱ ዳንኤል በግዞት ለሚኖሩ የእግዚአብሔር ታማኝ ሕዝቦች ተስፋ ስለሚሰጥ ነው። ይህ ዓይነቱ የዳንኤል ገጽታ በአስቴር መጽሐፍ ውስጥ ካለው መልዕክት ጋር በጣም ተመሳሳይ ነው።

የዳንኤል መጽሐፍ በጽሑፎች "ትረካ" ክፍል ውስጥ የመጀመሪያው መጽሐፍ ነው። በዚህ የጽሑፍ ክፍል ውስጥ አራት መጻሕፍት አሉ ዳንኤል፣ አስቴር፣ ዕዝራ ነህምያ (ዕዝራና ነህምያ በመጀመሪያ እንደ አንድ መጽሐፍ ነበሩ) እና ዜና መዋዕለ (የዜና መዋዕለ መጽሐፍም በመጀመሪያ እንደ አንድ መጽሐፍ ነበር)።

በዚህ የጽሑፍ ክፍል ውስጥ ያሉት የመጀመሪያዎቹ ሦስት መጻሕፍት በጊዜ ቅደም ተከተል የተቀመጡ ናቸው። በዚሁ መሰረት ዳንኤል የመጀምሪያ ነው፤ ምክንያቱም በዳንኤል ውስጥ የተመዘገቡት ድርጊቶች መጀመሪያ የተፈጸሙ በመሆናቸው ነው። መጽሐፈ አስቴር ደግሞ በሁለተኛነት ተደርድሯል ምክንያቱም በመጽሐፈ አስቴር የተመዘገቡት ድርጊቶች በሁለተኛነት ስለሚከተሉ ነው። ዕዝራ ነህምያ ደግሞ ሦስተኛ ነው፤ ምክንያቱም በዕዝራ ነህምያ ላይ የተመዘገቡት ነገሮች በመጨረሻ የተፈጸሙ በመሆኑ ነው። ዜና መዋዕል መጨረሻ የሆነው በተለያዩ ምክንያቶች ነው። ደግሞም በብሉይ ኪዳን እየተነገረ ያለው ታሪክ ማጠቃለያ ነው። ከዚህ ባሻገር ዜና መዋዕል ለአዲስ ኪዳን "ድልድይ" ይሆናል።

የዳንኤል መጽሐፍ ልክ እንደ አስቴር መጽሐፍም ሙሉ በሙሉ ከእሥራኤል ምድር ውጪ የተፈጸመ ነው። እነዚህ ሁለት መጽሐፍት ከእግዚአብሔር መልካም ሥፍራ ውጪ ቢኮን እንኳን እንደ ታማኝ የእግዚአብሔር ተከታይ መኖር እንደሚቻል ያረጋግጣሉ። "ባዕድ" በሆነ አገር ውስጥ እንኳን የእግዚአብሔር ሰዎች ከጌታ እርዳታ እና ሞገስ እንደሚያገኙ መጠበቅ አለባቸው። ይህም ዛሬ በምድር ላይ ላለ አማኝ ሁሉ ይሠራል። እኛ "ተበታትነን" የምንኖር መጻተኞች እና እንግዶች ነን ( **ያዕቆብ 1፡1** እና **1 ጴጥሮስ 1፡1** ይመልከቱ)።

አይሁዳውያን ከምድሪቱ ፈልሰው በግዞት በነበሩበት ወቅት ለተወሰነ ጊዜ በባቢሎን አገዛዝ ሥር ኖረዋል። በዳንኤል 1–5 ላይ የተመዘገቡት ክንውኖች የተፈጸሙት በባቢሎን ዘመን ነው። ባቢሎን በዚህ

ጊዜ እጅግ ኃያል መንግሥት ነበረች። ይሁን እንጂ በዳንኤል ሕይወት መገባደጃ ላይ ባቢሎን በፋርስ መንግሥት ሥር ወደቀች። በዳንኤል 6 ላይ የተመዘገቡት ክስተቶች የተከናወኑት የፋርስ መንግሥት በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ በሚገዛበት ዘመን ነበር። ደግሞም ፋርስ በዓለም ላይ እጅግ ኃያል መንግሥት ሆነ። በዳንኤል 7 እና 8 ላይ ተመዝግበው የሚገኙት ራዕዮች ባቢሎን በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ በሚገዛበት ዘመን ለዳንኤል የተገለጠ እውነት ነበር። በዳንኤል 9–12 ላይ የተጻፉት ራዕዮች ደግሞ ፋርስ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ በሚገዛበት ዘመን ለዳንኤል የተገለጠ ነው። ለእግዚአብሔር ሕዝብ ከዳንኤል የተሰጠው ትምህርት ቢኖር ምድራዊ መንግሥታት የሚነሱና የሚወድቁ መሆናቸውን ነው የእግዚአብሔር መንግሥት ግን ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።

የዳንኤል መጽሐፍ በሁለት ይከፈላል። እያንዳንዱ ክፍል ስድስት ምዕራፎች አሉት። የመጀመሪያው ስድስት ምዕራፎች በትረካ መልክ የተጻፉ ናቸው። ይህም ከምዕራፍ 1–6 በታሪኮች የተሞሉ ናቸው ማለት ነው። የዳንኤል ሁለተኛው ክፍልም ስድስት ምዕራፎች አሉት፤ ከምዕርፍ 7–12 ማለት ነው። በዚህ ክፍል ለዳንኤል የተገለጠው የራዕዮቹ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ናቸው።

ከምዕራፍ 1–6 እና 7–12 መካከል ባለው ከፍተኛ የአጻጻፍ ለውጥ ምክንያት የዳንኤል መጽሐፍ አንባቢዎችን ግራ ሊያጋባ ይችላል። የዳንኤል የመጀመሪያ ክፍል በታሪክ የተሞላ በመሆኑ ከዳንኤል ሁለተኛ ክፍል ይልቅ ለመረዳት ቀላል ነው። አንባቢዎች ግን ሁቱንም የዳንኤል ክፍሎች በጥንቃቄ ማጥናት አለባቸው። እንደ እድል ሆኖ የመጽሐፉን ዋና ነጥብ ለመረዳት በምዕራፍ 7–12 ያሉትን ራዕዮች እያንዳንዱን ገጽታ መረዳት አስፈላጊ አይደለም። የዳንኤል የመጀመሪያ አጋማሽ ታሪኮች ለብዙ ምክንያቶች ጠቃሚ ናቸው። ከእነዚህም ጥቂቶቹ እንደሚከተሉት ናቸው።

— በዳንኤል 1–6 ያሉት ታሪኮች እግዚአብሔር ሕዝቡ በባዕድ አገር በሚኖሩበት ጊዜም ቢሆን እንደሚያስብላቸው እና ለሕዝቡም እርዳታ እንደ ሚያደርግላቸው ያሳያሉ።

— በዳንኤል 1–6 ላይ ያሉትን ታሪኮች ለእግዚአብሔር ሰዎች የመጸለይ አስፈላጊነት ያሳያሉ።

— ታሪኮቹ የእግዚአብሔር ሕዝብ እሱን እንዲታዘዙ፤ ቢታዘዙ ደግሞ ለእግዚአብሔር ታማኝ በመሆን መቀጠል እንደሚችሉ ያሳያሉ። እነዚህ ታሪኮች የእግዚአብሔር ሕዝቦች ሁልጊዜ ከጠላቶቻቸው እንደሚድኑ ዋስትና አይሰጡም። ይልቅስ እነዚህ ታሪኮች የእግዚአብሔር ሕዝብ ምንም እንኳን የከፋ መከራ ውስጥ ቢገባም እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር እንደሚሆን ያስረዳሉ። በመጨረሻም

የእግዚአብሔር ሰዎች ቢገደሉ እንኳ በእግዚአብሔር ይድናሉ ምክንያቱም የክርስቶስ ድል በሁሉም ነገር ላይ ነውና። በሞት ላይ እንኳን ሳይቀር ማለት ነው።

— በዳንኤል 1–6 ላይ ያሉትን ታሪኮች በዚህ ዘመን ያሉ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ሊከተሉዋቸው የሚገቡትን የታማኝነትና የጽናት ምሳሌዎች ናቸው።

— በዳንኤል 1–6 ላይ ያሉት ታሪኮች እግዚአብሔር በኃያላን ነገሥታትና በዓለም መንግሥታት ሁሉ ላይ የበላይ ሆኖ እንደሚገዛ ያረጋግጣሉ። እነዚህ ታሪኮች እግዚአብሔር ነገሥታትን የሚያስነሣ እርሱ እንደሆነና ደግሞ ነግሥታትንም የሚሽር መሆኑን ያኅላሉ። ከእግዚአብሔር በላይ የሆነ ምንም ኃይል የለም። የእግዚአብሔር ሰዎች ማስታውስ ያለባቸው የሰማዩ መንግሥት ሁሉንም ነገር የሚገዛ መንግሥት መሆኑን ነው።

— በዳንኤል 1–6 ያሉት ታሪኮች እግዚአብሔር የታሪክ እቅዶች እንዳለው ያረጋግጣሉ። ክፋት ለምንጊዜውም ቢሆን አያሸንፍም። የእግዚአብሔር መንግሥት በመጨረሻ ሁሉንም ይገዛል። አማኞች በዚህ ረገድ እንደ ዳንኤል ናቸው። በስደት አገር እየኖሩ ወደ እውነተኛ ቤታቸው ለመመለስ እየጠበቁ ናቸውና።

በዳንኤል 2 ላይ ያለው የንጉሥ ናቡከደነፆር ራእይ በጣም ጠቃሚ ነገር ነው። ነገሩ በከበሩ ማዕድናት ስለተሰራ ግዙፍ ሐውልት ራእይ ጉዳይ ነው። ሐውልቱ የተለያዩ ምድራዊ መንግሥታትን የሚወክል ነበር። በመጨረሻም ሐውልቱ ከተራራ ላይ ተፈንቅሎ በተወረወረ ድንጋይ ተመቶ ተሰባበረ ተፈጨም በአውድማ ላይ እንደ ደቀቀ በነፋስም እንደሚወሰድ እብቅ ሆነ። እብቅ በነፋስ እንደሚወሰድ የሐውልቱም ብናኝ እስከ ማይገኝ በነፋስ የተወሰደ ሆነ። ምስሉን የመታው ደንጋይ ግን አልተሰበረም ይልቅስ እንደ “ታላቅ ተራራ ሆነ ምድርንም ፈጽሞ ሞላ።”

የዚህ ራእይ ዋና ነጥብ ሁሉም ምድራዊ መንግሥታት ምንም ያህል ሀይለኛ ቢመስሉም ይወድቃሉ። የተለያዩ የምድር መንግሥታት ይነሳሉ ደግሞም ይወድቃሉ። በመጨረሻም ሁሉም ምድራዊ መንግሥታት “ከዚህ ዓለም ባልሆነ” መንግሥት ይጠፋሉ። ይህ ራእይ የእግዚአብሔር መንግሥታት በሁሉም መንግሥታት ላይ እንደሚገዛ ያረጋግጣል። በዚህ ራእይ ውስጥ ዋና ነገር ሐዋልቱን የሰባበረው ድንጋይ ነው። ሐውልቱ ልክ እንደ ውድ ማዕድናቶች መንግሥት ነበር። ነገር ግን ከሌሎች መንግሥታት በተለየመለኩ ከተራራ የተፈነቀለው አለት መላውን ዓለም ይገዛል። ጠንቃቃ አንባቢዎች ስለ ክርስቶስና

እና ስለ መንግስቱ ሁኔታ በተነገሩ ሊሎች ነገሮች ላይ በመመሥረት ይህ ከተራራ የተፈነቀለው አለት የክርስቶስ እና የመንግሥቱ ምልክት መሆን እንዳለበት ይገነዘባሉ። በሐውልቱ ውስጥ ተወክለው የነበሩቱ ሁሉንም የዓለም መንግሥታት ማወቅ አስፈላጊ አይደለም። ነገር ግን ሐውልቱን የሰባበረው ድንጋይ ክርስቶስና ሕዝቡ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል!

ይህ ራእይ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ታላቅ ማበረታቻ ሊያመጣ ይገባል። የእግዚአብሔር ሕዝብ በባዕድ ኃይሎች ሥር ለዘላለም አይኖርምና። አማኞች መከራ ቢደርስባቸውም መከራቸው ጊዜያዊ እንደሆነ በመገንዘብ ሊበረታቱ ይገባቸዋል።

ከዚህ በተጨማሪ ይህ ራእይ ለዓለም ኃያላን መንግሥታት ማስጠንቀቂያ ሊሆን ይገባል። “አገዛዛቸው” ጊዜያዊ መሆኑን ማወቅ አለባቸው። ንሰሐም በመግባት በእግዚአብሔር ፊት በትሕትና ሊመላለሱ ይገባቸዋል።

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት እንደተናገሩት ይህ በዳንኤል 2 ላይ ያለው ራእይ ከሰው እይታ አንጻር ይመስላል። ነገሩ በናቡከደነፆር ላይ ታይቷል። የዓለም መንግሥታት በከበሩ ማዕድናት የሚወከሉት ለዚህ ነው። ናቡከደነትፆር ያሰራው ሐውልት ውድ መስሎ መታየቱ አልቀረም።

ይህ ራእይ በዳንኤል 7 ላይ ተደግሟል ማለት ይቻላል። ነገር ግን በዳንኤል 7 ራእዩ የተነገረው ለዳንኤል እንጂ ለናቡከደነፆር አይደለም። ዳንኤል የዓለምን መንግሥታት በሰማያዊ እይታ ሲመለከት፤ ለእርሱ ውድ አልነበሩም። ይልቁንም እንደ አውሬዎች ነበሩ እንጂ።

በዚህ ራእይ ውስጥ ያሉት የዓለም ኃያላን በከበሩ ማዕድናት አይወከሉም ደግሞም ውብ አይደሉም። ይልቁንም በተለያዩ አውሬዎች ተመስለዋል። ራእዩ የሚያጎላው በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የሚገዙት ምድራዊ መንግሥታት ልክ እንደ ከበሩ ማዕድናት ውድና ውብ እንዳልሆኑ ያሳያል። ይልቁንም በአውሬ ተመስለው ነው የቀረቡት። አውሬዎች ጥርሳቸውና ጥፍራቸው ለማድቀቅ፣ ለመቅደድ፣ ለመፍጨት እንደሚጠቀሙ ሁሉ። እንደ አራዊት የሆኑ የምድር መንግሥታት በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩትን ሰዎች አድቅቀው፣ ቀድደው፣ ቀጥቅጠው ይገዛሉ።

በዳንኤል 2 ላይ አንድ ድንጋይ ሐውልቱን አወደመው። በዳንኤል 7 ደግሞ “የሰው ልጅ” የተባለው አራዊቱን አሸንፏል። ይህ የሰው ልጅ ማን ነው? የአዲስ ኪዳን አንባቢዎች ኢየሱስ እንደሆነ ያውቃሉ። ኢየሱስ ለራሱ የሚወደውን ስም “የሰው ልጅ” የሚለው አንዱ ምክንያት ይህ ነው። ሆኖም የዳንኤል 7 አጋማሽ ግልጽ እንደሚያደርገው “የሰው ልጅ” ኢየሱስ ብቻውን አይደለም። በእርሱ ውስጥ ያሉትንም ሁሉ

ይጨምራል። ለዚህም ነው የዳንኤል 7 ሁለተኛ አጋማሽ የእግዚአብሔር ሰዎች መንግሥት ሲቀበሉ የሚያሳየው።


የዳንኤል የመጀመሪያ አጋማሽ እና የዳንኤል ሁለተኛ አጋማሽ የተለያዩ ቢሆኑም የተገናኙ መሆናቸውን ማየት ያስፈልጋል። ዳንኤል 2 እና ዳንኤል 7 በጣም ተመሳሳይ መሆናቸው ይህንን ያረጋግጣል። ሁለቱም የዳንኤል ክፍሎች እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን እቅድ ያሳያሉ። ሁለቱም ክፍሎች እግዚአብሔር በነገሥታትና በመንግሥታት ላይ እንደ ሚገዛ እና ለሕዝቡ እንደሚያስብ ያሳያሉ። ሁለቱም ክፍሎች ቅዱሳን እስከ መጨረሻው መጽናት እንደሚያስፈልጋቸው ያሳያሉ። እግዚአብሔር ብቻውን በሁሉ ላይ የሚነግሥበት ቀን ይመጣልና።


በዳንኤል 8–12 ላይ ሌሎች ራእዮች አሉ። እነዚህ ራዕዮች በዳንኤል 1–6 ካሉት ታሪኮች የበለጠ ለመረዳት አዳጋች ናቸው። ምክንያቱም ራእዮቹ የተጻፉት አንዳንድ ጊዜ "የምጻዓት ሥነ-ጽሑፍ" ተብሎ በሚታወቀው ዘይቤ ነው። ይህ ኣይነቱ አጻጻፍ ብዙውን ጊዜ እንግዳ ምልክቶችን፣ ፍጥረታትን፣ ቁጥሮችን እና ክስተቶችን የሚጠቀም የሥነጽሑፍ ዓይነት ነው።

ኢየሱስ፣ ጳውሎስ፣ እና ሐዋሪያው ዮሐንስ በመጨረሻዎቹ ነገሮች ላይ በሚያስተምሩበት ጊዜ ዳንኤልን ተጠቅመውበታል። በተለይም የራዕይ መጽሐፍ ደጋግሞ ዳንኤል የተናገረውን ያካትታል። ስለዚህ የዳንኤልን ትንቢት መረዳት በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስላሉቱ አስቸጋሪ ምንባቦች የበለጠ ግንዛቤ ይሰጣል። የዳንኤል መጽሐፍ መረዳት ወደ ተሻለ ግንዛቤ ይመራል። መጽሐፉንም የሚያሰላስሉ ሰዎች ጽናትን ያስገኝላቸዋል። ታሪኮቹንና ራእዮቹንም በሚያጠኑ ሰዎች ላይ ተስፋን ይፈጥራል። ደግሞም መከራን በትግስት ለመቋቋም ድፍረትን ያጎናጽፋል።

የዳንኤል የመጨረሻው ምዕራፍ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ከባድ መከራ እንኳ ቢኖር መቋቋም እንደሚያስፈልጋቸው ያስጠነቅቃል። ይሁን እንጂ "ጥበበኞች የሆኑት" ይድናሉ።

> *በዚያም ዘመን ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል፤ ሕዝብም ከሆነ ጀምሮ እስከዚያ ዘመን ድረስ እንደ እርሱ ያለ ያልሆነ የመከራ ዘመን ይሆናል፤ በዚያም ዘመን በመጽሐፉ ተጽፎ የተገኘው ሕዝብህ ሁሉ እያንዳንዱ ይድናል። በምድርም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉቱ ብዙዎች ይነቃሉ፤ እኩሌቶቹ ወደ ዘላለም ሕይወት እኩሌቶቹም ወደ እረፍትና ወደ ዘላለም ጉስቁልና። ጥበበኞቹም እንደ ሰማይ ፀዳል ብዙ ሰዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉ።* **ዳንኤል 12፡1–3**





## 22. መጽሐፈ አስቴር የእግዚአብሔርን ሰዎች እግዚአብሔር ሁልጊዜ እንደሚሠራ የሚያበረታታ መጽሐፈ ነው፤ እግዚአብሔር እንደሚሠራ "ማየት" በማይቻልበት ዘመን እንኳን ይህን እያደረገ እንደሆነ ይናገራል

የአስቴር መጽሐፍ የአይሁድ ሕዝቦች በግዞት ይኖሩ በነበረበት ወቅት የተፈጸሙትን ሁኔታዎች ይገልጻል። የአይሁድ ሕዝብ ከአገራቸው በምርኮ ተወሰደው በሚኖሩበት ዘመን በሁለት የተለያዩ መንግሥታት ሥር ይኖሩ ነበር። ባቢሎናውያን በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ለተወሰነ ጊዜ ገዙ፤ እንደዚሁም ፋርሳውያንም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለተወሰነ ጊዜ ይገዙ ነበር።

በትንቢተ ዳንኤል ውስጥ የሚገኙትን አብዛኛቹ ክንውኖች የተፈጸሙት በባቢሎን ዘመን ነው። ይሁን እንጂ በዳንኤል ሕይወት መገባደጃ ላይ ባቢሎን በፋርስ መንግሥት እጅ ወደቀች። የፋርስ መንግሥት ባቢሎንን እንዲቆጣጠር ያስቻለው የድል ክስተቶች በዳንኤል 5 ላይ ተገልጸዋል። በዳንኤል 6 ላይ የተገለጹ ነገሮች ደግሞ የተፈጸሙት የፋርስ መነግሥት በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ በሚገዛበት ጊዜ ነበር።

በመጽሐፈ አስቴር ውስጥ ተመዝግበው የሚገኙ ነገሮች የተፈጸሙት ፋርስ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በሚገዛበት ዘመን ነው። ይህ ወቅት የእግዚአብሔር ሕዝብ ትልቅ አደጋ ውስጥ የወደቀበት ዘመን ነበር። በፋርስ ይኖሩ የነበሩ ሰዎች የእሥራኤልን አምላክ አያውቁም ነበር፤ ስለዚህ የእግዚአብሔር ሰዎች መዳን የዓለም ሕዝብ ሁሉ መድኃኒት እንደሚያመጣ አላስተዋሉም ነበር። አዳኙ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ወገን እንደ ሚመጣ የፋርስ መንግሥት አያውቅም ነበርና (ዘፍጥረት 12፡1–3 ይመልከቱ)። ስለዚህ በፋርስ መንግሥት ውስጥ አንዳንድ ሰዎች የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማጥፋት የሚፈልጉ ነበሩ። ቢሳካላቸው ለዓለሙ ሁሉ የሚሆነውን ተስፋ ያበቃለት ነበር፤ ምክንያቱም ለዓለሙ ሁሉ የሚሆነው በረከት መምጣት የነበረበት በእግዚአብሔር ሕዝብ በኩል ነበርና።

መጽሐፈ አስቴር የእግዚአብሔርን ስም ፈጽሞ አይጠቅስም። ይህም አንዳንድ ሰዎች መጽሐፈ አስቴር በመጽሐፍ ቅዱስ መካተት አለበት ወይ ብለው እንዲጠይቁ አድርጓቸዋል። አንድንድ ሰዎች ደግሞ ምናልባት ደራሲውስ እግዚአብሔርን የሚያውቅና የሚከተል ይሆን የሚል ጥያቄም አላቸው። ይሁን እንጂ ደራሲው እግዚአብሔርን እንደሚወድና እንደ ሚከተልም ግልጽ ነው። ደራሲው በእግዚአብሔር ኃይል ላይ ታላቅ እምነት ነበረው። ደራሲው የእግዚአብሔርን ስም ላለመጠቀም የመረጠበት ምክንያት

አንባቢዎቹ እግዚአብሔር በዓለም ላይ ስለሚሰራበት መንገድ ጠንክረው እንዲያስቡበት ፈልጎ ይሆናል። ምንም እንኳን እንግዳ ቢመስልም ደራሲው ግን የእግዚአብሔርን ስም ለመጥቀስ አልፈለገም፤ ምክንያቱም ሕዝቡን ወደ እግዚአብሔር አሠራርና እግዚአብሔር ሕዝቡንም የሚያድንበት መንገድ የበለጠ ትኩረት ለመሳብ የፈለገ ይመስላልና።

የመጽሐፈ አስቴር ደራሲ ለምን የእግዚአብሔርን ስም አልተጠቀመም? በመጽሐፈ አስቴር ዘመን የአይሁድ ሕዝቦች ይኖሩ የነበሩት በስደት "በባዕድ" አገር ነበር። በባዕድ ንጉሥ ስልጣን ሥር ነበር የሚተዳደሩት። ይኖሩ የነበሩትም የእሥራኤል አምላክ በማይታወቅበት ቦታ ነበር። መጽሐፈ አስቴር እግዚአብሔር ሕዝቡን "በባዕድ አገር" ሥልጣን ሥር በነበሩበት ጊዜም ሆነ ሌሎች "አማልክት" በሚመለኩባቸው ቦታዎች ቢሆን ለማዳን በትጋት የሚሠራ መሆኑን ያሳያል። ይህም ለእግዚአብሔር ሕዝብ ታላቅ መጽናናት ሊያመጣ ይገባል።

አስተዋይ አንባቢ በአስቴር መጽሐፍ ውስጥ ብዙ "አጋጣሚዎች" እንዳሉ ልብ ሊል ያስፈልገዋል። ነገሮች በትክክለኛው ጊዜ የተከሰቱ ይመስላሉ። እነዚህ "አጋጣሚዎች" በተደጋጋሚ ተከስተዋል። እንደነዚህ ዓይነት "አጋጣሚዎች" ባይኖሩ ኖሮ የእግዚአብሔር ሰዎች ይጠፉ ነበር! ይህም እንደገና ለዓለሙ ሁሉ አሳዛኝ ነገር ያስከትል ነበር! እስቲ የሚከተሉትን "አጋጣሚዎች" ያስተውሉ።

— መርዶኪዮስ ሰዎች ንጉሡን ለመግደል ሲያሴሩ ሰማ (**አስቴር 2፡19–23** ይመልከቱ)። በእርሱ ምክንያት በንጉሡ ላይ የተሴረውን ውጥን ከሸፈ። ይህም ክስተት "በንጉሡ ፊት በታሪክ መጽሐፍ ተጽፎ ተቀመጠ (**አስቴር 2፡23** ይመልከቱ)።

— የፋርስ ንግሥት ከዙፋንዋ ተወገደች። አስቴር ደግሞ ንግሥት የተደረገችው የእግዚአብሔር ሕዝብ ከባድ የጥፋት አደጋ በተጋረጠበት ትክክለኛ ወቅት ላይ ነበር። በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር ሕዝብ እነሱን ወክሎ በንጉሥ ፊት የሚናገርላቸው ሰው እጅግ በጣም የሚያስፈልጋቸው ጊዜ ነበር (**አስቴር 4፡13–14** ይመልከቱ)።

— የአይሁድ ሕዝብ ጠላት የሆነው ሐማን መርዶክዮስን ለመግደል ዕቅድ አወጣ (**አስቴር 5፡ 9–14** ይመልከቱ)። ሆኖም መርዶኪዮስን ለመግደል በታሰበው በዛው ሌሊት ንጉሡ እንቅልፍ ሊወስደው ስላልቻለ "የታሪክ መዛግብት" እንዲነበብለት ጠየቀ። በዚህ ጊዜ የመርዶኪዮስን ታላቅ ሥራ አስታወሰ (**አስቴር 6፡1–3** ይመልከቱ)። መርዶኪዮስ እንደገና ሐማ ሊገድለው እየፈለገ ነው!

— በዚህ ጊዜ ንጉሡ መርዶኪዮስ እንዴት ማክበር እንዳለበት ሲያስብ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላት የሆነው ሐማ ወደ ንጉሡ ቤት ውጪው አዳራሽ ገባ። ንጉሡም ሐማን "ነጉሥ ሊያከብረው የወደደው ሰው" እንዴት ማክበር እንዳለበት ጠየቀው (**አስቴር 6፡6** ይመልከቱ)። ሐማ ንጉሥ ሊያከብረው የሚወደው ከኔ በቀር ማን አለ ብሎ ስለራሱ አሰበ! ንጉሡ ግን እየተናገረ የነበረው ስለ መርዶኪዮስ ነበር። በመጨረሻም ሐማ መርዶኪዮስን ለማክበር ተገደደ። ይህም ሂደት የመርዶኪዮስን ሕይወት አዳነ (**አስቴር 6፡ 10–11** ይመልከቱ)።

በእነዚህ "አጋጣሚዎች" መካከል በአንዱም የእግዚአብሔር ስም አልተጠቀሰም። ይሁን እንጂ ሁሉም እንዲፈጸሙ ያደረገው እግዚአብሔር ራሱ እንደሆነ ግልጽ ነው! ይህን ታሪክ የሚያነቡ ሰዎች እግዚአብሔር ከመጋረጃ ጀርባ ሲሠራ ማየት ይችላሉ።

በዚህ ዘመንም በምድር ላይ ያሉት ሁሉም የእግዚአብሔር ሕዝቦች ከአስቴር ጋር ተመሳሳይ ናቸው። ሁላችንንም የምንኖረው "በባዕድ አገር" ገዢዎችና መንግሥታት ሥር ነው። የምንኖረውም ሌሎች "አማልክት" በሚመለኩባቸው ቦታ ነው። አንዳንድ ጊዜም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማጥፋት እንደ ሐማን ያሉ ሰዎች አሉ። የእግዚአብሔር ሕዝብ ትልቅ አደጋ ላይ ነው! በዚህ ዓይነት ቤተ ክርስቲያን እንዴት ትተርፋለች? ነገር ግን እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመታደግ "ከበስተጀርባ" ስለሚሠራ የእግዚአብሔር ሕዝብ በሕይወት ይኖራል። የእግዚአብሔር ሰዎች መሥራትና በሕይወት መትረፍ መቻላቸውን የሚያረጋግጡ ተአምራት በየቀኑ እየተፈጸመ ነው።

ይህ የእግዚአብሔር ሕዝብ ፈጽሞ መከራ ላለመቀበሉ ዋስትና አይሆንም። ይሁን እንጂ መከራ ሲደርስባቸውና ሲሰቃዩ እግዚአብሔር ይህን መከራ እንዲደርስባቸው እንደፈቀደ ያውቃሉ። መጽሐፈ አስቴር ኃይለኛ ጠላቶች ሊያጠፏቸው በሚፈልጉበት ጊዜም እንኳ እግዚአብሔር ሕዝቡን ማዳን እንደሚችል ያሳያል።

በግልጽ ለማየት እንደሚቻለው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ዋናው ጭብጥ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለማዳን እንደሚችልና ይህን ለማድረግ አሁንም ቢሆን ከበስተጀርባ በንቃት እየሠራ መሆኑን ነው።

በአስቴር መጽሐፍ ውስጥ በርካታ "ጥላ ወይም አምሳል" እንዳሉ መገንዘብ ለአንባቢ ጠቀሜታ አለው።

**መርዶኪዮስ የክርስቶስ "ምሳሌ" ነው።** ስለ መርዶኪዮስ እና ተግባሮቹ ስናነብ ክርስቶስን የበለጠ እናውቀዋለን፤ ምክንያቱም ለእግዚአብሔር ሕዝብ ያለው ሕይወት እና አገልግሎት የክርስቶስ ሕይወት እና አገልግሎት ትንሽ ስዕል ነውና። መጽሐፈ አስቴር ተብሎ ሲጠራ የጸሐፊው ቃላት መርዶኪዮስ በአስቴር

መጽሐፍ ውስጥ በጣም አስፈላጊ ገጸ ባሕሪይ መሆኑን ያመለክታል። ይህም ግልጽ ነው፤ ምክንያቱም ደራሲው በመጽሐፉ መጀመሪያ ላይ በመርዶኪዮስ ላይ ያተኮረ ነው። እንደዚሁም በመጽሐፉ መጨረሻም በመርዶኪዮስ ላይ ያተኩራል። መርዶኪዮስ እንደ ክርስቶስም ፈጽሞ ለክፋት ታልፎ አልተሰጥም። ልክ ክርስቶስ ለሰይጣን ለመስገድ ፈቃደኛ እንዳልነበረ ሁሉ መርዶኪዮስም በሐማ ሲፈተን ለመስገድ ፈቃደኛ አልነበረም። መርዶኪዮስ የእግዚአብሔር ሕዝብ ከጥፋት አድኗል። ከተዋረደበት ተነስቶ በመንግሥቱ ውስጥ “በማዕረግ ሁለተኛ” ለመሆን በቃ። ክርስቶስ እንደ መርዶኪዮስም በሌላ ንጉሥ (በእግዚአብሔር አብ) ሥር ነው! የክርስቶስ ጥላ የሆነው ዮሴፍም ደግሞ በማዕረግ ሁለተኛ ነበር (**ዘፍጥረት 41፡37–45** ይመልከቱ!) ክርስቶስ እንደ መርዶኪዮስ (እና ዮሴፍም) ሁልጊዜ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ጥቅም እየሰራ ነው። ክርስቶስ እንደ መርዶኪዮስም በሀሰት በሕዝብ ላይ ራሱን ከፍ አላደረገም። ይልቁንም ሕዝቡን እንደ “ወንድሞቹ” አድርጎ ይመለከታቸዋል ( **ዕብራውያን 2፡11–18** ይመልከቱ)።

*አይሁዳዊውም መርዶኪዮስ ለንጉሡ ለአርጤክሲስ በማዕረግ ሁለተኛ ነበረ፤*

*በአይሁድም ዘንድ የከበረ በብዙ ወንድሞችም ዘንድ የተወደደ*


*መልካም የፈለገ ለዘሩም ሁሉ በደህና የተናገረ ነበረ።* **አስቴር 10፡3**

መርዶኪዮስ በተግባሩ ሁሉ ጻድቅ ሆኖ መቅረቡ ልብ ማለት ያስፈልጋል። በሐማን እጅ በግፍ እየተሰቃየ ነበር። ይህም የክርስቶስ መከራ ምሳሌ ነው። እርግጥ ነው በመረዶኪዮስና በኢየሱስ መካከል ያለው ትልቅ ልዩነት ኢየሱስ ለሕዝቡ መሞቱን ነው!

**ሐማ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች ሁሉ “ጥላ” ነው።** መጽሐፈ አስቴር ብዙ የወንጌል ጠላቶች እንዳሉ ክርስቲያኖችን ያስታውሳል። የሐማ መጥፋት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ትልቅ ማበረታቻ ሊያመጣላቸው ይገባል። ሁሉንም የእግዚአብሔር ጠላቶች በመጨረሻ ይደመሰሳሉና።

**አስቴር ደግሞ የሁሉም ክርስቲያኖች “ጥላ ወይም ምሳሌ” ናት።** ስለዚህ እንደ አስቴር ሕይወታችን የራሳችን እንዳልሆነ መረዳት አለብን። እግዚአብሔር መሆን ባለብን ሥፍራ አስቀምጦ ያኖረናል። እንደ አስቴርም ለእግዚአብሔር ዓላማዎች እና ለእግዚአብሔር ሰዎች ሕይወታችንን አደጋ ላይ መጣል አለብን (**አስቴር 4፡12–16** ይመልከቱ)። ይህ አደጋ ሕይወታችንን እስከማሳጣት ሊደርስ ይችላል።

በመጨረሻውም  መጽሐፈ አስቴር ያለፈውን፣ አሁን ስለአለው ሁኔታና ስለወደፊቱ ላይ ትኩረትን ይስባል። አስቴር እግዚአብሔር ለሕዝቡ ባድረገው ባለፈው ነገር የእግዚአብሔር ሰዎች እንዲደሰቱ ያደርጋል። አሁን ባለንበት ሁኔታ ሆነን ደግሞ የእግዚአብሔርን እርዳታ ስንፈልግ ይህ መጽሐፍ በሚያስፈልገን ነገር እምነታችንን ይገነባል። እንደዚሁም ከፊታችን ላለው ሙሉ በሙሉ እግዚአብሔር ሊታደገን እንደሚችል ተስፋን ይሰጣል።



## 23. ዕዝራ ነህምያ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደማይተው ወይም የመረጠውን ሥፍራ እንደማይረሳ ያስረዳል

በዘመናዊ መጽፍሐ ቅዱስ ውስጥ ዕዝራ እና ነህምያ ሁለት የተለያዩ መጽሐፍት ናቸው። አጠገብ ለአጠገብ ተደርድረዋል። በዘመናዊ መጽሐፍ ቅዱሶች ውስጥ ዕዝራ እና ነህምያ ከ 1 እና 2 ዜና መዋዕል በኋላ እና ከመጻሐፈ አስቴር በፊት ይገኛሉ። በጥንታዊው የዕብራይስጥ የጽሑፎች አደረጃጀት ግን ዕዝራ ነህምያ እንደ አንድ መጽሐፍ ነው። እነሱ የሚገኙት ከመጽሐፍ አስቴር በኋላ እና ከመጽሐፈ ዜና መዋዕል በፊት ነው።

ዕዝራ ነህምያ የኢየሩሳሌም መልሶ መገንባትና ቤተ መቅደሱን እንደገና በመገንባቱ ሂደት ላይ ያተኮረ ነው። እነዚህ መጻሕፍት የኢየሩሳሌምን መልሶ መገንባትና ቤተ መቅደሱንና ኢየሩሳሌምን በመገንባት ሥራ ሲመሩ በዕዝራ፣ ነህምያ እና በሌሎችም መሪዎች ላይ በፈሰሰው የእግዚአብሔር ጸጋ ላይ ያተኩራሉ። እነዚህ መጻሕፍት የሚያተኩሩት በአይሁድ ሕዝብ ላይ ኢየሩሳሌምና ቤተ መቅደሱን ለመገንባት ሲታገሉ በፈሰሰው የእግዚብሔር ጸጋ ላይ ነው። ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋ በመሪዎች እና በሕዝቡ ላይ የፈሰሰ ቢሆንም ይህ አሁንም በጣም አስቸጋሪ ጊዜ ነበር።

እነዚህ መጻሕፍት ደግሞ የሚያተኩሩት የእግዚአብሔር ሰዎች ቤተ መቅደሱንና ኢየሩሳሌምን እንደገና ለመገንባት ሲታገሉ ባጋጠማቸው ችግሮች እና መከራዎች ላይ ነው። እንደዚሁም እነዚህ መጻሕፍት በሰዎች ኃጢአተኝነት ላይ ያተኩራሉ። ሕዝቡ በዕዝራ ነህምያ ባኣልን እያመለኩ ባይሆኑም አሁንም ግን የእግዚአብሔር ሕጎች ለመታዘዝ እየተንገዳገዱ እንደነበር ግልጽ ነው። እነዚህ መጻሕፍት ለእግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ የሚታዘዙ ወይም የተሰጡ ሰዎችን ለመፍጠር ትልቅ ሥራ እንደሚያስፈልግ ያሳያሉ። ያ በእግዚአብሔር ሕዝብ ልብ ውስጥ ያለው ጥልቅ ሥራ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተገልጿል (**ሕዝቅኤል 36፡24–27 ይመልከቱ**)። ይህ "በእግዚአብሔር ሕዝብ ልብ ውስጥ ያለው ጥልቅ ሥራ" ማከናወን የተቻለው በጌታ በኢየሱስ ሕይወት፣ ሞት፣ ትንሣኤ እና ዕርገት ነው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ለእግዚአብሔር መታዘዝ ቀላልና የሚቻል እንዲሆን ያደርገዋል (**ዮሐንስ 14፡15–17** ይመልከቱ)።

በዕዝራ ነህምያ ዘመን እንደገና የተሠራው ቤተ መቅደስ ሁለተኛው ቤተ መቅደስ ተብሎ ተጠርቷል። የመጀመሪያው ቤተ መቅደስ በባቢሎናውያን ፈርሷል። ሊቃውንት አንዳንድ ጊዜ ይህ ሁለተኛው ቤተ መቅደስ እንደ **ሁለተኛው የቤተ መቅደስ** ጊዜ አድርገው የሚውሰዱት ከተሠራበት ጊዜ አንስቶ ነው።

ሁለተኛው የቤተመቅደስ ጊዜ የሚባለው ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ 516 እስከ 70 ዓ/ም ያለውን ጊዜ ነው። ይህ ሁለተኛው ቤተ መቅደስ በ70 ዓ/ም በሮማውያን ፍርሷል።

ክርስቲያኖች “ሦስተኛው የቤተመቅደስ ዘመን” እና ከዚያ በኋላ “አራተኛው የቤተመቅደስ ጊዜ” ይኖሩ እንደሆነ ማሰብ አያስፈልጋቸውም። “ሦስተኛው የቤተመቅደስ ጊዜ” አይኖርም ምክንያቱም እውነተኛው ቤተ መቅደስ ኢየሱስ የማዕዘን ድንጋይ የሆነበት ቤተ መቅደስ ተገንብቷል እናም አሁን እየተገነባ ነው። ሁሉም የቀደሙት “መቅደሶች” ማለትም (የማደሪያው ድንኳን፣ የመጀመሪያው ቤተ መቅደስ (በሰሎሞን የተገነባው) እና ሁለተኛው ቤተ መቅደስ) የዚህ እውነተኛ ቤተ መቅደስ ጥላዎች ነበሩ። ይህ እውነተኛው ቤተ መቅደስ “በሐዋሪያትና በነቢያት መሠረት ላይ የታነጸ ነው፤ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው” (**ኤፌሶን 2፡20–21**)። ይህ ቤተ መቅደስ—እውነተኛው ቤተመቅደስ—አሁን ሰዎች ለማምለክ እና ተስፋን፣ ፈውስን፣ ይቅርታን፣ ማሕበረሰብ እና እረፈትን ለማግኘት የሚመጡበት ቦታ ነው።

የሁለተኛው ቤተ መቅደስ ግንባታ በዕዝራ ውስጥ እንደ ሚከተለው ተገልጿል፡-

*አናጢዎቹም የእግዚአብሔርን መቅደስ በመሠረቱ ጊዜ ካህናት ልብሳቸውን ለብሰው መለከቱን ይዘው የአሳፍም ልጆች ሌዋውያን ጸናጽል ይዘው እንደ እሥራኤል ንጉሥ እንደ ዳዊት ሥራዓት እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ዘንድ ቆሙ።*

*ደግሞም፡— ቸር ነውና*

*ለእሥራኤልም ምሕረቱ ለዘላለም ነውና*

*እያሉ እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ እያከበሩ እርስ በርሳቸው ያስተዛዝላሉ ነበር፤ የእግዚአብሔርም ቤተ ስለተመሠረተ ሕዝቡ ሁሉ እግዚአብሔርን እያምሰገኑ በታላቅ ድምፅ እልል አሉ። የፊተኛውንም ቤት ያዩ ሽማግሌዎች የሆኑ ብዙ ካህናትና ሌዋውያን የአባቶችም ቤቶች አለቆች ግን ይህ መቅደስ በፊታቸው በተመሠረተ ጊዜ በታላቅ ድምፅ ያለቅሱ ነበር፤ ብዙ ሰዎችም በደስታ ይጮሁ ነበር፤ ደስ ብሎአቸውም የሚጮኹትን ድምፅ ከሕዝቡ ልቅሶ ድምፅ መለየት የሚችል አልነበረም፤ ሕዝቡም በታላቅ ድምፅ ይጮኽ ነበር ድምፁም ከሩቅ ይሰማ ነበር።* **ዕዝራ 3፡10–13**

ብዙ ሰዎች በዚህ ቤተመቅደስ ግንባታ ሲደሰቱ አንዳንድ ሰዎች ይህን ቤተመቅደስ ሲያዩ ማልቀሳቸው ጠቃሚ ነበር። ሰሎሞን የሠራው የመጀመሪያውን ቤተ መቅደስ ያዩት ሰዎች አለቀሱ፤ ምክንያቱም "የሁለተኛው" ቤተ መቅደስ እንደ መጀመሪያው ቤተመቅድስ ክብር አልነበረውም።

የዚህ ቤተመቅደስ ክብር አነስተኛ በመሆኑ አንዳንድ ሰዎች ያለቀሱ መሆናቸው ጉልህ ነው። ደግሞም የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ከክብር የጎደለ መሆን የለበትም። የዚህ ሁለተኛው ቤተመቅደስ አናሳ ክብር ተፈጥሮ ጊዜያዊ መሆኑን ያጎላል። ስለዚህ የዚህ የሁለተኛው ቤተመቅደስ አናሳ ክብር ተፈጥሮ አንባቢዎችን ለሌላ እጅግ የላቀ ክብር ያለው ቤተመቅደስ እንዲጠብቁ ያዘጋጃቸዋል።

ይህ ሁለተኛው ቤተመቅደስ በእርግጥም በሌላ ቤተመቅደስ ተተካ። ያም ቤተመቅደስ ክርስቶስና ቤተክረስቲያን ናቸው (**ዮሐንስ 2፡18–22** ይመልከቱ)። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ነፍሱን በሰጠ ጊዜ በዛው ቅጽበት የሁለተኛው ቤተመቅደስ መጋረጃ ከላይ ወደታች ለሁለት ተቀደደ (**ሉቃስ 23፡44–46** ይመልከቱ)። መጋረጃው ለሁለት መቀደዱ የሁለተኛው የቤተመቅደስ ጊዜ ማብቃቱን ያሳያል (**ዮሐንስ 4፡ 19–26** ይመልከቱ)። ይህ ከአሁን በኋላ ሰዎች ይቅርታን፣ ፈውስንና፣ ተስፋን የሚያገኙበት "ሥፍራ" አልነበረም። ይህ ሁለተኛው ቤተመቅደስ በአዲሱ ፍጹም በሆነው እና የመጨረሻው ቤተመቅደስ ተተካ (**ኤፌሶን 2፡19–22** እና **ራዕይ 3፡12** ይመልከቱ)።


ዕዝራ ነህምያ ትኩረት የሚያደርገው ኢየሩሳሌምን መልሶ በመገንባት ላይ ነው። ይህ ልክ እንደ ቤተመቅደሱም መልሶ ግንባታ እንደ "የመጀመሪያዋ" ኢየሩሳሌም የከበረ አልነበረም። ዕዝራ ነህምያ ኢየሩሳሌም እጅግ ውድ እንደሆነች ያሳያል። ይሁን እንጂ በዚህ ዘመን ያሉ አማኞች ተስፋቸው ምድራዊ ከተማ ላይ አይደለም። ይልቅስ የአማኞች ተስፋ በሁሉም ዘመናት እንደነበሩቱ ቅዱሳን የማይፈርስና ጠንካራ መሠረት ያላትን ከተማ እየጠበቁ ነው። ይህችም ከተማ "አዲሲቷ ኢየሩሳሌም" ተብላ ትጠራለች። ይህ በመጽሐፍ ቅድሱ ውስጥ ዋናው ጭብጥ ነው ( **መዝሙር 137፡6፤ ገላትያ 4፡26፤ ዕብራውያን 11፡9–16፣ 12፡22–24 እና ራዕይ 21፡1–2፡5** ይመልከቱ)።

በዕዝራ ነህምያ ላይ ትኩረት የተደረገባቸው ሦስቱም ነገሮች (ቤተ መቅደሱ፣ ከተማው እና ሕዝቡ) ሲሆኑ፤ እንደዚሁም በራዕይ ውስጥ ተገልጸዋል። በራዕይ ውስጥ ግን ቤተመቅደሱ የከበረ ነው፤ ከተማዋም አስተማማኝና ድንቅ ናት፤ እናም ሰዎች ፍጹም ደስተኛ እና ታዛዥ ናቸው። ዕዝራ ነህምያ አንባቢዎችን ለዚህ ክቡር ጊዜ ያዘጋጀናል።

*ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክና በጉ መቅደስዋ ናቸውና መቅደስ በእርስዋ ዘንድ አላየሁም። ለከተማይቱም የእግዚአብሔር ክብር ስለሚያበራላት መብራትዋም በጉ ስለሆነ፤ ፀሐይ ወይም ጨረቃ እንዲያበሩላት አያስፈልጋትም ነበር። አህዝብም በብርሃንዋ ይመላለሳሉ፤ የምድርምነገሥታት*

*ክብራቸውን ወደ እርስዋ ያመጣሉ፤ በዚያም ሌሊት ስለሌለ ደጆችዋ በቀን ከቶ አይዘጉም፤ የአሕዛብም ግርማና ክብር ወደ እርስዋ ያመጣሉ። ለበጉም በሆነው በሕይወት መጽሐፍ ከተጻፉት በቀር ጸያፍ ነገር ሁሉ ርኵሰትም ውሸትም የሚያደርግ ወደ እርስዋ ከቶ አይገባም።*

በአደባባይዋም መካከል ከእግዚአብሔርና ከበጉ ዙፋን የሚወጣውን እንደ ብርሌ የሚያንጸባርቀውን *የሕይወትን ውኃ ወንዝ አሳየኝ። በወንዙም ወዲያና ወዲህ በየወሩ እያፈራ አሥራ ሁለት ፍሬ የሚሰጥ የሕይወት ዛፍ ነበረ፤ የዛፉም ቅጠሎች ለሕዝብ መፈወሻ ነበሩ፤ ከእንግዲህም ወዲህ መርገም ከቶ አይሆንም። የእግዚአብሔርና የበጉ ዙፋን በእርስዋ ውስጥ ይሆናል፤ ባሪያዎቹም ያመልኩታል፥ፊቱንም ያያሉ፤ ስሙም በግንባሮቻቸው ይሆናል። ከእንግዲህ ወዲህ ሌሊት አይሆንም፤ ጌታ አምላክም በእነርሱ ላይ ያበራላቸዋልና የመብራት ብርሃንና የፀሐይ ብርሃን አያስፈልጋቸውም፤ ለዘላለም እስከ ዘላለም ይነግሣሉ።* **ራእይ 21፡22–22:5**



## 24. ዜና መዋዕል የሚያተኩረው የዳዊት ዘር በሆነው ንጉሥ እውነተኛውን ቤተ መቅድስ በመገንባቱ ላይ ነው።

በዘመናዊው መጽሐፈ ቅዱስ 1ኛ እና 2ኛ ዜና መዋዕል ሁለት መጻሕፍት ናቸው። በጥንታዊ የዕብራይስጥ መጻሐፎች ግን 1ኛ እና 2ኛ ዜና መዋዕል አንድ መጻሐፍ ነው።

ዜና መዋዕል በአቀማመጥ ከ1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል እንደዚሁም ከ1ኛ እና 2ኛ ነገሥት ጋር ተመሳሳይ ሊመስል ይችላል። ይህ መመሳሰል በዘመናዊው መጽሐፍ ቅዱሶች ውስጥ ከሳሙኤልና ከነገሥታት በኋላ በመቀመጡ ምክንያት የበለጠ ትኩረት ተሰጥቶታል። ይሁን እንጂ ዜና መዋዕል ከሳሙኤልና ከነገሥታት በጣም የተለየ ነው።

ለምሳሌ የዜና መዋዕል ጸሐፊ የሚለው (የዜና መዋዕል ጸሐፊን ለማመልከት ሊቃውንት የተጠቀሙበት ስም ነው) መጽሐፉ የሚጀምረው ከአዳም ጀምሮ ባለው የዘር ሐረግ ላይ ነው። ይህ የሚያሳየው በዜና መዋዕል ውስጥ የሚነገረው ታሪክ ከምድር መጀመሪያ ጀምሮ ያለውን የእግዚአብሔርን እቅድ ለማካተት የታሰበ ነው።

በዜና መዋዕል ውስጥ ጸሐፊው የሚናገረው ታሪክ የተመረጠውን ነው። ለምሳሌ በ 1ኛ ዜና ውስጥ የመጀመሪያውን ቁጥር ይመልከቱ።

*አዳም፣ ሴት፣ ሄኖስ . . .* **1ኛ ዜና 1፡1**

ይህ ሙሉ የዘር ሐረግ እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ምክንያቱም አቤልን ዘሎታል። የቃየልንም የዘር ሐረግ አላካተተም። ይህ በጣም ጠቃሚ ነው። እንግዲህ ዜና መዋዕል የሚያተኩረው ከሴት ትውልድ የመጡት ሰዎች የዘር ሐረግ ላይ ነው።

ከዚህ ባሻገር ዜና መዋዕል ጸሐፊው ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር ያደረገውን ኃጢአት አያመልክትም። ይልቁንም ሰሎሞን በኢየሩሳሌም ከዳዊት ከተወለዱት ልጆች መካከል እንደ አንዱ ልጁ በመቁጠር ይናገራል (**1 ዜና 14፡4** ይመልከቱ)። ሰሎሞን ከመወለዱ በፊት የነበሩትን ኃጢአተኛ ሁኔታዎች አይገልጽም። እንደ ዜና መዋዕል ያለ ጠንቃቃ የታሪክ ምሁር የዳዊትን ኃጢአት ያልጠቀሰው ለምንድር ነው? ከዚህ ውጪ ዜና መዋዕል የሰሎሞንን ኃጢአት አያመለከትም። ይልቁንም የዜና መዋዕል ጸሐፊ ራሱ ሰሎሞን በእግዚአብሔር ላይ ታላቅ ኃጢአት እንደሠራ አንባቢ እንዲያውቅ ይጽፋል።

ደራሲው ግን ለምን እንዲህ ያደርጋል? ወይስ ደራሲው እውነተኛ አይደለም? ደራሲው ሀሰተኛ ሊሆን አይችልም። ይልቁንም ታሪኩን የሚናገርበት መንገድ ከፍተኛ ጥንቃቄ እያደረገ ነው። የዜና መዋዕል ጸሐፊ ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር ያደርገውን ኃጢአት "ቸል ማለት" ይችላል፤ ምክንያቱም ዓላማው የዳዊትን ታሪክ ሙሉ በሙሉ መዘርዘር ስላልሆነ ነው። ከዚህ ውጪ ዳዊት ደግሞ ስለኃጢአቱ እንደ ተጸጸተ ግልጽ ነው። ይህ ደግሞ በዜና መዋዕል ውስጥ መድገም አያስፈልግም ነበር ይሆናል፤ የመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢ ስለዚህ የዳዊት ኃጢአት በሳሙኤል ውስጥ ስለተነገርው ሁሉንም ያውቃል፤ ምክንያቱም የሳሙኤል መጽሐፍ የተጻፈው ከዜና መዋዕል በፊት ነውና።

ይሁን እንጂ ዜና መዋዕል ከዳዊት ኃጢአት አንዱን በእጅጉ እንድሚያጎላ ለማስተዋል በጣም አስፈላጊ ነው (**1 ዜና መዋዕል 21** ይመልከቱ)። የዜና መዋዕል ጸሐፊ ትኩረት ያደርገው ዳዊት ባደርገው የሕዝብ ቆጠራ ላይ ነው። ደራሲው በዚህ ልዩ ኃጢአት ላይ ያተኮረውና የዳዊት ኦርዮንን መግደሉና ከቤርሳቤህ ጋር ያደርገው ምንዝርና ለምን ችላ አለው? ይህ የሚያደርገው ምክንያቱም የዚህ የተለየ ኃጢአት ቅጣት የወደፊቱ ቤተመቅደስ በሚገነባበት ቦታ ላይ ስለቆመ ይመስላል!

*ዳዊትም ይህ የእግዚአብሔር ቤት ነው፤ ይህም ለእሥራኤል ለሚቃጠል መሥዋዕት የሚሆነው መሠዊያ ነው አለ።* **1 ዜና 22፥1**

በዜና መዋዕል ጸሐፊው በዚህ ልዩ ኃጢአት ላይ ማተኮሩ እንደገና በዳዊት ዘር ስለ ቤተ መቅደሱ ግንባታ መጽሐፍ እየጻፈ መሆኑን ያሳያል።

የዜና መዋዕል ጸሐፊ የሰሎሞንን ኃጢአት "ቸል" ብሏል። ምናልባት ይህን የሚያደርገው የሰሎሞንን ሙሉ ታሪክ እየሰጠ ባለመሆኑ ነው። ይልቅስ ደራሲው ትኩረት ያደርገው ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን እንደ ሚገነባ በማተኮር ላይ ነው። ከዚህ ውጪ ሰሎሞን ከኃጢአቱ ስለመጸጸቱ ብዙ ማስረጃዎች አሉ። መጽሐፈ ምሳሌ፣ መጽሐፈ መክብብ እና መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን ሁሉም ሰሎሞን በሕይወቱ መገባደጃ ላይ ከኃጢአቱ ንስሐ የገባ ሰው እንደ ነበር ማስረጃ ሆነው ያገለግላሉ። ስለዚህ የዜና መዋዕል ደራሲ የሰሎሞንን ብዙ ኃጢአቶች እንደገና ማስታውስ አያስፈልገውም ነበር።

ዜና መዋዕል በተለይም ትኩረት ያደረገው የቤተ መቅደሱን ታሪክ በመናገር ላይ ነው። ከ **1ኛ ዜና 22** እስከ **2ኛ ዜና 7** ድረስ ትኩረት የተደረገው በቤተ መቅደሱ ዝግጅት እና ግንባታ ላይ ነው።

ከሰሎሞን በኋላ የተዘረዘሩት ነገሥታት ሁሉም ከይሁዳ የሆኑ መሆናቸውን ልብ ማለት ያስፈልጋል። ይህ ከ 2ኛ ነገሥት በጣም የተለየ ያደርገዋል። የዜና መዋዕል ጸሐፊ በሰሜናዊው የእሥራኤል መንግሥት ይገዙ  ስለ ነበሩት ነገሥታት አይናገርም። ስለዚህ ይህ የሚያሳየው የዜና መዋዕል ጸሐፊው

የዳዊትን የንጉሥነት ታሪክ እና በዳዊት ዘር የተሠራውን ቤተ መቅደስ ታሪክ እየተረከ ነው ማለት ነው። የእነዚህ ሁለት ነገሮች ታሪክ የተያያዙ ናቸው በመሆኑም የዜና መዋዕል ደራሲ አንባቢዎቹ አንድ ላይ እንዲመለከቱዋቸው ይፈልጋል።

ዜና መዋዕል በ **1 ዜና 17፡1–15** ላይ ለዳዊት በተገባው የተስፋ ቃል ምክንያት ከዳዊት ዘር በሆነው ንጉሥ እና በዳዊት ዘር በተሠራው ቤተ መቅደስ ላይ ያተኩራል (በተጨማሪም **2 ሳሙኤል 7፡1–17** ይመልከቱ)።

ዜና መዋዕል ስለሌሎች የይሁዳ ነገሥታት እንደገለጸው በተለይም ነገሥታቱ ከቤተመቅደሱ ጋር የተገኛኙት ወይም ቤተ መቅደሱን መልሰው ያቋቋሙት ወይም በቤተ መቅደሱ የነበረውን አምልኮ መልሰው ያስጀመሩት እንዴት እንደሆነ ላይ ያተኩራል።


መጽሐፉ የሚያበቃው የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ አንድ ሰው ሄዶ ቤተ መቅደሱን እንዲሠራ ባስተላለፈው አዋጅ ላይ ነው።


> *በኤርምያስ አፍ የተነገረው የእግዚአብሔር ቃል ይፈጸም ዘንድ በፋርስ ንጉሥ በቂሮስ በመጀምሪያው ዓመት እግዚአብሔር የፋርስን ንጉሥ የቂሮስን መንፈስ አስነሣ፤ እርሱም የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ እንዲህ ይላል። የሰማይ አምላክ እግዚአብሔር የምድርን መንግሥታት ሁሉ ሰጥቶኛል፤ በይሁዳም ባለችው በኢየሩሳሌም ቤት እሠራለት ዘንድ አዝዞኛል፤ ከሕዝቡም ሁሉ በእናንተ ዘንድ ማንም ቢሆን አምላኩ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ይሁን እርሱም ይውጣ ብሎ በመንግሥቱ ሁሉ አዋጅ አስነገረ ደግሞም በጽሕፈት አደረገው።* **2 ዜና 36፡22–23**

የዜና መዋዕል መጨረሻ መልሶ የዜና መዋዕል ዋና አሳሳቢ ጉዳይ በድጋሚ ማንሳት ነው። ይህም ዳግም በቤተ መቅደሱ ላይ ማተኮሩን ነው። የዳዊት የዘር ሐረግ ከቤተ መቅደሱ ግንባታ ጋር የተያያዘ መሆኑን ያውቃል፤ ስለዚህ ይህን “ቤት” ለእግዚአብሔር የሚሠራው ሰው በዳዊት የዘር ሐረግ አዲስ ንጉሥ እንደሚሆን ሳይገባው አለቀረም። ድራሲው ትክክል ነው። ኢየሱስ ያ ሰው ነውና!

ከአዳም ጀምሮ የዜና መዋዕል ጸሐፊ ይህ ቤተ መቅደስ ለሰዎች ሁሉ እንደሆነ አሳይቷል። የዜና መዋዕል ጸሐፊ በአዳም ልጅ በሴት ላይ በማተኮር በ**ዘፍጥረት 3፡15** ላይ ስለ “ዘሮች” የተሰጠውን ተስፋ እንደሚያውቅ አሳይቷል።

ዜና መዋዕል ጠንቃቃ የታሪክ ምሁር ነው። ሆኖም ደራሲው የጀመረውን ታሪክ ማጠናቀቅ አይችልም። ምክንያቱም የዘላለም ቤተ መቅደስ እና ይህንን ቤተ መቀደስ የሚገነባው የዳዊት ዘር ታሪክ በዜና መዋዕል ውስጥ የተሟላ አይደለም ደግሞም የእግዚአብሔር ሥራ በብሉይ ኪዳን ጊዜ አልተጠናቀቀም ነበርና።





## 25. ዜና መዋዕል ለኢየሱስና በአዲስ ኪዳን ለሚነገረው ታሪክ እንደ ድልድይ ነው

በዘመናዊ የእንግዝሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱሶች ትንቢተ ሚልክያስ በብሉይ ኪዳን የመጨረሻው መጽሐፍ ነው። ይህም አግባብነት ያለው ነገር ነው፤ ምክንያቱም ሚልክያስ የብሉይ ኪዳን ነቢያት የመጨረሻው ነቢይ ነውና። የሚልክያስ መጽሐፍ አንባቢዎችን ለዲስ ነቢይ ያዘጋጃል። ሚልክያስ ይህን ነቢይ "ነቢዩ ኤልያስ" ሲል ገልጾታል።

> *እነሆ ታላቁን የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ሳይመጣ ነቢዩን ኤልያስን እልክላችኋለሁ። መጥቼም ምድርን በእርግማን እንዳልመታ እርሱ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች፥ የልጆችንም ልብ ወደ አባቶች ይመልሳል።* **ሚልክያስ 4፡5–6**

ኢየሱስ እዳለው መጥመቁ ዮሐንስ በዚህ ጥቅስ በትንቢት የተነገረለት "ኤልያስ" ነው (**ማቴዎስ 11፡13–14** ይመልከቱ)። ስለዚህ ሚልክያስ ስለ "ኤልያስ" የተናገረው በብሉይ ኪዳን እና በኢየሱስ መካከል ያለ "ድልድይ" ነው።

ይሁን እንጂ በዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ የመጨረሻው መጽሐፍ ትንቢተ ሚልክያስ አይደለም። በዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻው መጽሐፍ ዜና መዋዕል ነው። ይህ መጽሐፍ በተፈጥሮ አንባቢን ወደ አዲስ ኪዳን ይመራል። የዜና መዋዕል ትረካ ስላላለቀ አንባቢን ወደ አዲስ ኪዳን ይመራል። የሚጨርሰውም የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ ባወጣው አዋጅ ነው። ሆኖም ለአንባቢው ይህ አዋጅ የሚፈጽመው ማን እንደሆነ ቢያንስ በዜና መዋዕል ውስጥ አልተነገረም።

> *በኤርምያስ አፍ የተነገረው የእግዚአብሔር ቃል ይፈጸም ዘንድ በፋርስ ንጉሥ በቂሮስ በመጀምሪያው ዓመት እግዚአብሔር የፋርስን ንጉሥ የቂሮስን መንፈስ አስነሣ፤ እርሱም የፋርስ ንጉሥ ቂሮስ እንዲህ ይላል። የሰማይ አምላክ እግዚአብሔር የምድርን መንግሥታት ሁሉ ሰጥቶኛል፤ በይሁዳም ባለችው በኢየሩሳሌም ቤት እሠራለት ዘንድ አዝዞኛል፤ ከሕዝቡም ሁሉ በእናንተ ዘንድ ማንም ቢሆን አምላኩ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ይሁን እርሱም ይውጣ ብሎ በመንግሥቱ ሁሉ አዋጅ አስነገረ ደግሞም በጽሕፈት አደረገው።* **2 ዜና 36፡22–23**

ይህን ማድረግ የሚችል ልዩ ሰው ማነው? ይህ ጥያቄ በዜና መዋዕል ውስጥ መልስ አላገኘም። ቂሮስ እግዚአብሔር ቤቱን ለመሥራት ከሚወጣው "ጋር" እንደሚሆን ተናግሯል። በቀረውስ በዜና

መዋዕል በመመርኮዝ ይህ ሰው ከዳዊት ዘር የሆነ ንጉሥ እንደሚሆን ግልጽ ነው፡፡ ግን ምን ዓይነት ንጉሥ ይሆናል? ስሙስ ማን ይባላል?፡፡

ይህ ያልተመለሰ ጥያቄ ሊሆን ይችላል፡፡ ደግሞም እንግዳ ይመስላል፤ ምክንያቱም መጻሕፍትን በቅደም ተከተል ለሚያነቡ ሰዎች በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ እንደተሰራ ያውቃሉ፡፡ የቤተ መቅደሱም ግንባታ ከዕዝራ ነህምያ ዋና ዋና ጉዳዮች አንዱ ነበርና፡፡ ነገር ግን ጉዳዩ ይህ ከሆነ ስለ ቤተ መቅደስ ግንባታ ባልተመለሰ ጥያቄ ብሉይ ኪዳን ለምን ያበቃል?

ብሉይ ኪዳን በዚህ መንገድ ያበቃል ምክንያቱም ዜና መዋዕል በዕዝራ ነህምያ ስለተሠራው ትንሽዬ ቤተ መቅደስ ግንባታ አይናገርም፡፡ ይልቁንም ይህ የእውነተኛውን እና የመጨረሻውን ቤተመቅደስ ግንባታ የሚመለከት ነው፡፡ ያን ቤት መሥራት የቻለው ማን ነው? የዚህ ጥያቄ መልስ በብሉይ ኪዳን ውስጥ አይገኝም፡፡ የቤተ መቅደሱንም ሰሪ ስም ማን እንደሆነ አይታወቅም፡፡ ነገር ግን ከዳዊት ዘር እንደሚሆን እናውቃለን ይሁን እንጂ እሱ ማን ነው? ( **1 ጴጥሮስ 1፡10–12** እንደሚናገረው ነቢያትም ቢሆኑ ይህንኑ ይጠይቁ ነበር፤ ጥያቄ!)

የዚህ ጥያቄ መልስ የሚገኘው በአዲስ ኪዳን የመጀመሪያው ቁጥር ላይ ነው፡፡

*የዳዊት ልጅ የአብርሐም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ መጽሐፍ* (**ማቴዎስ 1፡1**)

የጥያቄው መልስ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ቤተ መቅደሱን የሚሠራው እሱ ነው፡፡ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ነው፡፡

ቂሮስ በዜና መዋዕል መገባደጃ ላይ የተናገራቸው ቃላት ኢየሱስ በማቴዎስ መጨረሻ ላይ ከተናገረው ጋር ተመሳሳይ መሆኑ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው፡፡

> *ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፤ ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ፡፡ እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፍስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፤ ያዘዝኋቸውንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡* **ማቴዎስ 28፡18–20**

“ታላቁ ተልዕኮ” ቤተ መቅደሱን ለመገንባት የተሰጠ ተእዛዝ ነው። ለዚህም ነው ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ታላቅ ሥራ ከሚሰሩት “ጋር እሆናለሁ” ያለው። ቤተ መቅደሱን ሲገነባ እግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ነው (**2 ዜና መዋዕል 36፥23 ይመልከቱ**)፤ እንደዚሁም ክርስቶስ ከሕዝቡ ጋር ሆኖ  ሕዝቡም ከእርሱ ጋር ይህንን ዘላለማዊ እና እየሰፋ ያለው የአምልኮ “ቦታ” መገንባታቸውን ይቀጥላሉ!